# ጨ

**ጨ** ከ "ጠ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

**ጨለሀ** ግ ደረቀ፥ ከረረ።

**ጨለሄ** ቅ ድርቅ ያለ፥ የከረረ።

**ጨለመ** ግ 1. ማታ ሆነ፥ የፀሃይ ብርሃን አለፈ፥ መሸ። 2. አልታይ አለ፥ ብርሃን ታጣ። *ቤቱ ጨለመ።* 3. ከለለ፥ ጋረደ፥ ሸፈነ። *ትርኢቱን እንዳላይ ጨለምከኝ።* 4. ጠቆረ።

**ጨለመበት** የሚያደርገው ግራ ገባው።

**ጨለማ(ጭለማ)** ስ የፀሃይም ሆነ የሌላ ነገር ብርሃን የሌለበትና ማየት የማይቻልበት ቦታ ወይም ጊዜ።

**ጨለማ ለበሰ** 1. ጠቆረ። 2. ጨለማን ተገን አደረገ፥ ተከለለ።

**ጨለማ በላኝ** ረዳት ወይም ደጋፊ አጣሁ፥ ለችግር ተጋለጥኩ።

**ጨለማ ዋጠው** 1. ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ ውስጥ ሆነ። 2. ግራ ገባው፥ ጨነቀው፥ የሚያደርገውን አጣ።

**ጨለማን ተገን አደረገ** ጨለማን ተከለለ(ተደብቆ ጉዳት ለማድረስ፥..)።

**ጨለማው ገፈፈ** ጨለማው ተወገደ፥ብርሃን ሆነ።

**ጨለማ ፊት** 1. ጥቁር የሆነ(ሰው)። 2. ፊቱ ላይ ፈገግታ ወይም ደስታ የማይታይበት፥ ያዘነ፥ የተቆጣ፥ የተቸገረ፥ ሁሌ የከፋው የሚመስል።

**አጨለመ** ግ 1. ብርሃን አሳጣ። 2. አሰናከለ፥ አበላሸ (እድልን፥ ተስፋን፥...)።

***ጨለቀ**

**ጭለቃ** ስ ከማር ወይም ከስኳር ጋር የተመታ የተልባ ወይም የኑግ ወይም የሰሊጥ ብጥብጥ።

**አጨለቀ** ግ ኑግን ወይም ተልባን ወይም ሰሊጥን ከማር ወይም ከስኳር ጋር አሸ፥ መታ፥ በጠበጠ።

**ጨለቁ** ስ በአብዛኛው ሙሉ በሙሉ ቢጫ ሆኖ ከክንፎቹ በላይ አሸዋማ የሆነ መልክ ያለውና የተዘራ እህል የሚበላ ወማይ የሚያክል ወፍ (ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

**ጨለቅለቃ** ስ አይን ላይ የሚያንፀባርቅ ወይም የሚያብረቀርቅ በሰፊው የተንጣለለ ውሃ።

**ጨለጠ** ግ 1. ባዶ አደረገ፥ ጨረሰ፥ አጠነፈፈ (ፈሳሽን፥ መጠጥን)። 2. ጨርሶ ጠጣ።

**ጨላጣ** ቅ (ስድብ) የማይጠግብ፥ ሞላጫ፥ ዋሾ።

**ጭላጭ** ስ በብርጭቆ ወይም በሌላ እቃ ውስጥ በትንሹ የቀረ ፈሳሽ።

**ጭልጥ አለ** ግ 1. በሃደበት ቀረ፥ ቆየ፥ ጠፋ። 2. ሄደ፥ ነጎደ፥ እብስ አለ(በሃሳብ፥ በአካል)። 3. አለቀ፥ ተሟጠጠ (ለፈሳሽ ነገር)።

**ጭልጥ ያለ** እልም ያለ፥ በሃይል፥ በጣም___ የሆነ። *ጭልጥ ያለ ሌባ /ጭልጥ ያለ ውሸታም።*

**ጭልጥ ያለ ገደል** ጅው ያለ ረጅም ገደል።

**አጫለጠ** ግ 1. ከዚያም ከዚህ እያንቃረረ ቀዳ ወይም ጠጣ። 2. አብሮ ጠጣ፥ አጣጣ (የመጠጥ ጓደኛ)።

**አጫላጭ** ስ የመጠጥ ቤት ጓደኛ።

**አንጫለጠ** ግ ጠጣ።

**ጨለጨለ** ግ ለመለመ፥ አቆጠቆጠ(የበልግ እህል፥ ሳር)።

**ጨሌ** ስ አዲስ የወጣ ለምለም ሳር ወይም ቡቃያ።

**ጭል ጭል አለ** ግ 1. መብቀል ጀመረ(ሳር)። 2. በትንሽ በትንሹ ወረደ፥ ፈሰሰ (ፈሳሽ)። 3. በትንሽ በትንሹ ታየ፥ ሆነ፥ ተደረገ።

**አጨለጨለ** ግ አቆጠቆጠ፥ አበቀለ፥ መለምለም ጀመረ።

**ጨለፈ** ግ 1. በጭልፋ፥ በጣሳ፥... አወጣ፥ ቀዳ፥ ጠለቀ (ወጥን፥ ፈሳሽን፥..)።2. በጥቂቱ ወሰደ፥ ቀነፀለ (ነገርን፥ ትምህርትን፥ ...)። 3. ነጠቀ፥ ቀማ።

**መጨለፊያ(መጭለፊያ)** ስ ጭልፋ።

**ጭሉፋት(ጩሉፋት)** ስ ቀማኛ፥ ነጣቂ፥ሌባ።

**ጭልፋ** ስ ወጥን፥ ፈሳሽ ነገርን፥ ንፍሮን፥... ከጎድጓዳ እቃ ውስጥ (ድስት፥ሳህን፥ ማሰሮ) ለማውጣት እንዲያገለግል ከእንጨት ወይም ከብረት ወይም ከቀንድ፥... የተሰራ ጎድጎድ ያለ ባለ እጀታ እቃ።

**ጨላጣ "ጨለጠ"** ስር ተመ.

**ጨሌ "ጨለጨለ"** ስር ተመ.

**ጨሌ** ስ ጥቃቅንና ክብ ሆኖ ከመስታወት ማእድን በተለያዩ ቀለማት የተሰራ፥ በክር ተሰክቶ የሚያያዝበት ቀዳዳ ያለውና ለአምልኮት፥ ለጌጥ፥...የሚጠቀሙበት ዶቃ መሰል ጌጥ።

**ጨሌ ጣለ** በጨሌ ጠነቆለ።

**ጨሌ ጣይ** ስ በጨሌ የሚጠነቁል።

**ጨሌያም** ቅ (ስድብ) በጨሌ፥ በጥንቆላ የሚያምን።

**ጨሌ ባለጋሜ** ስ እንደ ደጋን ቀልመም ያሉ ቀንዶችና ረዥም ሆነው ጫፋቸው ላይ ፀጉር ያሉባቸው ጆሮዎች ያሉት፥ ብዙውን ጊዜ ሳር፥

ቅጠላቅጠልና ውሃ በሚገኝበት ቆላማ ስፍራ የሚኖርና እንደ ፈረስ ጋማ ያለው ትልቅ የዱር እንስሳ ፤ ቀራ ፈረስ።

***ጨመለቀ**

**ጨምላቃ (ጨመለቅ)** ቅ 1. (ስድብ) እድፋም፥ ቆሻሻ። 2. (ስድብ) ለፍዳዳ፥ ሞልቃቃ፥ ባለጌ።

**ጭምልቅ አለ** ግ 1. በቆሻሻ ተበከለ፥ ተልከሰከሰ። 2. ጨቀየ፥ ዳጥ ወይም ጭቃ ሆነ። 3. ተሞላቀቀ፥ ተለፋደደ።

**ጭምልቅ አደረገ** ግ 1. ለወሰ፥ አጨማለቀ (በጭቃ፥ በቆሻሻ)። 2.አሞላቀቀ፥ አባለገ(ልጅን)።

**ተጨማለቀ** ግ 1. በጭቃ ወይም በቆሻሻ ተለወሰ፥ ተነካካ፥ ተበከለ። 2. ተነከረ፥ ተዘፈቀ። *በእዳ ተጨማልቋል።* 3. ተሞላቀቀ፥ ተለፋደደ፥ ባለገ።

**አጨማለቀ** ግ 1. አባለገ፥ አሞላቀቀ(ልጅን)። 2. በጭቃ ወይም በቆሻሻ፥... ለወሰ፥ አነካካ።

**ጨመረ** ግ 1. አከለ፥ በነበረው ላይ ደመረ። 2. አበረከተ፥ አበዛ። 3. አገባ፥ ዶለ፥ ከተተ። 4. አደገ፥ ትልቅ ሆነ። 5. በዛ፥ በረከተ። 6. ከፍ አደረገ። *ፍጥነቱን ጨመረ።*

**ጭማሪ** ቅ ፊት በነበረው ላይ በኋላ የታከለ፥ የተጨመረ (ደሞዝ፥ ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር)።

**ጭምር** መዋ. በተጨማሪ፥ አንድ ላይ፥ አብሮ። *አንተም ጭምር እንድትመጣ።*

**ተጨመረ** ግ 1. ቀድሞ በነበረው ላይ ተደመረ፥ ታከለ። 2. ከፍ አለ። *ደሞዝ ተጨምሮለታል።* 3.አንድ ሆነ፥ አበረ።*ልጅም ከአባቱ ጋር ተጨምሮ ሰደበኝ።*

**ተጨማሪ** ቅ 1. በነበረው ላይ የታከለ፥ ተደራቢ። ስ 2. በፊት የተነገረውን የሚያጎለብት፥ የሚያበረታ ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ሃሳብ፥ አስተያየት።

**በተጨማሪ** በተደራቢ፥ ሌላ፥ በማከልም ለማለት የሚያገለግል ቃል። *በተጨማሪ በቅርብ ቀን እንደምመጣ ላገልፅልህ እወዳለሁ።*

**ተጨማመረ** ግ ታከለ፥ ተደመረ።*ሌሎች ወጪዎች ሲጨማመሩ ገንዘቡ ይበዛል።*

**ጨመቀ** ግ 1. ፍራፍሬን ወይም ሌላ ነገርን በእጅ ወይም በመሳሪያ በመጫን ፈሳሹን ከውስጡ አወጣ። 2. እርጥብ ልብስንና የመሳሰለውን ነገር በሃይል በመጫን፥ በመጨበጥ፥ በመጠምዘዝ ያዘለውን ውሃ አስወገደ፥ አንጠፈጠፈ። 3. እንባ እንዲወጣው አይኑን ጭፍን ጭፍን አደረገ። 4. (የፅሁፍን፥ የንግግርን) ሃሳብ አሳጠረ፥ ፍሬ ነገሩን አጣርቶ አወጣ።5. በጣም፥ በሃይል ተጫነ ወይም አጠበቀ (ሲያቅፍ ሲጨብጥ።)

**መጭመቂያ** ስ እንደብርቱካን፥ አናናስ፥ ማንጎ፥... ያሉት ፍራፍሬዎች የሚጨመቁበት ወይም ከተለያዩ እፅዋት ዘይትን ወይም ሌላ ነገርን ጨምቆ ለማውጣት የሚያስችል መሳሪያ።

**ጭማቂ** ስ 1. ከብርቱካን፥ ከአናናስ፥ ከማንጎ፥... ተጨምቆ የወጣ መጠጥ። 2. ባጭሩ ተውጣጥቶ የቀረበ የሃሳብ ወይም የፅሁፍ ፍሬ ነገር።

**ጨመተ** ግ 1. አረመመ፥ ዝምተኛ ሆነ። 2. ረጋ፥ አደብ ገዛ፥ መንቀዥቀዥ ወይም መክለፍለፍ ተወ።

**ጭምት** ቅ 1. ዝምተኛ። 2. ረጋ ያለ፥ አደብ ያለው፥ የማይንቀዠቀዥ።

**አጨመተ** ግ ጭምት አደረገ።

**ጨመተረ** ግ የሰውነት ቆዳን ወይም ሌላ ነገርን አኮማትሮ ወይም አጨማድዶ ያዘ፥ ሸበሸበ፥ ጨረመተ (እርጅና፥ እሳት፥...)።

**ጨምታራ** ቅ ኮምታራ፥ ጨምዳዳ፥ ጨርማታ።

**ተጨማተረ** ግ ተኮማተረ፥ ተጨማደደ፥ ተጨራመተ።

**አጨማተረ** ግ አኮማተረ፥ አጨማደደ፥ አጨራመተ።

**ጨመደደ** ግ 1. ሸበሸበ፥ ሸመቀቀ፥ጨመተረ። 2. አጥብቆ ያዘ፥ ጨቦደ፥ እንቅ አደረገ። 3. አላንቀሳቅስ አለ፥ ጨበጠ፥ ቀሰፈ (ህመም)።

**ጨምዳዳ** ቅ 1. የተጨማደደ፥ የተሸበሸበ። 2. (ስድብ) ፊቱ የማይፈታ፥ ሁሌ የተከፋ የሚመስል። 3.ጨባጣ፥ ጨርማታ።

**ተጨማደደ** ግ ተጨማተረ፥ ተኮማተረ፥ ተሸማቀቀ።

**አጨማደደ** ግ አጨማተረ አኮማተረ፥ አሸማቀቀ።

**ጨመገገ** ግ ጨፈገገ፥ ቁጥርጥርአደረገ፥ አጠቆረ(ለምሳሌ ፊትን በብስጭት፥ በመከፋት፥..)፡

**ጨመጨመ**[1] ግ ደጋግሞ ወይም መላልሶ ሳመ።

**ጨመጨመ**[2] ግ በቤት ዋልታ ዙሪያ ማገር አሰረ፥ ታታ፥ ጠመጠመ።

**ጭምጭማት** ስ በዋልታ ዙሪያ ተጠጋግተው የሚማገሩ ወይም የሚታቱ ቀጫጭን ማገሮች በአንድነት።

**ተጨመጨመ** ግ በቤት ዋልታ ዙሪያ ማገር ተሰራ፥ ተታታ፥ ተጠመጠመ።

**ጨምላቃ** "*ጨመለቀ" ስር ተመ.

**ጨምባሳ** "ጨነበሰ" ስር ተመ.

**ጨምታራ** "ጨመተረ" ስር ተመ.

**ጨምዳዳ** "ጨመደደ" ስር ተመ.

**ጨምጫማ** ቅ አይኑ ጭፍንፍን ያለና እንባ ያዘለ። *አይነ ጨምጫማ።*

***ጨረመመ**

**ጨርማማ** ቅ 1. የተወላገደ፥ የተጨራመተ፥ ስርጉድጉድ:: 2. (ስድብ) ጨርማታ፥ ፊቱ የተጨማደደ::

**ተጨራመመ** ግ ተጣመመ፥ ተጨራመተ፥ ተወላገደ::

**አጨራመመ** ግ አጣመመ፥ አጨራመተ፥ አወላገደ::

***ጨረመተ**

**ጨርማታ** ቅ 1. ጉብጥብጥ ያለ፥ የተሰረጎደ፥ የተወላገደ(ቆርቆሮ ወይም ሌላ ነገር):: 2. (ስድብ) ሰውነቱ የተጨማደደ፥ያረጀ ወይም በጣም የሸመገለ::

**ተጨራመተ** ግ ጉብጥብጥ፥ እጥፍጥፍ አለ፥ ተኮማተረ::

**አጨራመተ** ግ ጉብጥብጥ፥ እጥፍጥፍ፥ ውልግድግድ አደረገ፣ ሰረጎደ፥ አኮማተረ::

***ጨረረ**[1]

**ጭርር አለ** ግ እርር፥ ድብን፥ ቅጥል አለ::

**ጭርር አደረገ** ግ እርር፥ ድብን፥ ቅጥል አደረገ::

**ተንጫረረ** ግ 1.ተቃጠለ፥ አረረ፥ ደበነ፥ ተኮማተረ(በፀሃይ..) :: 2.ደበነ፥ አረረ (በንዴት)::

**አንጫረረ** ግ አቃጠለ፥ አሳረረ፥ አደበነ፥አኮማተረ::

***ጨረረ**[2]

**ጨረራ** ስ 1. ጨረር:: 2. ከኤሌክትሪክ ወይም ከሌላ ተመሳሳይ ነገር የሚመነጭ የብርሃን ሃይል ወይም ሙቀት::

**ጨረር** ስ 1. ከፀሃይ የሚፈነጠቅ ብርሃን፥ ጮራ::2. በጣሪያ፥ በግድግዳ፥ በበር፥ በመስኮት ብስ በኩል ወይም ቀዳዳ የሚገባ የፀሃይ ብርሃን::

**የጨረር ሃይል** ስ ከፀሃይ ብርሃን ወይም ሙቀት የሚገኝ ሃይል ወይም ጉልበት::

**ጮራ** ስ ከፍተኛ ሃይል የሌለውና ፀሃይ ስትወጣ ፍንጥቅጥቅ ብሎ የሚታይ የፀሃይ ብርሃን፣ የብርሃን ፍንጣቂ::

**ጨረሰ** ግ 1. አጠናቀቀ፥ ፈፀመ፥ ከወነ፥ ደመደመ፥ አበቃ፥ አከተመ:: 2. ባዶ አደረገ፥ አሟጠጠ:: ምግቡን ጨረሰ:: 3. ገደለ::4. ጉዳት አደረሰ:: ተባይ ጨረሰን/ ሌባ ጨረሰን:: 5. የተወሰነ ጊዜ (ቀን ወር፥...) ወሰደ፥ ፈጀ:: ስራው አስር አመት ጨረሰ:: 6. ፈጀ፥ ተጠቀመ:: በዚህ ወር ብዙ ማገዶ ጨርሰናል:: 7. በላ:: መኪናዋ ለ5 ኪሎ ሜትር ጉዞ ሁለት ሊትር ቤንዚን ትጨርሳለች:: 8. ካለበት ደረጃ በላይ መሄድ የማይችልበት ሁኔታ ላይ ደረሰ፥ አሟጠጠ:: ትእግስቱን ጨረሰ:: 9. አለቀበት::

ልብሱን ጨርሷል::

**ጨርሶ** ተው.ግ. ፈፅሞ:: አረቄማ ጨርሶ አይጠጣም/ ጨርሶ ይግርሀ::

**መጨረሻ** ተው.ግ 1.መፈፀሚያ ፥ ማብቂያ፥ ማጠናቀቂያ:: 2 በጣም፥ ከሁሉም በስተሂላ:: መጨረሻ ላይ መጥቶ ከሁሉም የተሻለ ውጤት አገኘ::

**በመጨረሻ** በማጠቃለያ ወይም ባጠቃላይ ለማለት የሚያገለግል የአረፍተ ነገር ማያያዣ:: በመጨረሻ ልገልፅ የምፈልገው...::

**በመጨረሻው ሰአት** ለፍፃሜ ትንሽ ሲቀረው ወይም የተወሰነው ጊዜ ሊያልቅ ሲል::በመጨረሻዋ ደቂቃ የእሺታ ቃሉን ሰጠ/ በመጨረሻው ሰአት በምርጫው እንደሚሳተፍ ገለፀ::

**የመጨረሻ** 1. የማይቀየር፥ የማይሻሻል፥ የማይለወጥ:: የመጨረሻ ቃል/ የመጨረሻ ትእዛዝ: 2. አቻ የማይገኝለት:: የመጨረሻ ጥሩ ሰው ነው:: 3. ማኂጠሚ::የመጨረሻ ልጃቸው ዝሬ ነው::

**ጭራሽ** ተው.ግ. 1. በፍፁም፥ ፈፅሞ::ጭራሽ ሳላገኘሁም:: 2. ይባስ ብሎ፥ እንዲያውም:: ይቅርታ እንደመጠየቅ ጭራሽ ታኮርፋለህ ?

**በጭራሽ** ተው.ግ. በምንም አይነት፥ ፈፅሞ:: በጭራሽ አልነግርሀም::

**ጭራሹን** ጭራሽ::

**ጭርስ አለ** ግ 1. ለሞት ተዳረሰ፥ ደከመ:: 2. አለቀ::

**ጭርስ አደረገ** ግ 1.ፈፅሞ ጨረሰ፥ ምንም ሳይቀር አሟጠጠ:: 2 .አደከመ፥ ለሞት አደረሰ:: ሰውነቱን በሽታ ጭርስ አደረገው::

**ተጨረሰ** ግ አለቀ:: ስራው መቼ እንደተጨረሰ አላውቅም::

**ተጫረሰ** ግ ተፋጀ፥ ተጋደለ፥ ተባለቀ::

**አጨራረስ** ስ በአንድ የድርጊት ሂደት ማጠቃለያ ወይም ውጤት በማሳያ ደረጃ ላይ የሚታይ ክንዋኔ::ቡድኑ ጥሩ ጫወታ ያሳይና አጨራረስ ላይ ደካማ ይሆናል::

**አጫረሰ** ግ 1. የሌላውን ገንዘብ አብሮ በመጠቀም ቶሎ እንዲያልቅ አደረገ:: 2. እርስ በርሱ እንዲገዳደል፥ እንዲተላለቅ አደረገ::

**አጫራሽ** ቅ የሌላውን ገንዘብ አብሮ በመጠቀም፥ ጠጣት፥...እንዲባክን የሚያደርግ::

**አስጨረሰ** ግ 1. አስፈጀ፥ አስገደለ:: 2. የተጀመረው ነገር፥ ወሬ፥ ስራ፥... እንዲያልቅ አደረገ::

***ጨረቀ**

**ጭርቂያም** ቅ (ስድብ) ሽንታም::

**ጭርቅ አለ** ግ በትንሹ ፈሰስ ብሎ ቆመ

(ብዙውን ጊዜ ለሽንት)::

**ጭርቅ አደረገ** ግ በትንሹ ሸና፥ ጠብጠብ አደረገ::

**አጨረቀ** ግ ሽንቱን በትንሹ ሸና::

**ጨረቂት** ስ ንጣት ያለው የማሽላ አይነት::

**ጨረቃ** ስ በመሬት ዙሪያ እየዞረች ከፀሃይ የምታገኘውን ብርሃን ወደ መሬት የምትፈነጥቅ፥ ጠፈር ውስጥ ካሉት አካላት አንዱ ወይም በሌላ ፕላኔት ዙሪያ የሚዞር ተመሳሳይ አካል::

**ጨረቃ ምድር ያዘች** ኡደቷን ወደ መጨረስ ተቃረበች፥ ጧት ጧት መታየት ጀመረች::

**ጨረቃ ተወለደች** ጨረቃ በትንሹ ታየች፥ ተገለጠች፥ ብቅ አለች (እንደገና ኡደቷን ለመጀመር)::

**ጨረቃ ነው** የጨረቃ ብርሃን አለ (ማታ ወይም ሌሊት ላይ)::

**ጨረቃ ወጣች** ጨረቃ ብርሃኗን ሰጠች፥ አሳየች::

**ጨረቃ የመሰለ** ነጭ የሆነ፥ ፈካ ብሎ የሚታይ ::

**የጨረቃ አር** ስ ከእንጨት ላይ ተጣብቆ የሚገኝና ጠበቅ አድርገው ሲይዙት እርጥቡ የሚፈርጥ፥ ደረቁ ፍርክስ የሚል፥ ነጣ ወይም ቀላ ያለ እንቡጥ መሰል ነገር::

**ጨረቋ** ግ ፍሬ ጀመረ፥ጮርቃ ሆነ::

**ጮርቃ** ቅ 1. እንጭጭ፥ ለጋ (ፍሬ):: 2. በጣም ያላደገ፥ ያልጠና (ልጅ):: 3. (ዘይ.) በአስተሳሰቡ ያልበሰለ (ሰው)::

**ጮርቃ በርበሬ** ስ ያልበሰለ፥ ያልቀላ ቃሪያ በርበሬ::

**ጨረባ** ስ መልኩ ቡላ የሆነ የወፍ አይነት፤ በቋል፥ ጥሬ ፈጅ::.

**የጨረባ ተዝካር** ጫጫታ የበዛበት፥ መደማመጥ የሌለበት፥ ስነ ስርአት ያጣ ስብሰባ ወይም ንግግር::

**ጨረተ** ግ በመንተብ፥ በመፋቅ፥ በመፋተግ ፀጉር ወይም ጭራ መሰል ነገር አወጣ::

**ጭረት** ስ በመንተብ፥ በማለቅ፥ በመፋተግ ምክንያት የወጣ ፀጉር ወይም ጭራ መሰል ነገር::

**አጨረተ** ግ ፋቀ፥ ፈገፈገ፥ ጭረት እንዲወጣ አደረገ::

***ጨረተ**

**ጨረታ(ጫረታ)** ስ አንድን ነገር የመሸጫ መነሻ ዋጋውን ወስኖ፥ከዚያ በላይ ብልጫ ያለውን ዋጋ ለሚሰጥ ገዢ ለመሸጥ የሚዘጋጅ የዋጋ ውድድር(ፉክክር) ልዩ የሽያጭ ስርአት:

**ለጨረታ ቀረበ** አንድ ነገር በጨረታ ወይም በውድድር ዋጋ አብለጦ ለከፈለ እንዲሸጥ ለገበያ ወይም ለሽያጭ ቀረበ::

**በጨረታ ገዛ** አንድን ነገር በውድድር የተሻለ ክፍያ ሰጥቶ ገዛ::

**ጨረታ ወጣ** አንድ ነገር በጨረታ እንዲሸጥ ለገበያ ቀረበ::

**ጨረታ አወጣ** አንድን ነገር በጨረታ ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ወይም አንድን ስራ ለማሰራት ለውድድር አቀረበ::

**የጨረታ ማስታወቂያ** ስ አንድን ነገር በጨረታ ለመግዛት፥ ለመሸጥ ወይም አንድን ስራ ለማሰራት ተጫራቾችን ለውድድር የሚጋብዝ ማስታወቂያ::

**ተጫረተ** ግ ለግዥ ወይም ለሽያጭ ወይም አንድን ተግባር ለማከናወን በዋጋ ተፎካከረ፥ ተወዳደረ (በፅሁፍ ወይም በቃል፥ በግልፅ ወይም በምስጢር)::

**ተጫራች** ቅ የጨረታ ተፎካካሪ፥ ተወዳዳሪ (ሰው)::

**አጫረተ** ግ በዋጋ አወዳደረ፥ አፎካከረ፥ አበላለጠ (በቃል ወይም በፅሁፍ፥ በግልፅ ወይም በምስጢር)::

**አጫራች** ቅ ጨረታ የሚያካሂድ (ሰው)::

**ጨረነቀ** ግ ጨቆነ፥ ተጫነ::

**ጨርናቃ** ቅ አንገተ አጭር (ሰው)::

**ጨረገደ** ግ 1. ሳርን፥ ቅጠልን፥... በአንድነት አጨደ:: 2. መታ፥ ደበደበ (በሽመል፥ በዱላ፥...):: 3. በብዛት ጥርግ አድርጎ በላ::

***ጨረገገ**

**ተንጨረገገ** ግ ተንዠረገገ፥ ተንጠለጠለ(ፍሬ)::

**አንጨረገገ** ግ አንዠረገገ፥ ብዙ ፍሬ አፈራ::

***ጨረጨረ**

**ጭርጭር አለ** ግ ተንጨረጨረ::

**ተንጨረጨረ** ግ 1. ተጠበሰ፥ ተቆላ፥ ባእሳት በጣም ተቃጠለ (ስጋ፥ ቅቤ፥...) :: 2. ተከነ፥ አረረ፥ ደበነ(በንዴት)::

**አንጨረጨረ** ግ 1. ጠበሰ፥ ቆላ፥ እስኪያር አቃጠለ:: 2. አተከነ፥ አሳረረ፥ አናደደ፥ ክፉኛ አበሳጨ:: 3. አስጮሀ::

**ጨረጨሰ** ግ በጣም አረጀ፥ ሸመገለ::

**ጨርጫሳ (ጨረጨሰ)** ቅ (ስድብ) ያረጀ ያፈጀ፥ አሮጌ፥ ሽማግሌ ወይም አሮጊት::

**ጨረፈ** ግ በጨረፍታ መታ፥ ለኮፍ ወይም ነካ አደረገ::

**ጨረፍታ** ስ በመጠኑ፥ በከፊል፥ በትንሹ የማየት፥ የመስማት፥ የመምታት፥... ሁኔታ:: *በጨረፍታ አያት::*

***ጩረፈፈ**

**ጭርፍፍ አለ** ግ ተንጩረፈፈ::

**ተንጩረፈፈ** ግ ተንጨፈረረ፥ ተንዘረፈፈ::

**አንጩረፈፈ** ግ አንጨፈረረ፥ አንዘረፈፈ::

**ጨረፍታ "ጨረፈ"** ስር ተመ.

**ጨርማማ "ጨረመመ"** ስር ተመ.

**ጨርማታ "ጨረመተ"** ስር ተመ.

**ጨርቅ** ስ ከሱፍ ወይም ከጥጥ ወይም ከሃር ክር የሚዘጋጅና ለልብስ፥ ለመሸፈኛ፥ ለመጋረጃ፥... የሚያገለግል የፋብሪካ ስራ ወይም የሽመና ውጤት::

**ጨርቁን ጣለ** አበደ፥ ወፈፈ::

**ጨርቄን ማቄን አለ** ሰበብ፥ ምክንያት አበዛ::

**ጨርቅ ሆነ** 1. ለሰለሰ፥ ለፋ (ቆዳ):: 2. በጣም ሰከረ:: 3. በህመም ምክንያት ሰውነቱ መነመነ፥ ደከመ::

**ጨርቅ ለባሽ** (የን.አነ.) መናጢ ድሃ፥ ምንም የሌለው::

**ጨርቃም** ቅ (የን. አነ.) ቅርንጥሳም፥ ዘባተሏም፥ ቡትቷም::

**ጨርናቃ "ጨረነቀ"** ስር ተመ.

**ጨርጫሳ "ጨረጨሰ"** ስር ተመ.

**ጨሰ (ጤሰ)** ግ 1. በመንደድ፥ በመቃጠል ምክንያት በነነ፥ ተነነ፥ ተትጎለጎለ፥ ወጣ (ጢሱ፥ እንፋሎቱ):: 2. ተናደደ፥ ተበሳጨ:: 3. በጣም ተወደደ፥ ዋጋ ቀጠለ::*የመኪና ዋጋ እንደድሮው ኣይደለም፤ ጨሷል::* 4. በጣም አረጀ፥ ጨረጨሰ:: *የጨሰ ሽማግሌ::*

**ሳይጨስ ነደድ** ሲነድ ጢስ የማይወጣው ጭራሮ እንጨት::

**ጪስ(ጢስ)** ስ ማገዶ፥ ማእጠንት ወይም ሌላ ነገር ሲቃጠል ወይም በእሳት ሲያያዝ የሚፈጠረው ጉም ወይም እንፋሎት መሰል ነገር::

**በጪስ** በእያንዳንዱ ቤት::*በጪስ ሁለት ሁለት ብር ከፈልን::*

**ጪስ መታው** ጪስ ጨሰበት ወይም ጪስ መሰለ::

**[የ] ጪስ እንጨት** ስ ሲቃጠል ጪሱ ጥሩ ሽታ ያለው እንጨት::

**ጪስ መውጫ** ስ የመኪናን ወይም የሌላ ሞተርን ለማንቀሳቀስ የሚቃጠለው የቤንዚን ወይም የናፍታ ጪስ ወደ ውጭ የሚወጣበት ቧንቧ መሰል አሸንዳ::

**ጪሰኛ (ጢሰኛ)** ስ በሰው መሬት ላይ ቤት ሰርቶ እያረሰ ሲሶ፥ እርቦ ወይም እኩሌታ ለባለመሬቱ ይሰፍር የነበረ ገበሬ::

**ተጯጯሰ** ግ 1. ተያያዘ፥ ተቀጣጠለ (እሳቱ)::2.ተጧጧቀ፥ተጋጋለ (ጠቡ፥ ነገሩ፥...)::

**አጨሰ** ግ 1. ማገዶን፥ የጢስ እንጨትን፥ ማእጠንትን በማቃጠል ጪስ እንዲወጣ አደረገ:: 2. ማገ፥ ጠጣ(ትንባሆን፥ ሲጋራን):: 3. መታ (በጥፊ፥ በጥይት):: 4. በጥሩ ዋጋ ሸጠ:: 5. አበገነ፥አናደደ::

**ማጨሻ** ስ እጣንና የመሳሰለው የሚጨስበት ገል ወይም ሌላ እቃ::

**አጫሽ** ስ ሲጋራ የሚያጨስ ወይም የሲጋራ ሱሰኛ::

**አጫጨሰ** ግ 1. ኣያያዘ፥ ኣቀጣጠለ(እሳትን):: 2. ኣጧጧቀ፥ ኣጋጋለ (ጠብን፥ ነገርን)::

**ማጫጫሻ** ስ ማያያዣ ወይም ማቀጣጠያ ኩበት፥ ፋንድያ፥ ግብስብስ፥...::

**ጨቀየ** ግ በውሃ ወይም በዝናብ ራሰ፥ በካ፥ ተጨማለቀ፥ ጭቃ ሆነ(መሬት)::

**ጭቃ** ስ 1.በዝናብ ወይም በውሃ የራሰ፥ የበካ ወይም የተጨማለቀ መሬት ወይም አፈር:: 2. ማጥ፥ አረንቋ፥ ረግረግ መሬት:: 3. (ስድብ) ረሀጥ፥ ሰነፍ (ሰው)::

**ጭቃ መራጊ** ስ ሙያው ግድግዳን በጭቃ መምረግ የሆነ ሰው:: ጭቃ ረጋጭም ይባላል::

**ጭቃ ረገጠ** ግድግዳ የሚመረግበትን ጭቃ ከጭድ ጋር አዋህዶ አቦካ::

**ጭቃ ረጋጭ / ኣቡኪ** ስ ለምርግ ስራ ተስማሚነት ያለውን አፈር በውሃ እያላቆጠና ከጭድ ጋር እያቀላቀለ እስኪቦካ ድረስ በመርገጥ የቤት ግድግዳን የሚመርግ ባለሙያ::

**[የ] ጭቃ ሱሪ** ስ በክረምት ወይም በጭቃ ጊዜ የሚለበስ ኣጭር ሱሪ::

**የጭቃ እሾህ** ሳይታወቅበት በስውር የሚያጠቃ ወይም የሚጎዳ፥ ተንኮለኛ (ሰው)::

**[የ] ጭቃ ጅራፍ** የሚያስቀይም ወይም የሚያስከፋ ንግግር (ሳይጠብቁት የተነገረ)::

**ጭቃ ሹም** ስ በቀድሞ ስርኣት የመሬት ስሪት ውስጥ በየአካባቢው በህዝብ ተመርጦ፥ ከአጥቢያ ዳኛና ከመልከኛ በታች እንደ መንግስት ሹም ሆኖ የሚያገለግል ሰው::

**ጭቃ ቀለም** ስ የለደለደ ቀለም ያለው መዓፈያ፤ እስኪርቢቶ::

**ጭቃ ቅባት** ስ ፈሳሽ ያልሆነ ቅባት::

**ጭቃ ቤት** ስ ግድግዳው በእንጨት ተሰርቶ በጭቃ የተመረገ ቤት (የሸክላ ወይም የድንጋይ ቤት ያልሆነ)::

**ጭቃ አፍ** ቅ ሲሳደብ ለኣፉ ለከት የሌለው፥ ተሳዳቢ::

**ጨቀጨቀ**[1] ግ 1. ነዘነዘ፥ ወተወተ፥ ነተረከ፥

በነገር አሰለቸ:: 2. ጠቀጠቀ፥ ደፈነ፥ ወተፈ:: 3. መሳልሰ ወጋ (በጦር፥ በሹል ነገር፥…):: 4. እርጥብ ጌሾን፥ ቃሪያን፥ በቆሎን፥… ወቀጠ::

**መጨቅጨቂት (መጨቅጨቂያ)** ስ እንጀራ ሲጋገር እንዳይነፍስበት በአክንባሎና በምጣድ መሃል ያለውን ቀዳዳ ለመድፈን በውሃ እየተራሰ የሚጠቀጠቅ የጨርቅ ትልታይ::

**ጨቅጫቃ** ቅ ነዝናዛ፥ ነትራካ፥ በነገር የሚያሰለች::

**ጭቅጭቅ** ስ 1. ንዝንዝ፥ ንትርክ:: 2. ጠብ፥ አለመስማማት:: 3. ሙግት፥ የፍርድ ቤት ነገር::

**ጭቅጭቀኛ** ቅ ተነዛናዥ፥ ተነታራኪ::

**ተጨቃጨቀ** ግ 1. ተነዛነዘ፥ተነታረከ:: 2. ተከራከረ፥ ተሟገተ፥ ተጣላ::

**ተጨቃጫቂ** ቅ ተነዛናዥ፥ ተነታራኪ፥ ጭቅጭቅ የማይሰለቸው::

**አጨቃጨቀ** ግ አጣላ፥ አወዛገበ፥ አነታረከ::

**አጨቃጫቂ** ቅ አወዛጋቢ፥ የሚያጣላ፥ የሚያነታርክ፤ አከራካሪ የሆነ(ነገር፥ ንብረት፥…)::

**ጨቀጨቀ**[2] ግ ጨቀየ፥ በዝናብ ወይም በውሃ ራሰ::

**ጨቀጨቅ** ስ ውሃ ያለበት ጭቃማ መሬት::

**ጨቅላ** ስ 1. አራስ፥ ለጋ፥ ሰውነቱ ያልጠነከረ፥ ርጥብ ህፃን፤ ልጅ:: 2. (ዘይ.) አስተሳሰቡ ያልበሰለ፥ እርቆ የማያስብ፥ የማያስተውል::

**ጨቅጫቃ** "**ጨቀጨቀ**[1]" ስር ተመ.

**ጨቆነ** ግ 1. ተጫነ፥ ገፍቶ፥ ረግጦ፥ አጣብቆ ያዘ:: 2. በአገዛዙ ወይም በሃላፊነቱ በደለ፥ ግፍ ፈፀመ፥ አሰቃየ፥ መብት ገፈፈ::

**ጨቋኝ** ቅ ግፍ ሰሪ ፥ በዳይ፥ መብት የሚነፍግ (በአስተዳደር፥ በአገዛዝ)::

**ጭቁን** ቅ መብቱና ነፃነቱ የተገፈፈ፥ በደል፥ ስቃይ የደረሰበት::

**ጭቆና** ስ 1. መብትን፥ ነፃነትን የመግፈፍና የማሰቃየት ድርጊት:: 2. የመጨቆን፥ መብት የማጣት ወይም የመከልከል ሁኔታ::

**ተጨቆነ** ግ ተሰቃየ፥ ግፍ ተሰራበት፥ በደል ተፈፀመበት፥ መብቱ ተገፈፈ(በአስተዳደር፥ በአገዛዝ፥…)::

**ተጨቋኝ** ቅ በደል፥ ስቃይ፥ ግፍ የደረሰበት (ሰው)::

***ጨበረረ**

**ጨበረር (ጨብራራ)** ቅ የተንጨበረረ፥ የተንጨፈረረ፥ ያልተበጠረ (ፀጉር)::

**ጨበሬ** ቅ የተንጨበረረ፥ የተንጨፈረረ፥ የቆመ፥ ያልተበጠረ(ፀጉር)::

**ተንጨበረረ** ግ ተንጨፈረረ፥ ቆመ (ፀጉር)::

**አንጨበረረ** ግ አንጨፈረረ፥ አጎፈረ፥ አቆመ (ፀጉርን) ::

**እንጭብሬ** ስ ራሰ ብትን ዘንጋዳ::

***ጨበረበረ**

**ተጭበረበረ** ግ ተታለለ::

**አጭበረበረ** ግ አታለለ፥ አሳሳተ፥ አደናገረ::

**አጭበርባሪ** ቅ አታላይ፥ አወናባጅ::

**ጨበሬ**[1] ስ ቀይነት ያለው አፈር::

**ጨበሬ**[2] "***ጨበረረ**" ስር ተመ.

***ጨበሰበሰ**

**ጨበስባሳ** ቅ በጭስ፥ በበሽታ፥… የተጭበሰበሰ፥ የተጨናበሰ፥ ሞጭሟጫ (አይን)::

**ተጭበሰበሰ** ግ 1. ተጭፈነፈነ፥ በደንብ አላይ አለ (አይን):: 2. በደንብ አልነድ አለ፥ ጨሰ (እርጥብ እንጨት)::

**አጭበሰበሰ** ግ አጭፈነፈነ፥ አላሳይ አለ (አይንን፥…)::

**ጨበጠ** ግ 1. እጁን ከሌላ ሰው እጅ ጋር በማያያዝ ሰላምታ ሰጠ ወይም ሰላምታ ተለዋወጠ:: 2.ያዘ፥ የራሱ አደረገ:: *ስልጣን መንግስት ጨበጠ::* 3. ጭብጦ አዘጋጀ:: 4. አንድን ነገር በጣቶቹና በመዳፎቹ አስገብቶ ያዘ:: 5. ጣቶቹን ኮርምቶ በመዳፉ ላይ ያዘ ወይም ለቡጢ መምቻ እንደሚሆን አደረገ:: 6. ዋጋውን አስወደደ:: *ነጋዴው የሚሸጥበትን ዋጋ ጨበጠ::* 7. ጉዳዩን አስሮ ያዘ፥ እንዳይፈፀም አደረገ:: *ጉዳዩ እንዳይፈፀም የጨበጠብኝ ጉቦ ፈልጎ ነው::* 8. ኮረመተ፥ አሰረ፥ አሰቃየ (ብርድ፥ ረሃብ፥ በሽታ፥ ችግር፥…):: *ብርዱ ሰውነቴን ጨብጦታል::* 9. አወቀ፥ ተረዳ፥ ያዘ(ጉዳይን፥ ነገርን፥…):: *ፍሬ ሃሳቡን ጨብጦታል::* 10. (ዘይ.) አስቀመጠ፥ አጠራቀመ፥ ያዘ (ሃብትን፥ ንብረትን፥…)::

**መጨበጫ** ስ የአንድ ነገር መያዣ ወይም እጀታ፤ በእጅ አጥብቆ ለመያዝ አመቺነት ያለው የአንድ ነገር አካል::

**መጨበጫ የለውም** 1.በግልፅ አይታወቅም፥ ዝብርቅርቅ ነው፥ አይያዝም (ሃሳቡ፥ ፍላጎቱ፥…):: 2.ለመያዝ አያመችም::

**ጨበጣ (የጨበጣ ውጊያ)** ስ በሳንጃ ወይም በሰደፍ ወይም በሌላ በእጅ የሚያዝ መሳሪያ በመጠቀም አጠገብ ለአጠገብ ሆኖ ግብግብ የሚጋጠሙበት ውጊያ::

**ጨባጣ** ቅ (ስድብ) 1. ኮርማታ፥ አጭርና ቀጭን:: 2. በህመም ምክንያት አካሉ የተኮራመተ (ሰው)::

**ጨባጭ** ቅ ንፉግ፥ ስስታም::

**ጭብጥ** ስ የአንድ ነገር ወይም ጉዳይ ፍሬ ሃሳብ::

**ጭብጡን አፈሰሰ** ጭብጡን ለመስካሪ ነገረ ወይም ገለጠ+ አስረዳ::

**ጭብጥ** ስ 1. የተጨበጠ እጅ+ ኩርኩም+ ቡጢ+ ጡጫ:: 2. በአንድ እጅ መዳፍ ውስጥ የተጨበጠ (ጥሬ+ ሳር+...):: 3. ትንሽ ወይም ጥቂት ነገር:: *ጭብጥ ቆሎ ይዞ ወደ ላሻሮ ጢጋ::*

**ጭብጦ** ስ 1. ተጋግሮ በትኩሱ የተድበለበለ እንጀራ (የመንገደኛ ስንቅ):: 2. ከበሶና ከማር ተድቦልቡሎ የተዘጋጀ ምግብ+ ስንቅ::

**ተጨበጠ** ግ 1. ተያዘ+ ተገኘ+ ታወቀ:: *ሃሳቡ ተጨብጦልኛል::* 2. ተኮራመተ+ ታሰረ( በሃዘን+ በበሽታ+...)::

**የተጨበጠ** በግልፅ የታወቀ+ የተረጋገጠ::

**ተጨባጭ** ቅ በእርግጥ ያለ+ የሚኖር ወይም በአካል የሚገኝ (ለነገር+ ለክስተት+ ለአካላዊ ነገር):: ،

**ተጨባጭ ሁኔታ** ስ አንድን ነገር አስመልክቶ በአንድ ወቅት የሚታየው ወይም ያለው ነባራዊ (ትክክለኛው) ሁኔታ ወይም ነገር::

**ተጨባበጠ** ግ 1. ተኮራመተ:: 2. ተጣጠፈ+ ተጨማደደ:: 3. የእጅ ሰላምታ ተለዋወጠ+እጅ ለእጅ ተያያዘ::

**አጨባበጠ** ግ በእጅ ማጨባበጥ አማካይነት አስማማ+ አስታረቀ::

**አስጨበጠ** ግ 1. የጉዳዩን ፍሬ ሃሳብ ወይም ቁም ነገር አስያዘ+ አስረዳ:: 2. ሰጠ+ በእጁ እንዲይዝ አደረገ::

**ጨበጨበ** ግ ለመለመ+ አቆጠቆጠ+ ቅጠል አወጣ::

**አጨበጨበ** ዝ.ከ.

***ጨበጨበ**

**ጭብጨባ** ስ ሁለት ውስጥ እጆችን በማማታት የሚፈጠር ድምፅ (ዘፈንን+ለቅሶን ለማዳመቅ፤ ደስታን+ ስምምነትን ለመግለፅ እንዲሁም ለመጣራት የሚደረግ)::

**ተጨበጨበ** ግ ጭብጨባ ተደረገ::

**አጨበጨበ** ግ 1. ሁለት ውስጥ እጆችን አግታ+ አጣፋ፤ ቸብቸብ አደረገ:: 2. ነገር አዳነቀ+ አቶከቶከ::

**አጨበጨበበት** ተደሰተበት+ ተዝናናበት+ ጠጣበት+ ጨፈረበት (ገንዘቡን)::

**አጨብጭቦ ቀረ** ምንም ሳያገኝ ባዶ እጁን ቀረ::

**አጨብጭቦ ተቀበለ** በደስታ ተቀበለ::

**አጨብጫቢ** ቅ ነገር አዳናቂ+ አቶክቷኪ+ አጎብጓቢ::

**አስጨበጨበ** ግ አድናቆትን አገኘ ወይም አተረፈ ደስ አሰኘ::

**ጨቡዴ** "ጨቦደ" ስር ተመ.

**ጨባ** ስ ክሰል የሚሆን ወይም የወተት ማእጠንት የሚያደርጉት የግራር አይነት::

**ጨባጣ** "ጨበጠ" ስር ተመ.

**ጨባጭ** ዝ.ከ.

**ጨብራራ** "*ጨበረረ" ስር ተመ.

**ጨብጥ(ጨብጦ)** ስ ሽንት የሚከለክልና የሚያቃጥል የአባለ ዘር በሽታ::

**ጨቦደ** ግ አጥብቆ ያዘ+ጨበጠ+ አፈፍ አደረገ::

**ጨቡዴ** ቅ ሃይለኛ+ ጠንካራ+ ጉልበተኛ (ሰው)::

**ጨነቀ** ግ ቸገረ+አወከ:: *ለበሽታው መድሃኒት ሰላጣ ጨነቀው::*

**ጨነቀኝ ጠበበኝ** ቸገረኝ+ የማደርገውን አጣሁ+ ተሰቃየሁ::

**ጭንቅ** ስ ችግር+ ስቃይ+ መከራ+ ፍርሃት::

**የጭንቅ አማላጅዋ** ስ የቅድስት ማርያም የቅፅል ስም::

**ጭንቀት** ስ በህመም በልዩ ልዩ ችግር ምክንያት አእምሮን+የሚያሰቃይ+ የሚረብሽ ወይም በጣም የሚያሳስብ መጥፎ ስሜት::

**ጭንቀታም** ቅ ፈሪ፤ በሆነው ባልሆነው ጭንቀት ወይም ፍርሃት የሚያበዛ::

**ተጨነቀ** ግ ተቸገረ+ ተጠበበ+ ታወከ+ ተሰቃየ+ የሚያደርገውን አጣ+ግራ ተጋባ (በህመም+ በችግር+ በሃሳብ+...)::

**ተጨናነቀ** ግ በጣም ተጣበበ+ ተጠጋጋ+ ተደራረበ+ አላፈናፍን አለ::

**አጨናነቀ** ግ በጣም አጠጋጋ+ አደራረበ+ አጣበበ::

**አስጨነቀ** ግ አስቸገረ+ መፈናፈኛ ከለከለ::

**ጨነቆረ** ግ 1. አንድ አይኑን ጨፍኖ አየ ወይም ተመለከተ:: 2. በቀዳዳ አየ:: 3. የተጨናቆረ ወይም የተጭፈነፈነ ፅሁፍ ፃፈ+ ቦጫጨረ::

**ጨንቋራ(ጭንቁር)** ቅ ጨምባሳ( ለአይን)::

**ጭንቁርቁር** ቅ 1. ጭምብስብስ:: 2. በደንብ የማይነበብ+ የተቦጫጨረ (ፅሁፍ)::

**ተጨናቆረ** ግ (ለፅሀፈት) የማይነበብ ሆነ+ ተቦጫጨረ::

***ጨነበሰ**

**ጨንባሳ (ጨምባሳ)** ቅ 1. በደንብ የማይነድ+ የሚጨስ (እሳት):: 2. የተጨናበሰ+ በደንብ የማያይ (አይን)::

**ጭንብስብስ** ቅ የተጨናበሰ+ በደንብ የማያይ (አይን)::

**ተጨናበሰ** ግ 1. በደንብ የማያይ ሆነ+

ተጨናቆረ፥ ተጭፈነፈነ:: 2. በጭስ ታፈነ፥ ታወከ::

**አጨናበሰ** ግ ማየት አወከ፥ አስቸገረ(አይንን)::

**ጨነገዘ** ግ ቆረጠ፥ ቀረደደ፥ አጨደ::

**ጨነገፈ** ግ 1. ፅንሱ ከመወለጃ ጊዜው ቀደም ብሎ ህይወት አልባ ሆኖ ወጣ:: 2. (የተተኮሰ ጥይት) ተበላሸ፥ ከሸፈ፥...:: 3. የታለመ፥ የታቀደው ጉዳይ ሳይሳካ ቀረ፥ ተጓጎለ፥ ተሰናከለ::

**ጨነገፈች** ግ አስወረደች፤ ቀኑ ሳይደርስ ህይወት የሌለው ፅንስ ከማህፀኗ ወጣ::

**ጭንጋፍ** ቅ (ስድብ) 1. ያለ ቀኑ የተወለደ:: 2. ጨባጣ፥ ድውይ፥ኮስማና:: ስ 3. ሞቶ የወጣ ፅንስ፤ ሽል::

**ተጨናገፈ** ግ ተጓጎለ፥ ከሸፈ፥ ተሰናከለ (የታቀደ፥ የተጀመረ ስራ ወይም ሌላ ነገር)::

**አጨናገፈ** ግ አስተጓጎለ፥ አከሸፈ፥ አሰናከለ፥ አደናቀፈ::

**አስጨነገፈ** ግ ፅንሱ ህይወት አልባ ወይም ውርጃ ሆኖ እንዲወጣ አደረገ (በሽታ ወይም ሌላ ችግር)::

***ጨነጎለ**

**ጨንጓላ** ቅ የተሰናከለ፥ አጓጉል የቀረ፥ ለውጤት ያልበቃ::

**ተጨናጎለ** ግ ተጓጎለ፥ ተሰናከለ፥ ለውጤት ሳይበቃ ቀረ::

**አጨናጎለ** ግ አሰናከለ፥ አጓጉል አደረገ፥ ያለውጤት አስቀረ::

***ጨነፈረ**

**አጨናፈረ** ግ መታ፤ ክፉኛ አሳመመ:: *ምቾ ሳጨናፍሮ ማለው::*

**ጨንቋራ** "ጨነቆረ" ስር ተመ.

**ጨንባሳ** "*ጨነበሰ" ስር ተመ.

**ጨንገር** ስ 1. ልምጭ፥ አርጩሜ፥ ለበቅ:: 2. አገዳው ቀጥ ብሎ የሚወጣ የጤፍ አይነት::

**ጨንጓላ** "*ጨነጎለ" ስር ተመ.

**ጨከነ** ግ 1. ክፉ ሆነ፤ ከርህራሄ፥ ከሃዘኔታ ራቀ:: 2. ቻለ፥ ታገሰ፥ በረታ፥ ደፈረ:: 3. ቆረጠ፥ ሳያመነታ ቀረ:: *ጨክና ሄደ::*

**ጨካኝ** ቅ ርህራሄ ወይም ሃዘኔታ የሌለው::

**ጭካኔ** ስ 1. ክፋት፤ ርህራሄ፥ ሃዘኔታ የሌለበት ስሜት:: 2. ብርታት፥ ድፍረት፥ ትእግስት::

**ጨከከ** ግ አረጀ፥ ጨረጨሰ (ለሰው)::

**ጨከከች** ግ ቁፍ፥ ጭር አለች:: *ዶሮዋ ሃያ ሳምስት እንቁላል ከወለደች በሂላ ጨከከች::*

**ጨካካ** ቅ 1. ያረጀ፥ የጨረጨሰ (ሰው):: 2. ቁፍ፥ ጭር ያለች (ዶሮ)::

**ጨካኝ** "ጨከነ" ስር ተመ.

**ጨካካ** "ጨከከ" ስር ተመ.

***ጨወተ**

**ጨዋታ(ጫወታ)** ስ 1. ንግግር፥ ውይይት:: 2. ልፊያ፥ ድሪያ፥ ቀልድ:: 3. የሚያስቅ፥ የሚያዝናና ወሬ ወይም ንግግር:: 4. ውድድር ወይም ፉክክር ያለበትና የሌለበት የቤትና የውጪ ስፖርት፥ መዝናኛ፥ ሌላም አይነት እንቅስቃሴ:: 5. ዘፈን፥ ዳንስ፥ ውዝዋዜ፥...::

**ጨዋታ ፈረሰ** ጨዋታው አበቃ፥አቆመ::*ጨዋታ ፈረሰ ዳቦ ተቆረሰ::*

**ከጨዋታ ውጭ** (ስፖ.) በእግር ኳስ ጨዋታ ላይ ከሚፈፀሙና ቅጣት ከሚያስጡ ስህተቶች አንዱ::

**የጨዋታ** የቀልድ፥ የምር ያልሆነ::

**ጭውውት** ስ ወሬ፤ የርስ በርስ ውይይት ወይም ንግግር::

**ተጫወተ** ግ 1. ተነጋገረ፥ ተወያየ:: 2. ተላፋ፥ ተቃለደ:: 3. የጨዋታ ወይም የውድድር እንቅስቃሴ አደረገ:: 4. ዘፈነ፥ ጨፈረ::

**ተጫወተበት** 1.ጉድ ሰራው፥ ያላሰበውን ነገር ፈፀመበት:: 2 . ቀለደበት፥ አሾፈበት:: 3. አላግባብ ተጠቀመ::*ገንዘቡን ተጫወተበት::*

**መጫወቻ** ስ 1. እንደ ኳስና አሻንጉሊት ያለ ለጨዋታ የሚያገለግል እቃ:: 2. መቀለጃ፥ ማሾፊያ:: *ሳንበሳ ሲያረጅ የዝንብ መጫወቻ ይሆናል::* 3. እንደ ክራር፥ ማሲንቆ፥ ዳማ፥ ካርታ የመሳሰሉ እቃዎች ወይም መሳሪያዎች::

**ተጫዋች** ቅ 1. ቀልደኛ፥ ጨዋታ አዋቂ:: 2. በእግር ኳስ፥ በመረብ ኳስ ወይም በሌላ አይነት ጨዋታ የሚሳተፍ::

**አጫወተ** ግ 1. አነጋገረ፥ አወያየ::*እንግዳውን ሳጫውተው::* 2. አባበለ፥ እንዳያለቅስ አደረገ (ህፃንን) :: 3. (ስፖ.) በዳኝነት መራ:: *እግር ኳስ ያጫውት የነበረው ዳኛ ታመመ::* 4. በጨዋታ እንዲሳተፍ አደረገ፥ ፈቀደ፥ አስገባ:: *ኳስ የሚጫወቱት ልጆች ሳጫውቱኝ ብላቸው እንቢ ሳሉኝ::*

**ማጫወቻ** ስ ልጅ እንዳያለቅስ ማባበያ ወይም ማታለያ የሚሆን ልዩ ልዩ እቃ::

**አጫዋች** ስ 1. የሚያነጋግር፥ የሚያወያይ፤ የሚያዝናና ቀልድ አዋቂ ሰው:: 2. (ስፖ.) የእግር ኳስ ወይም የሌላ ስፖርታዊ ውድድር ዳኛ::

**ጨዋ** ስ 1. በግብሩ ወይም በጠባዩ ጥሩ ስነ ምግባር ያለው፥ ከአፀያፊ ተግባር የራቀ(ሰው):: 2. ያልተማረ፥ ማይም::

**ጨዋታ** "*ጨወተ" ስር ተመ.

**ጨው** ስ ምግብ ጥሩ ጣእም እንዲያገኝና ሳይበላሽ እንዲቆይ ለማድረግ የሚያገለግልና ከመሬት ወይም ከውሃ የሚገኝ ነጭ ማእድን ፣ አሸቦ ::

**ጨው ሆነ** 1. ተወደደ:: 2. ጟጟ::

**ጨው መሰለ** ነጫጭባ ሆነ::

**ጨው ጨው አለ** የጨው ወይም የመኮምጠጥ ጣእም ሰጠ::

**ጨደደ** ግ 1. ቀደደ፥ ሰነጠቀ:: 2. ከበበ::

**ጨገሬታ(ጭገሬታ)** ስ ዱካ፥ ደብዛ፥ ምልክት:: *የሊታው ጨገሬታ ጠፍቷል::*

**ጨገገ** ግ 1. ጨለመ፥ ጭጋግ ሆነ:: 2. ከበደ፥ ጨፈገገ::

**ጭጋግ** ስ አቧራ የተሸከመ ወይም ጉም የሚመስል አየር::

**ጭጋግ ፊት** የከፋው የሚመስል (ሰው)::

**አጨገገ** ግ አጨፈገገ፥ አከፋ(ፊትን)::

**ጨጎረ** ግ 1. ፀጉር አወጣ ወይም አበቀለ(ሰውነት):: 2. አረም አበቀለ (መሬት)::

**ጭገር** ስ በሰዎች ብብትና አባለ ዘር አካባቢ የሚበቅል ፀጉር፤ ጭጉኝ::

**ጭገሩ ቆመ** ነገር ነገር አለው::

**ጭገራም** ቅ ብዙ ፀጉር ያለው::

**አጨጎረ (አጨገረ)** ግ 1. ሰውነቱ ፀጉር አወጣ ወይም አበቀለ:: 2. አረም አበቀለ::

**ጨጓራ** ስ በሰውና በእንስሳት ሆድ የሚገኝ፥ ለምግብ መፍጫነት የሚያገለግል እንደ ከረጢት ያለ አካል::

**የጨጓራ በሽታ** ስ በጨጓራ ውስጠኛ አካል ላይ የሚሰማ ህመም::

**ጨጓራ ፊት** ቅ 1.በኩፍኝ ወይም በፈንጣጣ ምክንያት ፊቱ የተበላሸና ጠቃጠቆ ያለበት:: 2. ጭፍግግ ያለ፥ የተከፋ የሚመስል::

**ጨጨብሳ** ስ ተሰባብሮ በቅቤ የታሸ ቂጣ::

**ጨጬ(ጬጬ)** ስ በወይና ደጋ የሚበቅልና ሲነድ እየተንጣጣ የሚፈናጠር የቁጥቋጦ አይነት ::

**ጨፈለቀ** ግ 1. ረገጠ፥ ዳጠ፥ ደፈጠጠ:: 2. ለየብቻ የነበረውን አንድ ላይ አደረገ፥ አቀላቀለ::*ወረቀቼን ሳስጨፍልቁ ለአንገቱ ሃብል ሳሰራሁ::* 3. ገመሰ፥ ተረተረ፥ ሰነጠቀ ወይም የመጀመሪያውን እርሻ አረሰ ::

**ጭፍልቅ** ቅ የመጀመሪያ እርሻ::

**ተጨፈለቀ** ግ 1. ለየብቻ የነበረው አንድ ላይ ተደረገ፥ ተቀላቀለ፥ ተዋሃደ:: 2. ተገመሰ፥ ተሰነጠቀ፥ የመጀመሪያው እርሻ ተከናወነ::

**ጨፈረ** ግ 1. በአመት በአል፥ በሰርግ፥ በልዩ ልዩ ደስታ ቀን፥... እየዘፈነ ዘለለ፥ ባአንገት ወረደ፥ ተወዘወዘ:: 2. (ዘይ.) በረቀ፥ ተደሰተ:: 3. (ዘይ.) በንዴት ወይም በቁጣ ብዙ ተናገረ::

**ጭፈራ** ስ ዝላይ፥ ዳንኪራ፥ ውዝዋዜ (የደስታ፥ የፈንጠዝያ)::

**ጭፋሮ** ዝ.ከ.::

**ተጨፈረ** ግ ጭፈራ ተደረገ::

**ተጫፈረ** ግ ተጣመረ፥ በአጫፋሬ ምእላድ ተያያዘ::

**አጫፈረ** ግ (ሰዋ.) አገናኘ፥ አጣመረ(ለምሳሌ ወንድሙና እህቱ ነገ ይመጣሉ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ "ና" አጫፋሪ ነው፤ ወይም ወንድሙ፥ እህቱ፥ አክስቱም ነገ ይመጣሉ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ "ም" አጫፋሪ ነው)::

**አጫፋሪ** ቅ 1. አበር፥ ግበረ አበር፥ አብሮ የሚሄድ፥ደጋፊ:: ስ 2. አያያዥ ወይም አጣማሪ ምእላድ::

**አስጨፈረ** ግ 1. እንዲዘፈን፥ እንዲጨፈር አደረገ:: 2. አስደሰተ:: 3. አናደደ፥ አበሳጨ፥ አስቆጣ::

***ጨፈረረ**

**ጨፍራራ (ጨፈረር)** ቅ በትጡ ያልተበጠረ (ፀጉር)::

**ጭፍርር አለ** ግ 1. በጣም ተንጨፈረረ፥ ቆመ(ፀጉር):: 2. ደረቀ (እፅዋት):: 3. (ዘይ.) ሞተ፥ ተፈነቸረ::

**ተንጨፈረረ** ግ 1. ተንጨበረረ (ፀጉር::) 2. ዛፍ ከድርቅ የተነሳ ቅጠሉቹን አራግፎ እንጨቱ ብቻ ቀረ:: 3. (ዘይ.) ሞተ::

**አንጨፈረረ** ግ 1. ፀጉር ከተገቢው በላይ በማደጉ ወይም በወግ ባለመያዙና ባለመበጠሩ ደርቆና ቀጥ ብሎ እንዲቆም ወይም ደግሞ ስርአት ባጣ መልኩ እንዲመሰቃቀልና እንዲንጨበረር አደረገ 2. ወደ ላይ አቆመ፥ ዘረጋ::*እጁን ሳንጨፍሮ ጌታዬ ጌታዬ እያለ ይግጠን ነበር::*

**ጨፈቀ** ግ 1. ለሰቀ፥ ለጥ ቀጥ አደረገ(ጨፈቃ ላይ ከባድ ነገር በማስቀመጥ፥ በመጫን፥በመርገጥ):: 2. መታ፥ ደበደበ:: 3. አጠጋጋ፥ ጠቀጠቀ::

**ጨፈቃ** ስ ትንንሽ ቅርንጫፍ ያለው ቀጫጭን እንጨት (ለቤት ግድግዳ ለአጥር፥... ስራ የሚያገለግል)::

**ተጨፈቀ** ግ በጨፈቃው ላይ ከባድ ነገር ተጭኖበት ልሰቅ እንዲል ተደረገ::

**ጨፈነ** ግ 1. አይኑን ከደነ፥ ገጠመ:: 2. ደበዘዘ፥ ብርሃን ጠፋ (በጉምና በዝናብ ምክንያት)::

**ጨፋና** ቅ አይኑ በደንብ የማይገለጥ ወይም የማያይ (ሰው)::

**ጭፍን** ቅ 1. የታወረ ወይም የማያይ (አይን):: 2. ግልፅ ያልሆነ:: 3. የማያመዛዝን ወይም የማያስተውል:: 4. በቂ ምክንያት የሌለው ወይም ያልታሰበበት::*ጭፍን የአሰራት እርምጃ::*

**በጭፍን** በመላ፥ ሳይመራመሩ፤ በድፍረት።

**ጭፍንፍን** ቅ ጨለማ የሆነ።

**ተጨፈነ** ግ ተገጠመ፥ ተከደነ፥ ተሸፈነ(አይን)።

**ተጭፈነፈነ** ግ 1.አየሩ በጉም፥ በጭጋግ ተሸፈነ፥ ጨለማ ሆነ። 2. ተድበሰበሰ፥ ግልፅ ሳይሆን ቀረ።

**ጨፈገገ** ግ 1. ከበደ፥ ጠቆረ (የአየር ሁኔታ)። 2. (ዘይ.) ፊቱን አጠቆረ፥ አጨማደደ።

**ጨፍጋጋ** ቅ 1. የጠቆረ፥ የከበደ(የአየር ሁኔታ)። 2. (ዘይ.) የማይጠዳው፥ ፊቱ የከበደ፥ የተከፋ የሚመስል።

**ጭፍግግ** ዝ.ከ. ።

**ጭፍግግ አለ** ግ ጠቆረ፥ ከበደ (አየሩ)።

**ጭፍግግ አደረገ** ግ አጨማደደ፥ አኮሳተረ(ፊቱን)።

**ጨፈጨፈ**[1] ግ 1. ቁጥቋጦን፥ ቅጠላቅጠልን፥... በስለት ወይም በመጥረቢያ፥... መለመለ፥ መነጠረ። 2. በዱላ፥ በመጥረቢያ፥...መታ፥ ደበደበ፥ ከተከተ። 3. በጣም ሰደበ፥ ዘለፈ። 4. በብዛት ገደለ፥ ፈጀ፥ ጨረሰ።

**ጨፍጫፊ** ቅ ጨካኝ፥ አረመኔ፥ ህዝብን የሚፈጅ።

**ጭፍጨፋ** ስ 1. የጅምላ ፍጅት፥ ግድያ። 2. እፅዋትን የመቁረጥና የማጥፋት ድርጊት።

**ጭፍጫፊ** ስ 1. ቁርጥራጭ፤ ትርፍራፊ (የእንጨት፥ የነገር)።2. ከነገሩ ጋር የተያያዘ ነገር ግን እንደ ዋና ፍሬ ነገር የማይወሰድ ነጥብ ወይም ሃሳብ።

**ተጨፈጨፈ** ግ 1. ተመነጠረ(ዛፍ፥ሳር፥ ቅጠል፥...)። 2 በብዛት ተገደለ (ሰው)። 3. (ዘይ.) ተሰደበ፥ ተዘለፈ።

**ጨፈጨፈ**[2] ግ አጠበ (ልብስን)።

**ጨፈጨፍ** ስ እግር የሚቆራርጥና የሚሰነጣጥቅ የክረምት ጭቃና ውሃ።

**ተንጨፈጨፈ** ግ 1. ተንቸረፈፈ፥ ወዛ። *ፊቱ ወዝ ተንጨፈጨፈ።* 2. ታጠበ፥ ተለቀለቀ (ልብስ)።

**አንጨፈጨፈ** ግ 1. አጠበ፥ አፀዳ፥ አለቀለቀ (ልብስን) 2. (ዘይ.) ሰደበ። *በስድብ አንጨፈጨፈው።*

**እንጭፍጫፊ** ስ የልብስ እጣቢ።

**ጨፋና** "ጨፈነ" ስር ተመ.

**ጨፌ** ስ 1. ለምለም ሳር የሚበቅልበት ውሃማ መሬት። 2. ውሃ ባለበት መሬት ላይና በወንዝ ዳር የሚበቅል ረጃጅም የሆነ ለምለም ሳር።

**ጨፍራራ** "*ጨፈረረ" ስር ተመ.

**ጨፍጋጋ** "ጨፈገገ" ስር ተመ.

**ጨፍጫፊ** "ጨፈጨፈ[1]" ስር ተመ.

**ጩ** የ"ጨ" ፊደል ካእብ ዘር።

**ጩሀት** "ጮሀ" ስር ተመ.

**ጩልፋት** "ጨለፈ" ስር"ጭሉፋት"ን ተመ.

**ጩልጩል**

**ጩልጩሌ** ቅ አይነ ትንንሽ።


**ጩልጩል አለ** ግ ክፍት ክድን አለ (ትንሽ አይን)።

**ጩርር**

**ጩርር አለ** ግ 1. ሆድ በህመም ወይም በመታወክ ምክንያት ጮሀ። 2. ውሃ ሲንቆረቆር የሚሰጠውን አይነት ድምፅ ሰጠ ወይም አሰማ።

**ጩቅ** ቅ ስስታም፥ ገብጋባ።

**ጩቤ** ስ እንደ ቢላዋ ያለ ሆኖ ከአንድ ወይም ከሁለት በኩል ስለት ያለውና በወገብ ላይ የሚታጠቁት የጦር መሳሪያ።



ጩቤ

**ጩጬ** ስ 1 የወፍ አይነት። 2 (ዘይ.) በጣም ትንሽ ልጅ (ተራ. አነ.)።

**ጪ** የ "ጨ" ፊደል ሳልስ ዘር።

**ጪስኛ** "ጨሰ" ስር ተመ.


**ጪስ** ዝ.ከ

**ጫ**[1] የ"ጨ" ፊደል ራብእ ዘር።

**ጫ**[2]

**ጫ አለ** ግ እረጭ፥ ፀጥ አለ።

**ጫማ** ስ 1. ከቁርጭምጭሚት በታች ከተረከዝ እስከ ጣት ድረስ ያለውና መሬት መርገጫ የሆነው የሰውነት ክፍል። 2. ከቆዳ ወይም ከፕላስቲክ ወይም ከሸራ የተሰራ በእግር የሚጠለቅ የእግር መርገጫ፤ መጫሚያ። 3. የቁመት፥ የከፍታ፥ የርቀት መጠን መለኪያ (አንድ ጫማ መጠኑ 0.305 ሜትር ነው)።




ጫማ

**ጫማ ላሰ/ሳመ** ተለማመጠ።

**ጫማ አደረገ** ጫማን በእግሩ አጠለቀ።

**ጫማውን ጠረሰ** አንድን ጉዳይ ለመፈፀም፥... ያለመሰልቸት ደከመ፥ ተመላለሰ።

**የጫማ ማሰሪያ** ስ ጫማ ከእግር ላይ እንዳይወልቅ የሚታሰርበት ወፈር ያለ ክር፤ ሲር።

**የጫማ ማንኪያ** ስ ጫማን ለማጥለቅ የሚረዳ ከቀንድ ወይም ከፕላስቲክ፥... የሚሰራ እቃ።

**የጫማ ምላስ** ስ ፊት ለፊት በጫማ ክር ማሰሪያዎች መካከል ያለውን ክፍት ቦታ የሚሸፍን ስስ ቆዳ።

**የጫማ ቀለም** ስ ቆዳ ነክ የሆነ ጫማን ለማለስለስና ለማሳመር የሚያገለግል ቅባትነት ያለው ቀለም።

**የጫማ ቡርሽ** ስ ጫማን ቀለም ለመቀባትና ለመወልወል የሚያገለግል ቡርሽ።

**ጫማ ሰፊ** ስ ጫማን በልክ ወይም በእግር መጠን (ቁጥር) የሚሰፋ ወይም የተቀደደውን የሚጠግን ባለሙያ።

**ጫማ ጠራጊ** ስ ጫማን በመወልወልና በማሳመር በሚያገኘው ገቢ የሚተዳደር ሰራተኛ፤ ሊስትሮም ይባላል።

**ተጫማ** ግ ጫማ አደረገ።

**መጫሚያ** የ"ጫማ"ን 1ኛና 2ኛ ፍቺ ተመ.

**ጫረ** ግ 1. እሳትን ከምድጃ ውስጥ በገል ወይም በሌላ ነገር ዝቆ አወጣ። 2. የክብሪትን እንጨት ራስና በክብሪት ቤቱ ጎን ላይ ያለውን ሻካራ ክፍል በማፋተግ እሳት አወጣ። 3. ጋሬጣ፥ እንጨት፥ ምላጭ፥... የሰውነትን ክፍል ወይም የሌላን ነገር አካል በመጠኑ ሰነጠቀ ፤ ቧጠረ፥ ፋቀ። 4. መሬትን በትንሹ ቆፈረ። *ዶሮ እየጫረች ትበላለች።* 5. (የግ.አነ.) ፃፈ። 6 (ዘይ.) ጀመረ፥ ተነኮሰ (ነገርን፥ ጠብን)።

**መጫሪያ** ስ 1. የእሳት መውሰጃ ገል። 2. ቆሻሻ ለመሰብሰብ የሚያገለግል የተቆለመሙ ጥርሶችና ረጅም እጀታ ያለው የእርሻ መሳሪያ።



መጫሪያ

**ጭረት** ስ እንደ ሰረዝ ያለ ምልክት። 2. ከሆሄድ የዜማ ምልክቶች አንዱ፤ ምልክቱም (\) ነው ።

**ተጫረ** ግ አንድ አካል ወይም የሰውነት ክፍል ተቧጠረ ፥ ተሸነተረ፥ ተፋቀ (በጋሬጣ ፥ በእንጨት፥...)።

**ተጫጫረ** ግ 1. ብዙ ቦታ ላይ ተቧጠረ፥ ተሸነታተረ፥ ተፋፋቀ። 2. አንዱ ከሌላው ቤት እሳት ወሰደ።

**አጫረ** ግ ተነኮሰ፥ ጀመረ (ነገርን፥ ጠብን)።

**ጫረታ** "*ጨረተ" ስር "ጨረታ"ን ተመ.

**ጫቅማ** ስ ጉሉ።

**ጫተረ** ግ ለፋ፥ ደከመ (በስራ)።

**ጫት** ስ ለጋ ቅጠሉ የሚታኘክና ሱስ የሚያስይዝ የእፅዋት አይነት።

**ጫት ቃመ** ግ ጫቱን እየቀጠፈና እየቀነጠሰ አኘከ።

**ጫት ቃሚ** ቅ ጫትን አዘውትሮ የሚያኝክ (ሰው)።

**ጫነ** ግ 1. እቃን፥ ሸቀጥን፥... በመኪና፥ በከብት፥ በመርከብ፥... ላይ አኖረ፥ አደረገ፤ አሸከመ። 2. ከአንድ ሃገር ወደ ሌላ ወሰደ፥ አጓጓዘ (እቃን)። 3.አሳፈረ። *አስር ሰው የጫነ መኪና።* 4. አንዱን በሌላው ላይ ደረበ፥ አኖረ፥ አሳረፈ፥ አስቀመጠ(ከላይ)። *ድንጋይ ጫነበት።*

**መጫኛ** ስ በከብት ጀርባ ላይ ጭነትን ለማሰር የሚያገለግል ጠፍር።

**መጫኛ ነካሽ** ስ (የን.አነ.) ሸቀጡን በአህያና በበቅሎ እያጓጓዘ የሚሸጥ ነጋዴ፤ ጠፍር ነካሽም ይባላል።

**ጫና** ስ 1. ከባድ ሸክም። 2. ከአቅም በላይ የሆነ ስራ ወይም ሃላፊነት። 3. ጭቆና።

**ጭነት** ስ ሸክም፤ በአጋሰስ፥ በአህያ፥ በመኪና፥... የተጫነ እቃ።

**የጭነቱ ልክ** ስ አንድ ተሽከርካሪ ሊይዝ የሚችለውና የተፈቀደለት የእቃና የሰው ብዛት ወይም መጠን።

**የጭነት መኪና** ስ የተለያዩ እቃዎችን የሚሸከም፥ የሚያጓጉዝ (ብዙውን ጊዜ ከባድ መኪና) (ስእሉን ሎጓጓዥ ስር ተመ.)።

**የጭነት ከብት** ስ ለጭነት አገልግሎት ማለትም ለሸክም ብቻ የሚውል ከብት፤ አጋሰስ።

**ጫን** ስ አስር ማድጋ ያህል የሚይዝ የስፍር መለኪያ (አንድ ጫን በቁና ወይም በማድጋ የሚይዘው መጠን እንደየአካባቢው ይለያያል)።

**ጫን ጫን ተነፈሰ** ግ በጣም ወይም በሃይል ተነፈሰ (ከድካም፥ከበሽታ፥... የተነሳ)።

**ጫኝ** ስ ሸቀጥን ከቦታ ቦታ በአጋሰስ ወይም በአህያ የሚያጓጉዝ ሰው።

**ጫን አለ** ግ 1. ተጫነ፥ አጠበቀ። 2. በደለ። 3. ጠቆን አደረገ።

**ተጫነ** ግ 1. እቃው፥ ሸቀጡ፥... በመኪና፥ በእንስሳ ጀርባ፥ በመርከብ፥... ላይ ተደረገ፥ ለመጓጓዝ ተዘጋጀ ወይም ጉዞ ጀመረ። 2. ነፃነት ነሳ። 3. አጣበቀ፥ ደፈጠጠ፥ ገፋ። 4. ተፅእኖ

ወይም ግፊት አደረገ።

**ተጫጫነ** ግ ቀፈፈ፥ ከበደ፥ ሰውነት ድክም አለ።

**ጫንቃ** ስ 1. በትከሻና በትከሻ፥ በአንገትና በጀርባ መካከል ያለው የሰውነት ክፍል፤ ደንደስ። 2. ትከሻ።

**በ___ ጨንቃ** በ___ ድጋፍ፥ እርዳታ። *በሰው ጫንቃ ይኖራል።*

**ጫኖ** ስ ከደረቱ በላይ ጥቁር ሆኖ ከጆሮዎቹ አካባቢ ግራጫ መልክ ያለው፥ በሃይቆችና በትናንሽ ወንዞች አካባቢ የሚገኝ፥ በመጠን ከዳክዬ የሚበልጥ የአሞራ አይነት።

**ጫኝ** "ጫነ" ስር ተመ.

**ጫካ** ስ በብዛት ችፍግ ብሎ የበቀለ ልዩ ልዩ ዛፍ፥ ቁጥቋጦ የሚገኝበት ቦታ፤ ደን።

**ጫወታ** "*ጨወተ" ስር "ጨዋታ" ን ተመ.

**ጫጉላ [ቤት]** ስ ሙሽራና ሙሽሪት ለተወሰነ ጊዜ የሚሞሸሩበት ቤት።

**ጫጨ(ጫጫ)** ግ ኮሰሰ፥ ከሳ፥ ቀጠነ፥ ሰለለ።

**ጫጩት** ስ 1. ከእንቁላል የወጣ ወይም የተፈለፈለና ገና ያላደገ የዶሮ፥ የወፍ፥ የአሞራ ልጅ። ቅ 2. ትንሽ (ልጅ)።

***ጫጫ**

**ጫጫታ** ስ ከፍተኛ ድምፅ የሚሰማበት የብዙ ሰው ንግግር፥ ሁካታ።

**ተንጫጫ** ግ 1. ብዙ ሰው ተሰብስቦ ከፍ ባለ ድምፅ እርስ በርሱ ተነጋገረ፥ አወራ። 2. በብዛት ሆኖ የጩሀት ድምፅ አሰማ (ሰው፥ወፍ፥...)። 3. አለቀሰ (ብዙ ሰው አንድ ላይ)።

**አንጫጫ** ግ እንዲንጫጫ አደረገ፥ አስጮሀ (ልጆችን፥ ...)።

**ጫጫ** "ጫጨ"ን ተመ

**ጫጫረ** "ጫረ" ስር ተመ.

**ጫጫታ** "*ጫጫ" ስር ተመ.

**ጫፍ** ስ 1. የአንድ ነገር የላይኛው ወይም የታችኛው የመጨረሻው ክፍል። 2. መሃል ያልሆነ፥ ዳር ወይም ጠርዝ። 3. መጨረሻ። *ጉዳዩን ከጫፍ ላድርሰታል።* 4. ከዋናው ጉዳይ ወይም አካል ጥቂት ብቻ፥ ትንሽ ነገር፥ ዋናውን ያልሆነ፥ ዝርዝሩን ያልያዘ። *ጫፍ ይዘህ ብዙ አታውራ።*

**ጫፌን ንካኝ** እስቲ አጠገቤ ደርሰህ ትንሽ ምታኝ የማለትና የማስፈራራት አነጋገር።

**ጫፍ ጫፉን** በዝርዝር ሳይሆን አንዳንዱን። *የዚህን ወሬ ጫፍ ጫፉን ሰምቼዋለሁ።*

**ጬ** የ "ጨ" ፊደል ሃምስ ዘር።

**ጭ** የ "ጨ" ፊደል ሳድስ ዘር።

**ጭለማ** "ጨለመ" ስር "ጨለማ" ን ተመ.

**ጭሉፋት** "ጨለፈ" ስር ተመ.

**ጭላሃ** ስ ትንሽ እንጎቻ።

**ጭላት** ስ ጭልፊት።

**ጭላዳ** ስ ተራራማና ድንጋያማ በሆኑ በኢትዮጵያ ደጋማ ቦታዎች የሚገኝ፥ በጠጉሩ ርዝመትና ለስላሳነት እንዲሁም በቀለሙ ቡናማነት ከሌ ሎቹ የዝንጀሮ ዝርያዎች በቀላሉ የሚለይ፥ ከመቀመጫው በተጨማሪ በደረቱና በአንገቱ ላይ መላጣ ያለው የዝንጀሮ አይነት (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

**ጭላጭ** "ጨለጠ" ስር ተመ.

**ጭል**

**ጭላንጭል** ስ 1. የግድግዳ፥ የመስኮት፥ የጣራ፥... ቀዳዳ (ብርሃን ዘልቆ የሚገባበት)። 2. መጠነኛ እይታ (የነገር፥ የተስፋ)። *የተስፋ ጭላንጭል።*

**ጭልታ** ስ የነገር፥ የሃሳብ ጭላንጭል።

**ጭል ጭል አለ** ግ 1. በትንሽ በትንሹ ታየ(መብራት)። *ኩራዟ ጭል ጭል ትላለች።* 2. በጥቂት በጥቂቱ ወረደ፥ ፈሰሰ(ውሃ)።

**ጭልል**

**ጭልል አለ (ጭል አለ)** ግ አንዳች አልባ ሆነ፥ ጭር አለ።

**ጭል [ል] ያለ ሜዳ** ለጥ ያለ ሜዳ።

**ጭልቃ** "*ጨለቀ" ስር ተመ.

**ጭልታ** "ጭል" ስር ተመ.

**ጭልጌ(ጭልጊ)** ስ ከወይፈን ቆዳ የሚዘጋጅ ስለቻ።

**ጭልፊት** ስ 1. በክረምት የማትታይ (ጫጩት፥ ስጋ፥.. የምትነጥቅ) የአሞራ አይነት (ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)። 2.(ዘይ.) ነጣቂ ሌባ፥ ሞጭላፋ።

**ጭልፋ** "ጨለፈ" ስር ተመ.

**ጭማሪ** "ጨመረ" ስር ተመ.

**ጭማቂ** "ጨመቀ" ስር ተመ.

**ጭም አለ** ግ ፀጥ፥ ጫ አለ።

**ጭምር** "ጨመረ" ስር ተመ.

**ጭምብል** ስ ከሹራብ ወይም ከጨርቅ ወይም ከእንጨት፥... በተለያየ ቅርፅ የሚሰራና አንድ ሰው ማንነቱ በተመልካች ተለይቶ እንዳይታወቅ ፊቱን የሚደብቅበት ወይም የሚከልልበት የፊት ገፅታ ሽፋን ወይም መሸፈኛ።

**ጭምት** "ጨመተ" ስር ተመ.

**ጭምጭማት** "ጨመጨመ" ስር ተመ.

**ጭምጭምታ** ስ በይፋ ያልወጣ ወይም

ያልተረጋገጠ ወሬ።

**ጭረት** ፡"ጫረ" ስር ተመ.

**ጭሩ** ስ ላባዎቹ ጥቁር ሆነው ሌላው አካሉ አሸዋማ መልክ ያለው ድንቢጥን የሚያክል የወፍ ዘር (ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

**ጭሪ** ስ የከብቶችን ቆዳ በምንቃሯ እየወጋች የምታቆስልና ደም የምትመጥ አፈቀይ የወፍ አይነት፤ አረጭ (ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

**ጭራ** ስ 1. ጅራት። 2. የአንድ ነገር የኋለኛ አካል ክፍል። 3. ከፈረስ ወይም ከበሬ ጅራት ወይም ከቃጫ፥... የሚሰራ የዝንብ መከላከያ። 4. ተከታይ፤ ከኋላ ከኋላ ሉክ ሉክ የሚል። 5. በአስተሳሰብ፥ በውድድር፥... ወደኋላ የቀረ። 6. የአንድ ነገር ፍንጭ፥ ምልክት።



ጭራ 3ኛ ፍቺ

**ጭራ ቆናኝ** የዝንብ መከላከያ ጭራ እየነነነና እያስጌጠ የሚሰራ ባለሙያ።

**ጭራ አወጣ/ አበቀለ** በጣም ተናደደ።

**ጭራው አይያዝም** አንድ ቦታ ላይ አይቀመጥም፥ ሲፈለግ አይገኝም (ሰው)።

**ጭራውን ቆላ** 1. ጭራውን አወዛወዘ፥ ነሰነሰ (ፈረስ፥ ውሻ፥...)። 2. ተፍነከነከ፥ በጣም ተደሰተ። 3. ተለማመጠ።

**ጭራውን ይዞ ተከራከረ** የገዛውን ከብት ለእኔ ነው ባይ ሳይለቅ ወይም ሳይሰጥ በእጁ እንዳደረገ ተከራከረ።

**ጭራው ጮሌ** በጣም ብልጥ የሆነ፥ ቀልጣፋ።

**ጭራሮ** ስ 1. ለማገዶ የሚያገለግል የደረቀ ቀጫጭን እንጨት ወይም የዛፍ ቅርንጫፍ። ቅ 2. ቀጭን (እግር)።

**ጭራሽ** "ጨረሰ" ስር ተመ.

**ጭራቅ** ስ 1. አራት አይና ነው ተብሎ የሚታሰብና ሰው ይበላል የሚባል የሰው ጅብ። ቅ 2. አረመኔ፥ ጨካኝ፥ ርህራሄ የሌለው።

**ጭራንፎ** ስ የዛፍ ቅርንጫፍ፤ ዛፍ ላይ እንዳለ የደረቀ ጭራሮ።

**ጭሬ** ስ ረዥም ጦር።

**ጭር**

**ጭር አለ** ግ 1. ፀጥ፥ ረጭ አለ፥ ድምፅ ጠፋ። 2. በአካባቢው የሚንቀሳቀስ ሰው ጠፋ፥ ባዶ ሆነ። 3. ሰውነቱ በድንጋጤ፥ በሀመም፥... የተነሳ ከሳ፥ ኮሰሰ። 4. የመጥረያ ደወል የሚያሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ።

**ጭር አለች** እንቁላል መጣል ተወች (ዶሮ)።

**ጭርቂያም** "*ጨረቀ" ስር ተመ.

**ጭርት** ስ በሰው አካል ላይ (ብዙውን ጊዜ አንገትና ፊት ላይ) የሚታይና እያሳከከ ስፋት የሚጨምር የቆዳ በሽታ።

**ጭርንቁስ** ስ ቡትቶ፥ የተጣጣፈ አሮጌ ጨርቅ፥

**ጭርንቁሳም** ቅ (ስድብ) ቡትቶ ለባሽ።

**ጭቁን** "ጨቆነ" ስር ተመ.

**ጭቁኝ** ስ መድሃኒትነት አለው የሚባልና ሽታው የማያስደስት (የሚያንገሸግሽ) የቅጠል አይነት።

**ጭቃ** "ጨቀየ" ስር ተመ.

**ጭቅቅት** ስ የሰውነት ቆሻሻ፥ እድፍ።

**ጭቅቅታም** ቅ (ስድብ) እድፋም፥ ቆሻሻ።

**ጭቅና** ስ፥ ከሽንጥ ጋር አብሮ የሚወጣና በጣም ለስላሳ የሆነ የብልት አይነት።

**ጭቅጭቀኛ** "ጨቀጨቀ[1] " ስር ተመ.

**ጭቅጭቅ** ዝ.ከ.

**ጭቆና** "ጨቆነ" ስር ተመ.

**ጭባ** ቅ (ስድብ) አጭርና ቀጭን የሆነ፥ ድውይ።

**ጭብጥ** "ጨበጠ" ስር ተመ.

**ጭብጥ** ዝ.ከ.

**ጭብጠ** ዝ.ከ.

**ጭብጨባ** "*ጨበጨበ" ስር ተመ.

**ጭቦ** ስ ግፍ፥ በደል፤ በሸር፥ በተንኮል፥ በሃሰት የተፈፀመ ነገር።

**ጭቦኛ** ቅ ግፈኛ፥ በደለኛ፤ በተንኮል፥ በሃሰት የሚሰራ።

**ጭነት** "ጫነ" ስር ተመ.

**ጭን** ስ ከጉልበት በላይ ከብሽሽት በታች ያለ የሰውነት ክፍል (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

**የጭን በቅሎ** ስ ባለቤቷ ብቻ የሚቀመጥባት በቅሎ።

**የጭን ገረድ** ስ በጥንት ዘመን በዘመቻ ጊዜ ከጌታዋ ጋር አብራ የምትሄድና የምትተኛ ሴት።

**የጭን ፈረስ** ስ ባለቤቱ ብቻ የሚቀመጠው ወይም የሚጋልበው ፈረስ።

**ጭንቀታም** "ጨነቀ" ስር ተመ.

**ጭንቀት** ዝ.ከ.

**ጭንቁላ** ስ ማሰሮ።

**ጭንቁር[1]** ስ በፊት ላይ (ብዙውን ጊዜም አፍንጫ ላይ) የሚወጣና አፍንጫን የሚያበላሽ ቁስል፤ ሻህኝ፤ ቁንጭር።

**ጭንቁር[2]** "ጨነቆረ" ስር ተመ.

**ጭንቁርቁር** ዝ.ከ.
**ጭንቅ "ጨነቀ"** ስር ተመ.
**ጭንቅላት** ስ 1 የራስ ቅል። 2 እውቀት፣ ማስተዋል፣ የማመዛዘን ችሎታ።
**ጭንቅላቱ ላሽቋል** እውቀቱ ወይም የማመዛዘን፣ የማስተዋል ችሎታው ቀድሞ ከነበረበት ደረጃ ቀንሷል።
**ጭንቅላት የለውም** አያመዛዝንም።
**ጭንቅላተ ቢስ** (ስድብ) ማመዛዘን የማይችል።
**ጭንቅላታም** ቅ (ስድብ) ትልቅ ጭንቅላት ያለው።
**ጭንቅሉ** ዝ.ከ.
**ጭንብስብስ "ጨነበሰ"** ስር ተመ
**ጭንጋፍ "ጨነገፈ"** ስር ተመ.
**ጭንጩ** ቅ ዘሩ ከሌላ ጋር ያልተደባለቀ ወይም ያልተዋሃደ። *ጭንጩ ለማሬ።*
**ጭንጫ** ስ 1. ድንጋያማ ወይም አለታማ መሬት። 2. በቀላሉ የማይገሰስ (የማይደፈር) የልጃገረድ ድንግልና።
**ጭካኔ "ጨከነ"** ስር ተመ.
**ጭኮ** ስ ከበሶ ዱቄት በቅቤ ታሽቶ የሚዘጋጅ ምግብ።
**ጭው**
**ጭው አለ** ግ 1. በጆሮ ውስጥ የጩሀት ድምፅ ተሰማ። 2. ከሳ፣ ገረጣ (የሰው ፊት)።
**ጭው ያለ ሜዳ** አቀበትና ቁልቁለት የሌለው ለጥ ያለ ሜዳ።
**ጭው ያለ በረሃ** ምንም ሰው የሌለበትና ድምፅ የማይሰማበት በረሃ።
**ጭው ጭው አለ** ጮሀ፣የጫጩት አይነት ድምፅ አሰማ።
**ጭውውት "*ጨወተ"** ስር ተመ.
**ጭዳ** ስ ለአምልኮ ባእድ የሚደረግ እርድ።
**ጭዳ አለ** ግ 1. ለአምልኮ ባእድ መስዋእት አቀረበ ወይም ደም አፈሰሰ። 2. ገደለ። *ተጠንቀቅ ጭዳ እንዳልልሀ።*
**ጭድ** ስ የጤፍ ገለባ።
**ጭገራም "ጨጎረ"** ስር ተመ.
**ጭገሬታ "ጨገሬታ"** ን ተመ.
**ጭገር "ጨጎረ"** ስር ተመ.
**ጭጉኝ** ስ ጭገር።
**ጭጋግ "ጨገገ"** ስር ተመ.
**ጭጎት** ስ በገጠር አካባቢ በጭቃ ወይም በግንብ ቤት ግድግዳ ላይ የሚሰራ የኩራዝና የአንዳንድ እቃ ማስቀመጫ በታ።
**ጭጎጎት** ስ ፍሬው ልብስ ላይ የሚከስከስና የሚጣበቅ የእፅዋት አይነት።
**ጭጎጎት ፊት** የማይጠዳው፣ ፊቱ የማይፈታ።
**ጭጫን** ስ ቁጫጭ።
**ጭጭ**
**ጭጭ አለ** ግ 1. ፀጥ፣ ረጭ፣ ዝም አለ፤ ሳይናገር ቀረ። 2. በድንገት ሞተ።
**ጭጭ እንዳትል** ድምፅ እንዳታሰማ ወይም እንዳትናገር።
**ጭጭ ምጭጭ የለም** ድምፅ ማሰማት ወይም መተንፈስ የለም።
**ጭፈራ "ጨፈረ"** ስር ተመ.
**ጭፋር** ስ .1 የቅንድብ ፀጉር። 2. የዘንባባ፣ የቴምር ወይም የሰሌን ቅጠል።
**ጭፋሮ "ጨፈረ"** ስር ተመ.
**ጭፍልቅ "ጨፈለቀ"** ስር ተመ.
**ጭፍን "ጨፈነ"** ስር ተመ.
**ጭፍንፍን** ዝ.ከ.
**ጭፍግግ "ጨፈገገ"** ስር ተመ.
**ጭፍጨፋ "ጨፈጨፈ"** ስር ተመ.
**ጭፍጫፊ** ዝ.ከ.
**ጮ** የ"ጨ" ፊደል ሳብእ ዘር።
**ጮሀ** ግ 1. ከፍ ያለ ድምፅ አሰማ ወይም ሰጠ። 2. ኡኡ፣ እሪ፣... አለ፣ የድረሱልኝ ጥሪ አሰማ። 3. ድምፅ አሰማ(ዶሮ፣ ውሻ፣ ጅብ፣...)። 4. አቤት አለ፤ አቤቱታ አቀረበ(ለዳኛ፣ ለሹም)። 5. ድምፅ አውጥቶ አለቀሰ። 6. ተቆጣ።
**ጮሀበት** ተቆጣው።
**ጯሂ** ቅ 1. ድምፁን ከፍ አድርጎ የሚናገር፣ ለፍላፊ። 2. (የጥንት አነጋገር) አቤቱታ አቅራቢ።
**ጩሀት** ስ 1. ከሰው፣ ከእንስሳ ወይም ከሌላ ነገር የሚወጣ ከፍተኛ ድምፅ። 2. ጫጫታ፣ ሁካታ።3. እሪታ፣ኡኡታ።
**ጩሀቴን ቀሙኝ** አቤቱታ ማቅረብ ወይም ብሶቱን ማሰማት፣ መክሰስ... የሚገባው ተበዳዩ እያለ፣ በደል አድራጊው (ፈፃሚው) በደል እንደደረሰበት ሆኖ ተናገረ፤ በተበዳዩ ወገን ላይ እሮሮ አሰማ ለማለት የሚነገር አባባል።
**ጮክ አለ** ግ ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ።
**ተጮሀ** ግ ኡኡ፣ እሪ፣... ተባለ፣ ተለቀሰ፣ ኡኡታ ተሰማ (በሃዘን፣ በድንጋጤ፣ እርዳታን በመሻት)።
**ተጯጯሀ** ግ 1. ሳይደማመጥ ሁሉም በየፊናው ተናገረ፣ ተንጫጫ። 2. ተላቀሰ።

**አጮሀ** ግ 1. ከፍ ያለ ድምፅ እንዲያሰማ አደረገ:: 2. መታ:: *በጥፊ አጮሀው::*
**አጯጯሀ** ግ ሽብር በመፍጠር እንዲጮሀ አደረገ፥ አንጯጯ::
**አስጮሀ** ግ እንዲጮሀ ወይም ጩሀት እንዲያሰማ አደረገ::
***ጮለ**
**አጮለ** ግ በጥፊ መታ፣ አጠናገረ::
**ጮሌ** ቅ ብልጥ::
**ጮመ** ግ በጣም ሰባ::
**ጮማ** ስ በጣም ስብ ወይም ነጭ የሆነ የከብት ስጋ::
**ጮረረ** ግ ወረደ፥ ተንቆረቆረ፥ፈሰሰ (ፈሳሽ)::
**መንጮርር** ስ ጣሪያ ላይ የሚሰራ የዝናብ ውሃ መውረጃ አሸንዳ::
**ጮራ** "*ጮረረ[2]" ስር ተመ.
**ጮርቃ** "ጨረቋ" ስር ተመ.
**ጮቄ** ስ በጣም ደጋ የሆነና ጨቀጨቅ ያለበት በታ::
**ጮቅ[1]** ስ የክረምት ጭቃ::
**ጮቅ[2]** ስ በእግር ጣቶች መሃል የሚወጣ ቁስል ወይም ስንጥቃት::
**ጮቤ** ስ ሁለት እግርን በአንድነት እያነሱ የራስን ቂጥ በመምታት የሚደረግ ዝላይ::
**ጮቤ መታ/ ረገጠ** በጣም ተደሰተ::
**ጮካ** ቅ ጮሌ፥ ብልጥ::
**ጮጮ[1]** ስ ከስንደዶ፥ ከአክርማ ወይም ከግራምጣ ተሰፍቶ ለወተት ማለቢያነት የሚያገለግል የቤት እቃ (ስእሉን የስፌት እቃ ስር ተመ.)::
**ጮጮ[2]** "ጨጮ"ን ተመ.
**ጯ** የ "ጨ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር::
**ጯሂ** "ጮሀ" ስር ተመ.

# ጸ

**ጸ** ከ"ጠ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

**ጹ** የ"ጸ" ፊደል ካእብ ዘር።

**ጺ** የ"ጸ" ፊደል ሳልስ ዘር።

**ጻ** የ "ጸ"ፊደል ራብእ ዘር።

**ጳጉሜን (ጳጉሜ፥ ጳጉሚት)** ስ በዘመነ ዮሃንስ፥ ማቴዎስና ማርቆስ አምስት አምስት ቀናት በዘመነ ሉቃስ ግን ስድስት ቀናት ያሉትና ከነሃሴ ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ አስራ ሶስተኛ ወር።

**ጳጳስ (ብ.ቁ. ጳጳሳት)** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ማእረጉ ከኤጲስቆጶስ በላይ ከሊቀጳጳስ በታች የሆነ መንፈሳዊ አባት።

**ጵጵስና** ስ የጵጵስና ማእረግ ወይም ስልጣን።

**አጳጳሰ** ግ የጵጵስና ማእረግ ወይም ስልጣን ሰጠ።

**ጼ** የ"ጸ"ፊደል ሃምስ ዘር።

**ጽ** የ"ጸ" ፊደል ሳድስ ዘር።

**ጾ** የ"ጸ" ፊደል ሳብእ ዘር።

# ፀ

**ፀ** ከ"ጸ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ) ።

**ፀሃይ** ስ 1. መሬትና ሌሎች ፕላኔቶች ዙሪያዋን የሚዞርዋት፥ ብርሃንና ሙቀት የምትሰጥ ኮከብ፤ ጀምበር። 2. ከፀሃይ የሚገኝ ሙቀት።

**ፀሃይ መታው /ከካው** 1. (ለሰው) የፀሃይ ሙቀት ጎዳው፥ አደከመው። 2. ፀሃይ አደረቀው፥ ሞቀው።

**ፀሃይ ወጣ** 1. የፀሃይ ብርሃን ታየ፥ ነጋ፥ ቀን ሆነ። 2. (ዘይ.) ችግር፥ ሃዘን፥... ተወገደ፥ ደስታ ሆነ።

**ፀሃይ ገባች /ጠለቀች** ጨለመ፥ መሸ።

**የፀሃይ ቆብ** ስ ለፀሃይና ለብርድ መከላከያ ሲባል የሚደረግ ቆብ።

**የፀሃይ ግርዶሽ** ስ የፀሃይ ብርሃን በከፊል ወይም በሙሉ በጨረቃ መከለል ወይም መጋረድ።

**ፀሃፊ "ፃፈ"** ስር ተመ.

**ፀለየ** ግ አምላክን ለመነ፥ ተማፀነ፥ ወይም አመሰገነ።

**ፀሎት** ስ ለአምላክ የሚቀርብ ልመና፥ምስጋና።

**ፀሎት አደረሰ** ፀሎት ፀለየ፥ ደገመ።

**ፀሎተ ሃሙስ** ስ ከፋሲካ እሁድ በፊት የሚገኘው ሃሙስ የሚጠራበት ስም።

**ፀሎተ ማእድ** ስ ከማእድ በፊትና በሂላ የሚፀለይ ፀሎት።

**ፀሎተ በረድ** ስ በረዶ እንዳይጥልና በሰብል ላይ ጉዳት እንዳያደርስ የሚፀለይ ፀሎት።

**ፀሎተኛ** ቅ ለፈጣሪው ዘወትር ፀሎት የሚያቀርብ፤ ሃይማኖተኛ።

***ፀረረ**

**ፀር(ጠር)** ስ ጠላት ወይም ተስማሚ ያልሆነ ወይም ተቃራኒ ነገር።

**ፀረ __ የ __** ጠላት ወይም ፀር ለማለት የሚያገለግል ከፊለ ቃል። *ፀረ ዲሞክራሲ /ፀረ ኣይሮፕላን* ።

**ተፃረረ** ግ ተቃወመ፥ተቃረነ፥ ተጣላ።

**ተፃራሪ** ቅ ተቃዋሚ፥ ተቃራኒ፥ ባላንጣ።

**ፀበል(ጠበል)** ስ 1. ህመምተኞች ፈውስ ለማግኘት የሚጠጡት ወይም የሚጠመቁበት የተፀለየበት ውሃ። 2. በተፈጥሮ ፈዋሽነት ያለውና ብዙውን ጊዜ በታቦት ስም የሚጠራ የምንጭ ውሃ። 3. ለክርስትና፥ ለዝክር፥ ለማህበር፥ ለተዝካር የተዘጋጀ ድግስ (ምግብ፥ መጠጥ)።

**ፀበል ቅመስ** (ለክርስትና፥ ለዝክር፥... የተዘጋጀውን) መጥተህ ተጋበዝ።

**ፀበል ፀዲቅ (ጠበል ጠዲቅ)** ስ ለክርስትና፥ ለዝክር፥... የተዘጋጀ ድግስ (ምግብና መጠጥ)።

**ፀበለተኛ (ጠበለተኛ)** ስ በህመም ምክንያት ፀበል በመጠጣትና በመጠመቅ ላይ ያለ ሰው።

***ፀበረቀ**

**ነፀብራቅ** ስ 1. ብልጭታ። 2. አንድን ሁኔታ፥ አስተሳሰብ የሚያመለክት ድርጊት ወይም ሃሳብ።

**ተንፀባረቀ** ግ 1. ብርሃን እንደመስታወትና ውሃ ባሉ አካላት ላይ ካረፈ በሂላ ተቀልብሶ በሌላ አካል ላይ ብልጭልጭታ አሳየ። 2 ተብለጨለጨ። 3. የራስ የሆነ ወይም ከሌላ ሰው የተወሰደ አንድ አይነት አስተሳሰብ በንግግር ወይም በድርጊት ላይ ታየ፥ ተከሰተ፥ ተገለጠ።

**አንፀባረቀ** ግ 1. አብረቀረቀ፥አብለጨለጨ። 2. አማረ፥ ተዋበ። 3. የራስ ወይም የሌላ ሰው የሆነን አንድ አስተሳሰብ በንግግር ወይም በድርጊት አሳየ፥ አስተጋባ፥ ግልፅ አደረገ።

**አንፀባራቂ** ቅ 1. የሚያብለጨልጭ። 2. የሚያምር፥ ውብ።

**ፀነሰ** ግ ወጠነ፡፡

**ፀነሰች** ግ በማህፀኗ ሽል ያዘች፥ አረገዘች።

**ፅንስ** ስ 1.ሽል። 2. ውጥን።

**ፅንሱ ወረደ** ጨነገፈ።

**ፅንስ ሃሳብ** ስ ስለአንድ ነገር በአእምሮ ውስጥ የተቀረፀ ግንዛቤ።

**ተፀነሰ** ግ 1. ተረገዘ፡2.ተወጠነ።

**ፀና** ግ 1. ረጋ፥ ቆመ። 2. ፀደቀ(ፍርድ፥ ውሳኔ)።

**ፅናት(ጥናት)** ስ ያለማወላወል፥ በአንድ አቋም ላይ መርጋት።

**ፀናፅል** ስ መዘምራን (ካህናት) ማህሌት በሚቆሙበት ጊዜ በቀኝ እጃቸው ይዘው ወደላይና ወደታች በማንቀሳቀስ የሚያቅጨለጭሉት የቤተክርስቲያን የዝማሬ መሳሪያ (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

**ፀአዳ** ስ 1. ንፁህ፥ የፀዳ። 2. ነጭ።

***ፀየፈ**

**ፀያፍ (ጠያፍ)** ቅ 1. ነውር፥ የሚያስጠላ፥ የማያስቀይም። 2.ሰው ፊት ወይም በአደባባይ መነገር የማይገባው (ነገር)።

**ፅዩፍ(ጥዩፍ)** ቅ ተጠያፊ፥ እጅግ ጥንቁቅ (የማይፈልገውን ነገር ወይም ምግብ ባለመንካት ወይም ባለመጠቀም)።

**ተፀየፈ(ተጠየፈ)** ግ ናቀ፥ ጠላ።

**ተፀያፊ** ቅ ንቀትን፥ ጥላቻን የሚያሳይ።

**አስፀየፈ** ግ አስጠላ፥ አስከፋ፥ አስቀየመ።

**አስፀያፊ** ቅ 1. የሚያስጠላ፥ የሚያስቀይም። 2. መጥፎ፥ ነውር፥ አሳፋሪ የሆነ።

**ፀደቀ**[1] ግ 1. መንግስተ ሰማያት ወይም ገነት ገባ። 2 ተመቸው፥ የሚስማማውን አገኘ።

**ፀደቀበት** የሚፈልገውን በመስጠት ወይም በማድረግ ችግሩን አቃለለለት።

**ፀዲቅ (ፃዲቅ፥ጣዲቅ)** ስ በመላእክት፥ በፃድቃን፥... ስም ወይም ሟችን ለመዘከር የሚጋገር ዳቦ።

**ፃድቅ** (ብ. ቁ. **ፃድቃን**) ቅ 1. ለነፍሱ ያደረ ሃይማኖተኛ ሰው። 2. መልካም፥ ደግ ሰው። 3. በመንፈሳዊ ተግባሩ ከቅዱስነት ደረጃ የደረሰ መሆኑ ታምኖበት በስሙ ቤተክርስቲያን የተሰራለትና ፅላት የተቀረፀለት፥ የበቃ ሰው።

**ፅድቅ** ስ 1. መልካም ስራ ለሰራና የእግዚአብሄርን ትእዛዝ ለፈፀመ ከእግዚአብሄር የሚሰጥ ሰማያዊ ዋጋ። 2. መልካም፥ በጎ ስራ።

**ፀደቀ**[2] 1. የተተከለ ችግኝ ለመደ፥ ለመለመ፥ ስር ሰደደ። 2. ጠና፥ ተቀባይነት አገኘ፥ ይሁን ተባለ (ሃሳብ፥ውሳኔ፥ ...)።

**ፀደይ** ስ ከመጋቢት 26 እስከ ሰኔ 25 ያለው ጊዜ፤ የበልግ ወቅት፥ የዘር ወራት።

**ፀዲቅ** "ፀደቀ" ስር ተመ.

**ፀዳ (ጠዳ)** ግ ነፃ፥ ጠራ፥ ንፁህ ሆነ።*ቤቱ ፀዳ መስሪያ ቤቱ ከሌቦች ፀዳ።*

**ፅዱ** ቅ ንፁህ፥ ያማረ፥ የፀዳ።

**ፅዳት** ስ ንፅህና።

**የፅዳት ሰራተኛ** ስ ቤትን ወይም ቢሮን፥... በማፅዳት የሚተዳደር ሰው።

**ተፀዳዳ** ግ ሽንትን ወይም አይነ ምድርን ከሰውነቱ ውስጥ አስወገደ ወይም አስወጣ።

**መፀዳጃ [ቤት]** ስ ሽንት ቤት።

**አፀዳ** ግ 1. አጠበ፥ ንፁህ አደረገ። 2. ወለወለ፥ ጠረገ። 3. አጠራ፥ ንፁህ አደረገ (ከሌባ፥ ከወንበዴ፥...)።

**አይፀዳሽ** ቅ ደስተኛ ያልሆነ፥ ብዙ ጊዜ ፊቱ ላይ ደስታ የማይታይበት።

**ፀዳል** ስ ብርሃን ወይም የብርሃን ፍንጣቂ።

**ፀጉር (ጠጉር)** ስ 1. በእንስሳት አካል ላይ የሚበቅል ጭገር። 2. በሰው ገላ በተለይም በጭንቅላት ላይ ብዛት ያለው ሆኖ የሚበቅል ጭገር።3. እንደ ሹራብ ባሉ ልብሶች ላይ የሚገኝ እንደፀጉር ያለ የሚነጭ ጭገር።

**ጉሩ ሸሸ** ፀጉሩ መመለጥ ጀመረ።

**ፀጉር ስንጠቃ** በአንድ ጉዳይ ላይ ከሚያስፈልገው በላይ ጥቃቅን የሆኑ ነጥቦችን ማንሳት።


**ፀጉረ ሉጫ** ለስላሳ ፀጉር ያለው ሰው።

**ፀጉረ ልውጥ** ለአካባቢው እንግዳ የሆነ አዲስ ሰው።

**ፀጉር ቆራጭ /አስተካካይ** ስ የወንዶችን ፀጉር የሚቆርጥ፥ የሚያስተካክልና የሚያሳምር ባለሙያ።

**ፀጉር ሰሪ** ስ የሴቶችን ፀጉር በመቁረጥ፥ በመተኮስ፥በመጎንጎን፥ ... የሚያሳምር ባለሙያ።

**[የ] ፀጉር አሰራር** ስ የተለያዩ አይነቶች የፀጉር አጎናጎን፥ አለባበጥ፥... መንገዶች (ብዙውን ጊዜ የሴቶች) ።




[የ] ፀጉር አሰራር

**ፀጋ** ስ አምላካዊ ስጦታ፥ ሃብት፥ ረድኤት።

**ፀጥ**

**ፀጥታ** ስ 1. ዝምታ ወይም የድምፅ አለመኖር። 2. እርጋታ፥ ሰላም።

**ፀጥታ ነሳ** ሰላም ነሳ፥ አወከ፥ ረበሸ።

**ፀጥታ አስከባሪ** ስ ሁከትን ወይም ረብሻን የሚቆጣጠርና የሚከላከል ሰላም አስጠባቂ ወታደራዊ ሃይል።

**የፀጥታ ምክር ቤት** ስ አምስት ቋሚ የሆኑና በየጊዜው የሚቀየሩ አስር አባል ሃገሮች ያሉት፥ የአለምን ሰላም ለመጠበቅ በተባበሩት መንግስታት ስር የተቋቋመ ድርጅት።

**ፀጥተኛ** ቅ 1. ዝምተኛ፥ ጨዋ። 2. ጫጫታ ወይም ሁካታ የሌለበት ሰላማዊ (ቦታ)።

**ፀጥ አለ** ግ 1. ዝም ወይም ጭጭ አለ። 2. ሰላም ሰፈነ። *ሃገሩ ፀጥ ብሏል።* 3. (ዘይ.) አረፈ፥ ሞተ።

**ፀጥ አሰኘ** ግ ዝም ወይም ጭጭ እንዲል አደረገ።

**ፀጥ አደረገ** ግ 1. ዝ.ከ. ። 2. ገደለ።

**ፀፀተ** ግ ባላደረግሁ ወይም ባልሰራሁ አሰኘ፥ቆጨ።

**ፀፀት** ስ ባላደረግሁ፥ ባልሰራሁ፥ባልተናገርሁ፥.. የሚያስኝ የሃዘን ወይም የቁጭት ስሜት::

**ተፀፀተ** ግ ባላደረግሁ፥ ባልሰራሁ፥... አለ፥ ተቆጨ፤ ባደረገው፥ በሰራው፥... አዘነ፥ ቅር ተሰኘ::

**ፁ** የ"ፀ"ፊደል ካእብ ዘር::

**ፂ** የ"ፀ" ፊደል ሳልስ ዘር::

**ፂም (ጢም)** ስ በአገጭ፥ በጉንጭና በከንፈር አካባቢ የሚበቅል ፀጉር::

**ፂም አወጣ** ፂም አበቀለ::

**ፂም መላጫ** ስ ምላጭን በውስጡ መያዝ የሚችልና ለመላጫነት የሚያገለግል ባለእጀታ መሳሪያ::

**ፃ** የ"ፀ" ፊደል ራብእ ዘር::

**ፃህል** ስ የቅዱስ ቁርባን መያዣና ማቅረቢያ ዝርግ ሳህን::

**ፃእረሞት "ጣእረ ሞት"**ን ተመ.

**ፃእር "ጣእር"** ን ተመ.

**ፃዲቅ "ፀደቀ"** ስር ተመ.

**ፃድቅ** ዝ.ከ.

**ፃፈ** ግ 1. በወረቀት፥ በብራና፥... ላይ ቀለም ባለው ነገር (ብእር፥ እስክሪብቶ፥...) የፊደላትን ቅርፅ አስቀመጠ፤ ከተበ:: 2. ፅሁፍ ወይም ድርሰት አዘጋጀ፤ ደረሰ:: 3. በፅሁፍ ገለፀ ወይም አሳወቀ:: 4. ደብዳቤ ላከ:: 5. ቀለም በማውረድ በወረቀት ወይም በብራና ላይ ምልክት ማድረግ ቻለ (ብእር፥ እስክሪብቶ):: *እስክሪብቶው መፃፍ ጀመረ::*

**መጣጥፍ** ስ በአንድ ርእስ ላይ የተፃፈን ማብራሪያ፥ ገለፃ፥ ምርምር፥... የያዘ አጭር ፅሁፍ::

**መፅሃፍ** (ብ.ቁ .**መፃህፍት**) ስ በእጅ ወይም በታይፕ ወይም በህትመት መሳሪያ የተፃፈ፥ ብዙ ገፆች ያሉትና በጥራዝ መልክ የተዘጋጀ ፅሁፍ::

**መፅሃፍ ገላጭ** ኮከብ ቆጣሪ፥ ጠንቋይ::

**መፅሃፍ ቅዱስ** ስ ብሉይና ሃዲስ ኪዳንን አጣምሮ የያዘ መፅሃፍ::

**ፀሃፊ** ስ 1. በፅሁፍ ስራ ላይ የተሰማራ ሰራተኛ:: 2. ለአንድ ባለስልጣን ደብዳቤዎችን የማርቀቅና በታይፕ የመፃፍ፥ መዛግብትን የመያዝ፥ መልእክቶችን የመቀበል፥.. ስራ የሚያከናውን ሰራተኛ:: 3. ፅሁፍ አዘጋጅ ወይም ደራሲ::

**ፀሃፌ ትእዛዝ** ስ ከንጉስ የሚሰጡ ትእዛዞችን የሚፅፍና የሚልክ እንዲሁም ከውጭ የሚመጡ ደብዳቤዎችን እየተቀበለ ለንጉስ የሚያቀርብ የሚኒስትርነት ማእረግ የነበረው ባለስልጣን::

**ፅሁፍ** ስ 1. በወረቀት፥ በብራና፥... ላይ የተፃፈ ወይም የሰፈረ ነገር:: 2. በአንድ ርእስ ጉዳይ ላይ የተጠናቀረ ዘገባ:: 3. የአፃፃፍ ወይም የፊደል አጣጣል ሁኔታ::

**የፅሁፍ ፈተና** ስ ለቀረበ ጥያቄ መልሱ በፅሁፍ ብቻ የሚቀርብበት ወይም የሚሰጥበት የፈተና አይነት::

**ፅህፈት** ስ 1. በቀለም፥ በብእር፥... አማካኝነት ወረቀት፥ ብራና፥... ላይ የሰፈረ ነገር:: 2. አፃፃፍ፥ የፊደል አጣጣል:: 3. ለተለያየ ነገር መድሃኒት ወይም መፍትሄ ይሆናል እየተባለ በተለያየ ቀለም በወረቀት፥ በብራና፥... ላይ ተፅፎና ተጠቅልሎ በሰውነት ላይ የሚታሰር ክታብ::

**የፅህፈት መሳሪያ** ስ እንደ እርሳስ፥ እስክሪብቶ፥ ወረቀት፥ ማስመሪያ፥.. የመሳሰሉና ለፅሁፍ ስራ የሚያገለግሉ እቃዎች::

**የፅህፈት ስራ** ስ ከፅሁፍ ስራ ጋር የተያያዘ ስራ::

**የፅህፈት ጠረጴዛ** ስ የፅህፈት ስራ የሚከናወንበት ጠረጴዛ::

**ፅህፈት ቤት** ስ የአንድ ድርጅት ወይም መስሪያ ቤት የአስተዳደር፥ የፅህፈት ስራ፥... የሚከናወንበት ቦታ፥ ቢሮ::

**ተፃፃፈ** ግ መልእክትን በፅሁፍ ተለዋወጠ::

**ፄ** የ"ፀ" ፊደል ሃምስ ዘር::

**ፅ** የ"ፀ" ፊደል ሳድስ ዘር::

**ፅሁፍ "ፃፈ"** ስር ተመ.

**ፅህፈት** ዝ.ከ.

**ፅላት** ስ ታቦት፤ በላዩ ላይ ስመ እግዚአብሄር የተፃፈበት የእንጨት ሰሌዳ::

**ፅላተ ሙሴ /አሪት/ ኪዳን** ስ በብሉይ ኪዳን እንደተፃፈው እግዚአብሄር ለሙሴ የሰጠውና አስርእቱ ትእዛዛት የተፃፉበት የድንጋይ ሰሌዳ::

**ፅልመት** ስ 1. ጨለማ:: 2. ጥቁረት::

**ፅልማሞት (ጥልማሞት)** ስ 1. ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ:: 2. በጣም የጠቆረ፥ ጥቀርሻ የመሰለ ነገር::

**ፅልምያኮስ (ጥልም ያኮስ)** ቅ 1. በጣም ጥቁር የሆነ፥ ጠቋራ:: ስ 2.ሰይጣን::

**ፅሞና (ጥሞና)** ስ እርጋታ፥ ዝግታ::

**በፅሞና** በእርጋታ:: *የተነገረውን ሁሉ በፅሞና አዳመጠ::*

**ፅኑ "ጠና"** ስር ተመ.

**ፅና "ፅንሃህ"**ን ተመ.

**ፅናት[1] "ፀና"** ስር ተመ.

**ፅናት[2] "ጠና"** ስር ተመ.

**ፅንሃህ (ፅንሃ፥ ፅና፥ ጥና)** ስ ከብረት ወይም ከነሃስ የሚሰራ የቤተክርስቲያን እጣን ማጨሻ፣ ሻኩራ።

**ፅንስ "ፀነሰ"** ስር ተመ.

**ፅንፍ "ጠንፍ"** ስር **"ጥንፍ"** ን ተመ.

**ፅዋ(ጥዋ)** ስ 1. ከሸክላ ወይም ከቀንድ፥... የሚሰራና ለመጠጫ የሚያገለግል እቃ። 2. በመላእክት፥ በሰማእታት ፥... ስም ማህበር የሚጠጡ ምእመናን በፀበል መልክ የተዘጋጀውን ጠላ የሚሸሙበት ትንሽ ገንቦ። 3. በመላእክት፥ በሰማእታት፥... ስም የሚጠጣ ማህበር። 4. (ዘይ.) እድል፥ እጣ፥ ፋንታ።



ፅንሃህ

**ፅዋውን አነሳ** (በግብግብ ወቅት) መጠጥ የተቀዳበትን ብርጭቆ ወደላይ ከፍ አድርጎ በመያዝ ግብግቡ ለተካሄደበት ጉዳይ ያለውን ድጋፍ፥ ደስታ፥...ገለፀ።

**ፅዋው ሞላ** እድሜው ደረሰ፥ የተወሰነው የግፍ ጊዜ አለቀ። *ፅዋው ሲሞላ ሁሉም የስራውን ያገኛል።*

**ፅዱ "ፀዳ"**ስር ተመ.

**ፅዳት** ዝ.ከ.

**ፅድ "ጥድ"**ን ተ.መ.

**ፅድቅ "ፀደቀ[1]"**ስር ተመ.

**ፅጌ** ስ 1. የአበባ ወቅት፣ "ወርሃፅጌ" ም ይባላል። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ .) ቅድስት ድንግል ማርያም ልጇን ይዛ ወደ ግብፅ የተሰደደችበትን ጊዜ በማሰብ ከመስከረም 26 እስከ ህዳር 6 ቀን የሚደረግ.የፆም፥ የፀሎትና የማህሌት ወራት።

**ፅጌረዳ** ስ የተለያየ ቀለምና ጥሩ መአዛ ያለው የአበባ አይነት፣ ተክሉም ፅጌረዳ ይባላል።

**ፆ** የ"ፀ" ፊደል ሳብእ ዘር።

**ፆመ(ጦመ)** ግ 1. ሃይማኖታዊ በሆነ ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሰአት መብላትና መጠጣት ተወ፥ ከምግብ ተቆጠበ። 2. በስርአተ ሃይማኖት ምክንያት ለተወሰኑ ቀናት ስጋ፥ ቅቤ፥ ወተት፥... ከመመገብ ተቆጠበ።

**ፆም** ስ 1. ሃይማኖታዊ በሆነ ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሰአት መብላትና መጠጣት ፈፅሞ ሙሉ በሙሉ መተው ወይም የተወሰኑ የምግብ አይነቶችን፥ ተግባሮችን፥ ... መተው።2. ፆም የሚፆምበት ጊዜ፥ ወቅት።

**ፆሙን (ጦሙን) ዋለ** ምግብ ሳይቀምስ ዋለ።

**ፆም ሻረ** 1. ፆም መፆሙን ትቶ ወይም ዘንግቶ ያለሰአቱና ያለ ጊዜው በላ።2. በፆም ጊዜ የፍስክ ምግብ በላ።

**ፆም ያዘ** መፆም ጀመረ።

**የፆም ምግብ** ስ እንደ ስጋ፥ ቅቤ፥ ወተትና እንቁላል፥... ያሉትን የማይጨምር የምግብ አይነት።

**የፆም ቆሎ** ስ 1. የሁዳዴ ፆም ሲያልቅ ለነፍስ አባት የሚሰጥ እህል ወይም ዱቄት፥...። 2. በፆም ጊዜ ምእመናን ለካህናት የሚሰጡት ቆሎ(በገጠር አካባቢ)። 3. ቀደም ሲል በነበረው ስርአት በፆም ጊዜ ገባር ለሹም ወይም ለባለርስት ይሰጠው የነበረ የቆሎ እህል።

**የፆም ወጥ** ስ 1.ስጋ ወይም ቅቤ የሌለው ወጥ። 2. (ዘይ.) ችኮ፥ ለዛ የሌለው (ሰው)።

**ፆመ ድጓ** ስ 1. በሁዳዴ ፆም ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚዘመር ያሬዳዊ ድርሰት። 2. ከላይ የተጠቀሰውን ዜማ የያዘ መፅሃፍ።

**ፆመኛ** ስ የፆምን ስርአት ተከትሎ የሚፆም ሰው።

**ጿሚ** ዝ.ከ.

**ፆታ** ስ ወገን (የእንስት ወይም የተባእት)።

**ጿ** የ"ፀ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

**ጿሚ "ፆመ"** ስር ተመ.

# ፊ

**ፊ** ከ "ፀ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ) ።

**ፈለመ** ግ 1. ቀድሞ መታ ወይም ወጋ:: *ውሃ ለቀደመ ግዳይ ለፈለመ::* 2. ተለመ፥ አንድ ፈር ቀደደ (ለእርሻ)::

**ፍልሚያ** ስ 1. ትግል፥ ግብግብ፥ ውጊያ:: 2. ጥል፥ አምባጓሮ::

**ፍልም** ስ ትልም::

**ተፋለመ** ግ ትግል፥ ግብግብ፥ ውጊያ ገጠመ::

**ተፋላሚ** ቅ ባላንጣ፥ ተፎካካሪ (በትግል፥ በውጊያ)::

**ፈለሰ** ግ 1. ተሰደደ፥ አገሩን ጥሎ ሄደ:: 2. ተነቀለ፥ ተመነገለ፥ ተፈነቀለ::

**መፍሉስ** ቅ 1. ጥርሰ ሸራፋ፥ ወላቃ:: 2. ከራንቻ ጥርሱ ወልቆ በፊት በኩል ከታችና ከላይ ሁለት ጥርስ ያለው (በቅሉ)::

**ፈላሻ** ስ 1. ይኖርበት የነበረውን አገር ለቆ በመሄድ በሌላ አገር የሚኖር ህዝብ 2. ቤተ እስራኤል::

**ፍልስልስ** ቅ የወላለቀ፥ የፈራረሰ::

**ተፋለሰ** ግ 1. ተለዋወጠ፥ በተባለው ጊዜ ሳይሆን ቀረ:: *እሱ በመቅረቱ ፕሮግራማችን ተፋለሰ::* 2. ተበታተነ፥ ተለያየ፥ ተዘበራረቀ (አንድ ላይ የነበረ፥ በስርአት የተቀመጠ ወይም ተመሳሳይ የነበረ ነገር)::3. ተጓቀሰ፥ተደባደበ::

**አፈለሰ** ግ 1. ነቀለ፥ አወለቀ:: 2. ነቅሎ ወይም አንስቶ ወደ ሌላ ቦታ ወሰደ:: 3. መታ:: *በኩርኩም አፈለሰው::*

**አፋለሰ** ግ 1. በታቀደው ወይም በተወሰነው ጊዜ እንዳይሆን አደረገ:: 2. አዘበራረቀ፥ በታተነ (በአንድ ላይ፥ በስርአት የተቀመጠን ወይም ተመሳሳይ የነበረን ነገር):: 3. አጣላ፥ እንዳይስማሙ አደረገ::

**ፈለሰመ** "**ፈለሰፈ**"ን ተመ.

***ፈለሰሰ**

**ፈልሳሳ(ፈለስስ)** ቅ በምቾት ወይም በድሎት ያለ፥ ደስተኛ::

**ተንፈላሰሰ** ግ ተመቸው፥ ደላው ወይም ተንደላቀቀ::

**አንፈላሰሰ** ግ እንዲመቸው ወይም እንዲደላው አደረገ፥ አንደላቀቀ::

**ፈለሰፈ(ፈለሰመ)** ግ በምርምር ወይም በጥናት አዲስ ነገር ሰራ፥ አገኘ::

**ፈላስፋ (ፈላስማ)** ስ 1. የፍልስፍና ሰው:: 2. አንድን ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ የሰራ፥ የፈጠረ፥ ያገኘ ሰው:: 3. ጥበበኛ፥ አዋቂ፥ ተመራማሪ::

**ፈልሳፊ** ቅ አንድን ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ የሰራ፥ ያገኘ፥ የፈጠረ::

**ፍልስፍና** ስ 1. ስለ ተጨባጩ አለም እውነታ፥ በተለይም የተፈጥሮን አመጣጥ፥ ምክንያትና ምንነት እንዲሁም ይህ ሁሉ ነገር የሚመራበትን ስርአትና እውነት ለማወቅ ወይም ለማግኘት ጥናት የሚያደርግ የእውቀት ዘርፍ:: 2. በተራ ቁጥር አንድ በተጠቀሰው የእውቀት ዘርፍ መሰረት በአንድ ነገር ላይ በተደረገ ጥናትና ምርምር አማካኝነት የሚገኝ ግንዛቤ፥ እምነት፥ እውቀት፥ የሰረፀ አተያይ ።

**ተፈለሰፈ** ግ በምርምር አንድ አዲስ ነገር ተሰራ፥ ተፈጠረ::

**ተፈላሰፈ** ግ ተመራመረ፥ ተራቀቀ::

**ተፈላሳፊ** ስ ተመራማሪ::

**አፈላሰፈ** ግ አመራመረ::

**ፈለቀ** ግ 1. ከስር ወደላይ ወጣ፥ ፈሰሰ፥ መነጨ (ለምሳሌ ምንጭ)::2. ብልጭ አለ፥ በረቀ፥ አንፀባረቀ (ብርሃን)::

**ፍልቅ አለበት** አቀረሸው (ህፃን)::

**ፍላቂ** ቅ ሙሉ ፈሳሽ ከያዘ ብርጭቆ፥ ጠርሙስ፥...ላይ በትንሹ ቡልቅ ብሎ የሚፈሰው ፈሳሽ::

**ፍልቅልቅ** ቅ ፊቱ ላይ ፈገግታ ወይም የደስታ ስሜት የሚታይበት::

**ፍልቅልቅ አለ** ግ ተፍለቀለቀ::

**ተፍለቀለቀ** ግ 1 . በጣም ፈላ፥ ተንተከተከ:: 2. ፊቱ በደስታ በራ፥ ተደሰተ፥ ፈነደቀ::

**አፈለቀ** ግ 1. አወጣ፥ አመነጨ (ውሃን):: 2. ከራሱ (ከአእምሮው) አንቅቶ ወይም አመንጭቶ አቀረበ:: *አዲስ ሃሳብ አፈለቀ::*

**ፈለቀቀ** ግ 1. የተጣበቀ ነገርን ለየ፥ ከፈለ፥ ፈረቀቀ:: 2. የጥጥ ፍሬን ለማውጣት ፍንድን አላላ:: 3. የጥጥ ፍንድን እያላላና ፍሬውን ከውስጡ እየፈለገ አወጣ::

**ፍልቃቂ** ቅ ከተያያዘ ወይም ከተጣበቀ ወይም ድፍን ከሆነ ነገር ውስጥ ተለይቶ ወይም ተከፍሎ የወጣ አንዱ ክፍል:: *የብርትኳን ፍልቃቂ::*

**ፍልቅቅ** ቅ 1. ፍሬውን ለማውጣት እንዲያመች ተብሎ የላላ (የጥጥ ፍንድ):: 2. ተያይዞ ወይም ተጣብቆ የነበረና በኋላም በከፊል የተላቀቀ፥ የተሰነጠቀ::

**ተፈለቀቀ** ግ 1. ተያይዞ ወይም ተጣብቆ የነበረው በከፊል ተላቀቀ፥ ተሰነጠቀ:: 2. የጥጥ ፍንድ፥ የአበባ እምቡጥ፥... ሽፋኑን ሰንጥቆ

ወይም ፈልቅቆ ወጣ (ወደውጭ)።

**ፈለቀጠ** ግ ከፈለ፥ ገመሰ፥ ፈለቀቀ (ሎሚን፥ ብርትኳንን፥..)።

**ፍልቃጭ** ቅ ከፋይ፥ ገማሽ፥ ፍንካች።

***ፈለከለከ**

**ፍልክልክ አለ** ግ ተፍለከለከ።

**ተፍለከለከ** ግ በብዛት ተንቀሳቀሰ፥ ተላወሰ፥ ተርመሰመሰ (ትላትል፥ ነፍሳት)።

**አፍለከለከ** ግ አርመሰመሰ።

**ፈለገ** ግ 1. ሻ፥ ወደደ፥ ፈቀደ። 2. የጠፋን ወይም አስፈላጊ የሆነን ነገር ለማግኘት ሞከረ፥ ጣረ።

**ፍለጋ** ስ የጠፋን ወይም የሚያሻን ነገር ለማግኘት የሚደረግ ሙከራ፥ ጥረት።

**ፍላጎት** ስ አንድ ነገር ለማድረግ፥ ለማግኘት፥ ለመሆን የመሻት ስሜት።

**ተፈለገ** ግ አስፈላጊ ሆነ።

**ተፈላጊ** ቅ 1. ጠቃሚ፥ ተገቢ፥ ተስማሚ። *ጃንጥላ ለክረምት ተፈላጊ እቃ ነው።* 2. ተወዳጅ።*የኢትዮጵያ ቡና በጣም ተፈላጊ ነው።*

**ተፈላለገ** ግ 1. ተጠያየቀ፥ ተሳሰበ። 2. አንዱ ሌላውን ለማግኘት ጣረ። 3. ፈለገ። *እስኪ በአካባቢህ የሚሸጥ ቤት እንዳለ ተፈላለግልኝ።*

**ተፈላለጉ** 1. ተዋደዱ(ተቃራኒ ፆታዎች በፍቅር)። 2. ለፀብ፥ ለግድያ ተሳሰቡ።

**አፈላለገ** ግ አንድን ነገር ለማግኘት በየቦታው፥ በየአቅጣጫው ፈለገ ወይም አጠያየቀ።

**አፋለገ** ግ የጠፋ ነገር ለማግኘት በሚደረግ ፍለጋ ረዳ፥ ተባበረ።

**አስፈለገ** ግ 1. ተፈላጊ፥ ጠቃሚ ሆነ።2. አማረ።*አዲስ ልብስ አስፈለገኝ።* 3. አንድ ነገር መሆን፥ መደረግ፥ መገኘት፥... እንዳለበት ግድ ሆነ።

**አስፈላጊ** ቅ ጠቃሚ፥ ተፈላጊ።

**ፈለግ** ስ 1. ከእጅና እግር ጣት እንዲሁም ከተረከዝ ላይ እየተላጠ የሚነሳ ቆዳ። 2. መሬት ላይ የሚያርፈው የኮቴ፥ የጫማ፥ የእግር ቅርፅ፤ ዱካ። 3. አርአያ፥ ምሳሌ። *የወንድሙን ፈለግ ተከትሎ ሃኪም ሆነ።*

**ፈለጠ** ግ 1. ሰነጠቀ፥ ገመሰ፥ ሸነሸነ (ለምሳሌ እንጨትን)። 2. ተረከከ፥ በዱላ መታ (ጭንቅላትን)። 3. በጣም አመመ (ራስ ምታት)።

**ፈላጭ "እንጨት ፈላጭ"** ን ተመ.

**ፈላጭ ቆራጭ** 1. አምባገነን፤ በህዝብ ፍላጎትና ፈቃድ ሳይሆን እንዳሻው የሚመራ ወይም የሚያስተዳድር (መሪ፥ መንግስት)። 2. ሌሎችን በመጫን ራሱ እንደፈለገው ብቻ ማንኛውንም የሚያደርግ።

**ፍላጭ** ስ የፍልጥ ስንጣሪ፥ ቁራጭ።

**ፍልጥ** ስ የተሰነጣጠቀ፥ የተፈላለጠ እንጨት።

**ፍልጥ ያህላል** ትልቅ ነው (ብዙውን ጊዜ ለጥርስ)።

**ፈለፈለ[1]** ግ 1. ቦረቦረ፥ ሰረሰረ። 2. በተነባበረ ወይም በተጠጋጋ ነገር ስር ወይም መካከል ሰርስሮ ለመግባት ታገለ። 3. ፍሬን ከሽፋኑ፥ ከቆረቆንዳው ለየ፤ ጠረጠረ።

**ፈልፍሎ አወጣ** (የተደበቀ ነገርን፥ ምስጢርን፥...) ፈልጎ ወይም ተከታትሎ ይፋ አወጣ።

**ፈልፈላ** ቅ 1. ተንኮለኛ፥ ሸረኛ። 2. የተደበቀ ነገር የማያመልጠው፥ ሰርሳሪ።

**ፍልፍል** ቅ ከእንቁሪባው ወይም ከቆረቆንዳው የተላቀቀ የባቄላ፥ የበቆሎ፥...ፍሬ።

**ፈለፈለ[2]** ግ ብዙ ልጅ ወለደ።

**ፈለፈለች** ዶሮ ወይም ወፍ ለታቀፈችው እንቁላል ሙቀት በመስጠት ጫጩት እንዲወጣ አደረገች።

**ፍልፍል** ቅ ከእንቁሪባው ወይም ከሽፋኑ የተላቀቀ የባቄላ፥ የበቆሎ፥... ፍሬ ።

**ተፈለፈለ** ግ ተቀፈቀፈ፥ ጫጩት ከእንቁላል ውስጥ ወጣ።

**ፈሊጥ** ስ 1. በምሳሌ፥ በንፅፅር፥ በተረትና ምሳሌ፥... አማካኝነት የሚቀርብና ስሜትን የሚስብ የአነጋገር ዘዴ፤ ዘይቤ። 2. የባህርይ፥ የልማድ፥ የአሰራር ዘዴ።

**ፈሊጣዊ አነጋገር** ስ ሁለት ቃላት ለየብቻቸው ሆነው ሲነገሩ ከሚሰጡት ሃሳብ ውጪ በአንድ ላይ ሲጣመሩ የሚሰጡት የተለየ ሃሳብ (ለምሳሌ እጁ አጠረ ፥ልቡ ወለቀ፥ አይን አውጣ፥ ሆደ ሰፊ)።

**ፈላ[1]** ግ 1. ተፍለቀለቀ፥ ተንተከተከ (እሳት ላይ የተጣደ ውሃ፥ ወጥ፥...) 2. ሊጠጣ ደረሰ (እሳትላይ የተጣደው ቡና ወይም ሻይ)። 3. (ጥንስስና እንኩሮ በአንድ ላይ በመሆን) ተብላላ።

**ፈላበት** የጥጋብ ወይም የጉርምስና ስሜት ተሰማው።

**እንፋሎት** ስ ከሚፈላ ውሃ ወይም ሌላ ፈሳሽ ነገር ላይ የሚወጣ ጭስ መሰል ነገር፤ ተን።

**ፍላሎት** ስ የታፈነ፥ የታመቀ የሃዘን ወይም የንዴት ስሜት።

**ፍል** ቅ በጣም የሞቀ ወይም የፈላ(ውሃ)።

**ፍል ውሃ** ስ በተፈጥሮ ከመሬት እየፈለቀ የሚወጣ ሙቅ ውሃ።

**ፈላ[2]** ግ 1. በቀለ፥ ችግ አለ (ችግኝ)። 2. (ዘይ.) በብዛት ታየ፥ ቁጥሩ ጨመረ።

**አፈላ** ግ ፍሬ ዘርቶ ችግኝ አበቀለ::

**ፍል** ስ ችግኝ::

**ፈላስማ** "ፈለሰፈ" ስር "ፈላስፋ"ን ተመ.

**ፈላስፋ** "ፈለሰፈ" ስር ተመ.

**ፈላሻ** " ፈለሰ" ስር ተመ.

**ፈላጭ** " ፈለጠ" ስር ተመ.

**ፈልሳሳ** "*ፈለሰሰ" ስር ተመ.

**ፈልሳፊ** " ፈለሰፈ" ስር ተመ.

**ፈልፈላ** " ፈለፈለ[1]" ስር ተመ.

**ፈረመ** ግ 1. አንድን ፅሁፍ ህጋዊ ለማድረግና በይዘቱ መስማማቱን ለመግለፅ በፅሁፉ ግርጌ ስሙን ፃፈ+ ፊርማውን አኖረ::2. (ዘይ.) በፊርማ አፀደቀ::*ስምምነቱን የፈረሙ ሃገሮች::*

**ፊርማ** ስ 1. አንድን ፅሁፍ ህጋዊ ለማድረግና ስምምነትን ለመግለፅ የሚመለከተው አካል በፅሁፉ መጨረሻ ላይ ከስም ጋር የሚኖረው የራሱ የሆነ የጣት አሻራ ወይም የፅሁፍ ምልክት:: 2. ውል+ ስምምነት::

**ፊርማ ቀደዱ** ተፋቱ+ ጋብቻቸው ፈረሰ::

**ተፈረመ** ግ የፊርማ ምልክት ተደረገበት::

**ተፈራረመ** ግ በፅሁፍና በፊርማ ተዋዋለ (ለጋብቻ ወይም ለሌላ ጉዳይ)::

**አፈራረመ** ግ በፅሁፍና በፊርማ አዋዋለ::

***ፈረመረመ**

**ፍርምርም** ቅ ትጉህ+ ተጣጣሪ::

**ተፍረመረመ** ግ ተፍጨረጨረ+ ተጣጣረ::

**አፍረመረመ** ግ አፍጨረጨረ+ አተጋ::

**ፈረሰ** ግ 1. ተናደ+ ተፈነቃቀለ+ እንዳልነበር ሆነ:: 2. ተሻረ (ህግ+ ስርአት+ ውል+ ደንብ):: 3. ተበተነ+ ሳያልቅ ተቋረጠ (ስብሰባ):: 4. ሳይሆን+ ሳይሳካ ቀረ:: *ቀጠሮው ፈረሰ::* 5. ቁምጥና+ ደረመን አጠቃው:: *ሰውነቱ ፈረሰ ::* 6. በሰበሰ (ሬሳ)።

**ፈራረሰ** ግ ፈረሰ+ ወዳደቀ+ እንዳልነበር ሆነ::

**ፈራሽ** ቅ 1. ቋሚ ያልሆነ+ ሟች:: 2. ዘላቂነት የሌለው+ ጊዜያዊ::

**ፍራሽ** ቅ ከፈረሰ ቤት ወይም አጥር ላይ የሚሰበሰብ እቃ (እንጨት+ ቆርቆሮ+...)::

**ፍርስራሽ** ዝ.ከ.

**ፍርስ አለ** ግ (ዘይ.) በጣም ሳቀ ወይም በጣም አለቀሰ::

**ፍርስ አደረገ** ግ (ዘይ.) በጣም አሳቀ ወይም በጣም አስለቀሰ::

**ተፋረሰ** ግ 1. ሳይስማማ ቀረ (በሃሳብ+ በውል+...):: 2. ከሸፈ+ ሳይሳካ ቀረ::

**አፈረሰ** ግ 1. ናደ+ ፈነቃቀለ+ እንዳልነበር አደረገ:: 2. ሻረ+ ጣሰ:: *ህግ አፈረሰ::* 3. ተቃወመ፤ አልስማማ አለ:: 4. መድሃኒትነቱን እንዲያጣ አደረገ+ አረከሰ:: 5. ቅስናውን+ ምንኩስናውን+...ተወ+ህጉን ጣሰ+ ስርአቱን ተላለፈ:: 6. ቃል በገባበት ወይም በተስማማበት መሰረት ሳያደርግ ቀረ፤ ከዳ:: 7. ቀደም ሲል የተነገረን ሃሳብ ትክክል እንዳልሆነ አሳየ ወይም አረጋገጠ :: *ቲዎሪውን አፈረሰ::*

**አፍራሽ** ቅ 1. ገንቢ ወይም ጠቃሚ ያልሆነ(ሃሳብ+ ድርጊት):: 2. አሉታዊ (ሃሳብ ወይም አገላለፅ)::

**አፈራረሰ** ግ ናደ+ አፈረሰ+ እንዳልነበር አደረገ::

**አፋረሰ** ግ እንዳይሳካ+ ስምምነት እንዳይኖር አደረገ::

**ፈረሰኛ[1]** ስ በደረት በኩል የሚገኝ የዶሮ ብልት::

**ፈረሰኛ[2]** "ፈረሰ" ስር ተመ.

**ፈረሱላ** ስ አስራ ሰባት ኪሎ ያህል የሚመዝን የቡና+ የበርበሬና የሌሎች ልዩ ልዩ ነገሮች ክብደት መለኪያ::

**ፈረሳ ቤት** ስ ሰውነት ላይ ችፍ ብሎ የሚወጣ የእከክ አይነት::

**ፈረስ** ስ 1. ከቤት እንስሳት አንዱ የሆነ+ ለስላሳ ጋማና ጭራ እንዲሁም አራት እግሮች ያሉትና ለመጓጓዣ የሚያገለግል የጋማ ከብት (ስእሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.):: ቅ 2. (ዘይ.) ሀ. ረዥምና ግዙፍ የሆነ ሰው:: ለ. ተጠንቅቆ የማይራመድ+ ደንባራ (ሰው)::

**የፈረስ ስም** "አባ" የሚለውን ቃል እያስቀደመ የሚነገር+ ፈረስ የመጋለብ ወይም የመቀመጥ ሞያ ወይም ችሎታ ላላቸው ነገስታት+ መሳፍንት+ መኳንንትና ጀግኖች የሚሰጥና የባለፈረሱን ጠባይ+ ምኞት የሚገልፅ ስም፤ "አባ ታጠቅ"+ "አባ ዳኘው" የመሳሰለው አይነት ስም::

**የፈረስ ዘንግ** ስ ግንዱ ውስጠ ክፍት ሆኖ ቅልጥም ያለው+ በአናቱ አካባቢ ድብልብል የሆነ የአበባና የፍሬ መያዣ ኳስ መሰል ነገሮች የሚገኙበት አነስተኛ የእፀዋት አይነት፤ ራስ ክምር::

**የፈረስ ጉልበት** ስ 750 ያህል ኪሎ ዋት ጉልበት ያለው የሞተር ጉልበት መለኪያ::

**ፈረሰኛ** ቅ ፈረስ ግልቢያ አዋቂ ::

**ፈረሰኛ ውሃ** ስ በዝናብ ምክንያት ወንዝ በሚሞላበት ጊዜ ንፁህ የነበረውን የወንዝ ውሃ እያደፈረሰ ከዋናው የውሃው ሙላት ፊት ለፊት የሚጋልበው ድፍርስ ወይም ደራሽ ውሃ::

***ፈረቀ**

**ፈረቃ** ስ (የመማሪያ+ የመስሪያ ጊዜ) ተራ፤

*ወረፉ::ተማሪዎቹ በፈረቃ ይማራሉ::*

**ተፈራረቀ** ግ አንድን ነገር በየተራ አደረገ፤ አንዱ ሲለቅ ሌላው ተተካ::

**አፈራረቀ** ግ ከአንዱ በሗላ ሌላውን ተካ፥ አለዋወጠ::

***ፈረቀረቀ**

**ፍርቅርቅ** ቅ በምጣድ ላይ እያለ ስለነፈሰበት የተሰነጣጠቀ፤ ፍርክርክ (እንጀራ ወይም ዳቦ)::

**ተፍረቀረቀ** ግ ተሰነጣጠቀ፥ ነቃ፥ ተፍረከረከ (ዳቦ፥ እንጀራ)::

**አፍረቀረቀ** ግ ፍርቅርቅ እንዲሆን አደረገ፤ አፍረከረከ::

**ፈረቀቀ** ግ ለያየ፥ ነጣጠለ፥ ፈለቀቀ::

**መፈርቀቂያ** ስ ሽብልቅ::

**ተፈረቀቀ** ግ ተፈለቀቀ፥ ተነጣጠለ፥ ተለያየ::

**አፈራቀቀ** ግ አለያየ፥ አራራቀ:: *ለግሩን አፈራቆ ቆሟል::*

**ፈረቃ** "***ፈረቀ**" ስር ተመ.

***ፈረነሰ**

**ፍርንስ (ፈርናሳ)** ቅ ዘና ብሎ ወይም ተንፈላሶ የሚተኛ፥ የተኛ::

**ፍርንስ አለ** ግ ተፈረነሰ::

**ተፈረነሰ** ግ ዘና ብሎ ወይም ተንፈላሶ ተኛ::

**ፈረንጅ** ስ የቆዳው ቀለም ነጭ የሆነ የውጭ አገር ሰው::

***ፈረከረከ**

**ፍርክርክ(ፈረክራካ)** ቅ 1. የሚፈረፈር፥ የሚሸራረፍ:: 2. ፈሪ፥ ቡከን::

**ፍርክርክ አለ** ግ ተፍረከረከ::

**ተፍረከረከ** ግ 1. ተሸራረፈ፥ ተፈረፈረ:: 2. መበታተን፥ መለያየት፥ መፈራረስ፥... ጀመረ (አንድ አይነት አላማ ወይም ሃሳብ የነበረው የፖለቲካ ድርጅት፥ ቡድን፥...):: 3. በፍርሃት ተርበተበተ፥ ተርበደበደ::

**አፍረከረከ** ግ 1. ሸራረፈ፥ ፈረፈረ:: 2. መለያየት፥ መበታተን እንዲፈጠር አደረገ (አንድ አይነት አላማ ወይም ሃሳብ በነበረው የፖለቲካ ድርጅት፥ ቡድን፥...መካከል)::

**ፈረከሰ** ግ 1. ገመሰ፥ ሰነጠቀ:: 2. አደቀቀ፥ ሰባበረ (ለምሳሌ ድንጋይን):: 3. ፈነከተ፤ አቆሰለ (ራስን)::

**ፈርካሳ** ቅ (ስድብ) በርጋዳ፥ እግሯን አፈራቃ፥ በርግዳ የምትቀመጥ (ሴት)::

**ፍርክስ** ቅ የተገመሰ፥ የተሰነጠቀ::

**ፍርክስክስ አለ** ግ ፍርስርስ አለ (ለምሳሌ የተቀቀለ ድንች፥ ባቄላ፥... በጣም ከመብሰሉ የተነሳ)::

**ተፈረከሰ** ግ ተገመሰ፥ ተሰበረ::

**ተፈረከሰች** ግ (የጥላቻ አነ.) ብርግድ ብላ፥ እግሯን አፈራቃ ተቀመጠች::

**ተፈረካከሰ** ግ ፍርክስክስ አለ::

***ፈረከከ**

**ፈርካካ** ቅ በፍርንትቱ አካባቢ ቁስል እንዳለበት ሁሉ ጭንና ጭኑ የማይጠጋጋ፥ የተራራቀ፥ በርጋዳ::

**ፈርክክ አለ** ግ ተንፈራከከ::

**ፈርክክ አደረገ** ግ አንፈራከከ::

**ተንፈራከከ** ግ ተራራቀ፥ ተለያየ፥ ተበራገደ (ለምሳሌ ጭንና ጭን)::

**አንፈራከከ** ግ አራራቀ፥ ለያየ፥ በረገደ (ለምሳሌ ጭንና ጭንን)::

**ፈረክራካ** "***ፈረከረከ**" ስር "**ፍርክርክ**"ን ተመ.

***ፈረዘዘ**

**እንፍርዝ** ቅ 1. ሆዱ የሞላ፥ የጠገበ:: 2. (ዘይ.) ዘና፥ ረጋ ያለ::

**ፈርዛዛ (ፈረዝዝ)** ቅ 1. ዝ.ከ.:: 2. (ዘይ.) ደስተኛ የሆነ፥ ሰላም ወይም ርጋታ ያለው::

**ፍርዝዝ አለ** ግ ተንፈረዘዘ::

**ተንፈረዘዘ** ግ 1. ጠገበ፥ ሆዱ ሞላ:: 2. (ዘይ.) ተደሰተ፤ ሰላም፥ እርካታ ወይም ርጋታ አገኘ፥ ተዝናና::

**አንፈረዘዘ** ግ 1. አጠገበ:: 2. አስደሰተ:: 3. ዘና፥ ረጋ አደረገ::

**ፈረደ** ግ 1. ፍርድ፥ ውሳኔ ሰጠ:: 2. ጥፋተኛ አደረገ:: *ለጫ በሉ ላይ ፈረደ::* 3. ባለውቃቢ ውቃቢዬ ነገረኝ የሚለውን መልስ ለጠያቂዎቹ (ለአስጠንቋዮቹ) ተናገረ::

**ፈረደበት** መጥፎ ወይም ክፉ ነገር አጋጠመው ወይም ደረሰበት::

**የፈረደበት** መከረኛ፥ ያልታደለ::

**ፍረደኝ** ጉዳዩን አይተህና ተመልክተህ ውሳኔ ወይም ዳኝነት ስጠኝ::*ህዝብ ፍረደኝ::*

**ፍርደኛ** ቅ ለፈፀመው ጥፋት በፍርድ ቤት ተፈርዶበት ወህኒ ቤት በእስር ላይ የሚገኝ::

**ፈራጅ** ስ ፍርድ ወይም ውሳኔ ሰጪ፥ ዳኛ::

**ፍርድ** ስ የዳኛ ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ::

**ፍርደ ገምድል** ትክክለኛ ያልሆነ ወይም አድሉአዊ ፍርድ የሚፈርድ::

**ፍርዱ ቀጠነ** ፍርዱ ተዛባ፥ ተጓደለ::

**ፍርድ ሸንጎ** ስ በቀበሌና በገበሬ ማህበራት ውስጥ ከነዋሪው ህዝብ መሃል ተመርጦ የዳኝነትን

ስራ ያከናውን የነበረ ኮሚቴ (ከ1966 አብዮት ወዲህ እስከ 1983 ኢ.ም.)።

**ፍርድ ቤት** ስ ዳኞች ፍርድ የሚሰጡበት፥ የዳኝነት ስራ የሚከናወንበትና ህግ የሚተረጎምበት መስሪያ ቤት።

**ፍርጃ** ስ መጥፎ አጋጣሚ፥ ጣጣ፥ ችግር።

**ተፈረደ** ግ ፍርድ ተሰጠ፥ ተበየነ።

**መፋረጃ (መፍረጃ) አደረገ** ግ ሰው እንዲወቅሰው ወይም እንዲፈርድበት አደረገ።

**ተፋረደ** ግ ጉዳዩን ለፍርድ አቀረበ።

**ይፋረደዋል** ላደረሰው በደል፥ግፍ፥... ይከሰዋል ወይም ለፍርድ ያቀርበዋል።

**ተፋራጅ** ቅ ተከራካሪ፥ ከሳሽ።

**አስፈረደ** ግ ጉዳዩ ወይም ክሱ እሱን በሚጠቅም ሁኔታ እንዲፈረድ አደረገ።

**ፈረድ** ስ ውሃ የሸረሸረው ፈፋ፥ ጉድባ።

**ፈረጀ** ግ በአንድ የተወሰነ መመዘኛ ወይም መለኪያ መሰረት በአይነት በአይነቱ፥ በመልክ በመልኩ፥.. ከፋፈለ፥ ለየ፥ መደበ።

**ፈርጅ** ስ 1. ወገን፥ ክፍል፥ መደብ። 2. የሸማ አንዱ አርብ (ለምሳሌ አንድ ነጠላ ሁለት ፈርጅ አንድ ጋቢ ደግሞ አራት ፈርጅ ሸማ ይኖረዋል)።

***ፈረገረገ**

**ፍርግርግ አለ** ግ ተፍረገረገ።

**ተፍረገረገ** ግ ተንፈራገጠ።

**አፍረገረገ** ግ አንፈራገጠ።

***ፈረገጠ**

**ፍርግጥ ፍርግጥ አለ** ግ ተፈራገጠ።

**ተፈራገጠ (ተንፈራገጠ)** ግ ተጋድሞ ወይም ተኝቶ እግሩን በማጠፍ፥ በመዘርጋት ወይም በማወራጨት ወዲያና ወዲህ ተንቀሳቀሰ፥ ተወራጨ (በህመም፥ በቅዠት፥... ምክንያት)።

**አፈራገጠ (አንፈራገጠ)** ግ ተጋድሞ ወይም ተኝቶ እግሩን ወዲያ ወዲህ በማንቀሳቀስ፥ በማጠፍ በመዘርጋት፥... አንቀሳቀሰ፥ አወራጨ (በህመም፥ በቅዠት፥... ምክንያት)።

**ፈረጠ[1]** ግ 1. ውስጡ የነበረው ፈሳሽ ፈንድቶ ወጣ፥ ፈሰሰ (ለምሳሌ ጡት፥ ቁስል፥ እባጭ)። 2. ተሰብሮ ወይም ተጨፍልቆ በውስጡ ያለው ፈሳሽ ፈሰሰ (እንቁላል፥ ቲማቲም፥...)። 3. (ዘይ.) ወጣ፥ ይፋ ሆነ (እውነቱ)። 4. ጠፋ፥ ፈሰሰ (አይን)።

**ፍርጥ ብትል** ፈፅሞ፥ በጭራሽ፥ ምንም ቢሆን ለማለት የሚያገለግል አገላለፅ። *ፍርጥ ብትል ገንዘብ አይሰጥህም።*

**ፍርጥርጥ አለ** ግ 1. በውስጡ ያለው መግል፥ ፈሳሽ ወጣ፥ ነፈረቀ (ቁስል)።2. ወጣ፥ ግልፅልፅ አለ (እውነቱ)።

**ተፍረጠረጠ** ግ 1. መግሉ፥ ፈሳሹ እንዲወጣ ተደረገ፥ ነፈረቀ (ቁስል)። 2. ወጣ፥ ይፋ ሆነ (እውነቱ)።

**አፍረጠረጠ** ግ 1. አድፈጠፈጠ፥ አመገለ (ቁስሉን)። 2. ይፋ አውጥቶ ተናገረ (እውነትን)።

**ፈረጠ[2]** ግ ወደቀ፥ ተፈጠፈጠ።

**አፈረጠ** ግ ጣለ፥ ከሰከሰ፥ ፈጠፈጠ።

**ፈረጠመ** ግ ዳበረ፥ ወፈረ፥ ጠነከረ (ለሰውነት)።

**ፍርጥም (ፈርጣማ)** ቅ ሰውነቱ የዳበረና የጠነከረ።

**ፍርጥም ያለ** ዝ.ከ.

**አፈረጠመ** ግ 1. ፈረጠመ። 2. ፈርጣማ እንዲሆን አደረገ።

**ፈረጠጠ** ግ 1. ሸመጠጠ፥ ሮጠ። 2. ሸሸ።

**ፈርጣጭ** ቅ 1. ከፍርሃት የተነሳ የሚሮጥ፥ የሚሸሽ። 2. ኮብላይ።

***ፈረጠጠ**

**ተንፈራጠጠ** ግ እግሮቹን አራርቆ፥ በጣም ከፍቶ ቆመ ወይም ተቀመጠ። *ሰውየው ተንፈራጦ ቆመ።*

**አንፈራጠጠ** ግ እግሮቹን አራርቆ፥ በጣም ከፍቶ ቆመ ወይም ተቀመጠ *እግሮቹን አንፈራጦ ቆሟል።*

**ፈረፈረ** ግ 1. እንጀራ ወይም ዳቦ ቆራርሶ ወጥ ወይም ቁሌት ውስጥ በመፈትፈት ፍርፍር አዘጋጀ።2. በትንንሹ ቆራረጠ፥ ቆራረሰ (ዳቦን እንጀራን)። 3. ሸረሸረ፥ ቦረቦረ።

**ፈረፈር** ስ ጎርፍ የቦረቦረው ወይም የሸረሸረው መሬት።

**ፍርፋሪ** ስ 1. ተበልቶ የተረፈና የነኳኮተ ወይም የተቆራረሰ እንጀራ፥ ዳቦ፤ ትርፍራፊ። 2. ከተቆረሰ ዳቦ፥ ኬክ፥... ላይ ከስር የሚቀረው የደቀቀ ቁርስራሽ።

**ፍርፍር** ስ እንጀራ ቆራርሶ ቀጠን ባለ ወጥ፥ መረቅ ወይም ቁሌት ውስጥ በመጨመርና በመጠኑ ደረቅ አድርጎ በመፈትፈት የሚዘጋጅ ምግብ።

**ተፈረፈረ** ግ 1. ተቆራረሰ፥ ደቀቀ። 2. ተቦረቦረ፥ ተሸረሸረ።

***ፈረፈረ**

**ፍርፍር አለ** ግ ተንፈራፈረ።

**ተንፈራፈረ** ግ ተንፈራገጠ፥ ተወራጨ፥ ተንደፋደፈ።

**አንፈራፈረ** ግ አንፈራገጠ፥ አወራጨ፥ አንደፋደፈ።

**ፈረፈር** "ፈረፈረ" ስር ተመ.

**ፈረፋንጎ (ፋራፋንጎ)** ስ ለጭቃ መከላከያነት የሚያገለግልና የመኪናን+ የብስክሌትን+... ጎማ በከፊል የሚሸፍን ቀጭን ብረት ወይም ቆርቆር።

**ፈሪሳዊ** ቅ ከንቱ ውዳሴ ወዳድ፣ እንዲህ ሰራ+ አደረገ+... መባልን የሚፈልግ፣ መሞካሸት+ መመፃደቅ የሚሻ፣ ግብዝ።

**ፈራ** ግ 1. ተርበደበደ+ ተንቀጠቀጠ+ ተሸበረ (ከአደጋ+ ከጭንቀት+ ከሚያስፈራ ነገር የተነሳ)። 2. ድፍረት አጣ። *መናገር ፈራ።* 3. ሰጋ+ ጠረጠረ። *ከስራ ያባርሩኛል ብሎ ፈራ።* 4. አከበረ+ ታዛዥ ሆነ። *እግዚአብሄርን ይፈራል።* 5. አፈረ+ ተሸኮረመመ። *የሰው አይን ፈራ።*

**ሲፈራ ሲቸር** ሳድርግ አላድርግ በማለት እያመነታ።

**ፈራ ተባ አለ** ሳድርግ አላድርግ በማለት አመነታ+ መድፈር አቃተው።

**ፈሪ** ቅ 1. ጀግንነት የሌለው+ ቡከን። 2. ድፍረት የሌለው። 3. አይነአፋር።

**ለ ___ ፈሪ** ለ ___ አንድ የጎደለው (ለምሳሌ ለመቶ አንድ ፈሪ ማለት ዘጠና ዘጠኝ ማለት ነው)።

**ፈሪሃ እግዚአብሄር** እግዚአብሄርን መፍራት።

**ፍርሃት (ፍራት+ ፍራቻ)** ስ 1. የመረበሽ ስሜት። 2. ስጋት+ ጥርጣሬ። 3. ድፍረት የማጣት ስሜት። 4. አይነ አፋርነት።

**ፍርሃት ፍርሃት አለው** ግ 1. ባባ+ ተረበሸ። 2. ድፍረት አጣ።

**ተፈራ** ግ 1. የሚያሰጋ+ የማይደፈር ሆነ። 2. ተጠረጠረ+ እስጊ ይሆናል ተብሎ ተገመተ። 3. ታፈረ+ ተከበረ።

**አስፈራ** ግ አሰጋ+ ጥርጣሬ ፈጠረ።

**አስፈሪ** ቅ 1. የፍርሃት+ የጭንቀት ስሜት የሚያሳድር ወይም የሚፈጥር። 2. አስከፊ።

**አስፈራራ** ግ 1. የፍርሃት ስሜት ፈጠረ+ አስጨነቀ። 2. ዛተ።

**ማስፈራሪያ ፊት** በጣም አስቀያሚ ፊት።

***ፈራ**

**ፍሬ** ስ 1. ተክል ከአበበ በሂላ ከአበባው ወይም ሊበላ ወይም የተለያየ ጥቅም ሊሰጥ ከሚችለው የተክሉ ክፍል ውስጥ የሚገኘውና በሂላም ተመልሶ ሲዘራ የሚበቅለው የተክል ቅንጣት፣ ዘር። 2. የአንድን ተክል ዘር በውስጡ ይዞ የሚገኘውና ሊላው አካሉ የሚበላው ክፍል (ለምሳሌ የብርትኳን+ የወይን+ የሾላ+... ፍሬ)። 3. (ዘይ.) ሀ . ቁም ነገር።*ንግግሩ ፍሬ የለውም።* ለ. መልካም ውጤት። *በስራችን ለፍሬ በቅተናል።* 4. ልጅ+ ዘር። *ትወደው ከነበረ ባሏ ፍሬ ሳታገኝ ቀረች።* 5. ፍሬ የሚመስል ቅርፅ ያለውና ወንዴ ዘር የሚገኝበት የአባለዘር ክፍል።

**ፍራፍሬ** ስ እንደ ብርትኳን+ ፓፓያ+ ሙዝ+... ያሉ የሚበሉ የተክል ፍሬዎች። ...

**ፍሬ ሰሞነኛ** ቅ (ኢ . ኦ. ተ. ቤ.) የሳምንቱ ተረኛ ዲያቆን (በተወሰነው ሰአት ቤተክርስቲያንን በመክፈትና በመዘጋት+ የቁርባን ህብስት በማዘጋጀት+... አገልግሎት የሚሰጥ)።

**ፍሬ ሰው** ስ ዋና+ ቁምነገረኛ ሰው።

**ፍሬቢስ** ቅ ቁምነገር የሌለው+ ከንቱ።

**ፍሬ ነገር** ስ ዋና+ ቁም ነገር።

**ፍሬከርስኪ (ፍሬፈርስኪ)** ቅ የማይረባ+ ቁምነገር የሌለው።

**ፍሬ ግብር** ስ ዋና+ አይነተኛ ግብር።

**ፍሬያማ** ቅ 1. ብዙ ፍሬ ያለው። 2. ጥሩ ውጤት ያለው።

**አፈራ** ግ 1. ፍሬ ያዘ ወይም አወጣ። 2. አስገኘ+ አወጣ።*ዩኒቨርሲቲው ብዙ ምሁራንን አፈራ።* 3. ወለደ። *ብዙ ልጆች አፈራ።* 4. አገኘ (ለምሳሌ ገንዘብን)።

**ፈራረሰ** "ፈረሰ" ስር ተመ.

**ፈራሽ** ዝ.ክ.

**ፈራጅ** "ፈረደ" ስር ተመ.

**ፈር** ስ 1.ማረሻ ሰንጥቆ የሄደበት የእርሻ መስመር፥ ትልም። 2. ስርአት+ መስመር።

**ፈር ያዘ** መስመር፥ ስርአት ያዘ።

**ፈርስ** ስ 1.በጨጓራ ውስጥ የሚገኝ የተፈጨና የቀጠነ የምግብ ጥርቅም። 2. ሆድ፥ ከርስ። 3.በውስጠኛው በኩል የሚገኘው የልብስ ወይም የጨርቅ መልክ።

**ፈርሳም** ቅ (ስድብ) ቀፈታም+ ቦርጫም።

**ፈርናሳ** "*ፈረነሰ" ስር "ፍርንስ"ን ተመ.

**ፈርካሳ** "ፈረከሰ" ስር ተመ.

**ፈርካካ** "*ፈረከከ" ስር ተመ.

**ፈርዛዛ** "*ፈረዘዘ" ስር ተመ.

**ፈርጅ** "ፈረጀ" ስር ተመ.

**ፈርጣማ** "ፈረጠመ" ስር " ፍርጥም" ን ተመ.

**ፈርጣጭ** "ፈረጠጠ" ስር ተመ.

**ፈርጥ** ስ ከተለያዩ የከበሩ ድንጋዮች የሚሰራና በቀለበት+ በዘውድ፥... ላይ የሚደረግ የሚያብለጨልጭ ጌጥ።

**ፈሰሰ** ግ 1. ተደፋ፥ ተከነበለ። 2. ተነገረ+ ተገለፀ። *ኑዛዜው ፈሰሰ።* 3. ምቾት ወይም ድሎት ባለበት ሁኔታ ተጓዘ።*በመኪና እየፈሰሰ መጣ።* 4.ተጨመረ+ ተደረገ።እርሻው ላይ ፍግ

*ፈሰሰበት*፡5. ወጣ (ለምሳሌ ዘር ከወንድ ብልት)። 6. በብዛት ሆኖ ታየ ወይምወጣ። *ሰዉ ሜዳ ላይ ፈሰሷል/የፈሰሰው ገንዘብ ትንሽ አይምስልህ።*

**ፈሰስ** ስ 1. በዝናብ ጊዜ ከጣሪያ የሚወርድ ውሃ፤ ጠፈጠፍ። 2. የውሃ መሄጃ ቦይ። 3. ሹሩባ በተሰራ ፀጉር፥ በሹሩባዎቹ መካከል ያለው ክፍት ቦታ። 4. (ብዙውን ጊዜ ለመንግስት) ተመላሽ የሚሆን ገንዘብ።

**ፈሳሽ** ስ እንደ ውሃ ወይም ዘይት ያለና በቀላሉ መፍሰስ የሚችል ጠጣር ወይም ጋዝ ያልሆነ ነገር።

**ፍሳሽ** ስ 1. ቆሻሻ ከሆነና ከሚያፈስ ጣሪያ ላይ የሚወርድ የዝናብ ውሃ። 2. እጣቢ፥ የቆሸሸ ውሃ ወይም ጎርፍ።

**ተፋሰሰ** ግ 1. እየፈሰሰ ባክኑ፥ ተበታተኑ። 2. ወጪ ገቢን ተሳሰበ።

**ተፋሰስ** ስ በስተውጭ በኩል በቤት ጣሪያ ዙሪያ ለዝናብ መከላከያ ተብሎ የሚሰራ ታዛ።

**አፈሰሰ** ግ 1. ደፋ፥ ከነበለ፥ በተነ። 2. ሽንቁር ወይም ቀዳዳ ስለአለው አልይዝ አለ፥ አንጠባጠበ። 3. ስልጣን ከህነቱን አፈረሰ። 4. ከሳ፥ ሰውነቱ ቀነሰ፥ ያልሰባ ሆነ። *ሙክቱ ላፍሰሷል።* 5. እንጀራ ጋገረ፥ አሰፋ። 6. ተናገረ፥ ገለፀ (ኑዛዜን)። 7. ዘርን ከሰውነቱ (ከብልቱ) አስወጣ፥ አስወገደ (ወንድ)።8. በብዛት አወጣ (ገንዘብን፥...)።

**አፋሰሰ** ግ 1. እያፈሰሰ አባከነ፥ በታተነ። 2. ወጪ ገቢን አሳሳ፥ ሂሳብ አስተሳሰበ።

**ፈሰከ(ፈሰገ)** ግ *ፆሙን ፈታ፥ ገደፈ።*

**ፋሲካ (ፋሲጋ)** ስ 1. ሃምሳ አምስት ቀናት የሚፈጀው የሁዳዴ ፆም አብቅቶ ፆሙ የሚፈታበትና በአሉ የሚከበርበት እለተ እሁድ፣ ትንሳኤ። 2. ለተወሰኑ ቀናት ከተፆመ በሗላ ፍቺ የሚደረግበት ቀን፣ ፍስክ። 3. (ዘይ.) ደስታ። *ቤታቸው ሁልጊዜ ፋሲካ ነው።*

**ፍስክ (ፍስግ)** ስ 1. ለተወሰኑ ቀናት ከተፆመ በሗላ ፆሙ አብቅቶ ፍቺ የሚደረግበት ቀን። 2. ስጋ፥ ቅቤ፥ እንቁላል፥... የሚበላበት ወይም የማይፆምበት ጊዜ።

**የፍስክ (የፍስግ)** ቅ በፍስክ ጊዜ የሚበላ (ለምሳሌ ስጋ፥ ቅቤ፥...)።

**ተፈሰከ (ተፈሰገ)** ግ *ፆም ተፈታ።*

**ፈሰፈሰ** ግ 1. ደጋግሞ መታ፥ ደበደበ። 2. አንድን ነገር በብዛት አደረገ። *ምግቡን፥ ስራውን፥... ፈሰፈሰው።*

**ፈሳ** ግ 1. በአይነ ምድር መውጫው በኩል መጥፎ ሽታ ያለው አየር ከሆዱ አስወጣ። 2. ሟሸሸ፥ ተጨማተረ፤ ተነፈሰ።

**ፈሰፈስ(ፈስፋሳ)** ቅ ፈሪ፥ ቡከን።

**ፈስ** ስ 1. መጥፎ ሽታ ያለውና በአይነምድር መውጫ በኩል ከሆድ የሚወጣ የተቃጠለ አየር። 2. (ዘይ.) ፈሪ።

**ፈሱ ቀረጥ/ዘረጥ አለ** 1. (ተራ አነ.) የፈስ ድምፅ አሰማ፥ ፈሳ።

**ፈሱን ቀደደ** (ተራ አነ.) ፈሱን አንዛረጠ።

**ፈሱን ቆረጠ /ጨረሰ** (ተራ.አነ) አንድን ነገር ለማከናወን ወይም ለማግኘት በጣም ለፋ።

**ፈሱን አስረጨው** (ተራ አነ.) 1. በጣም አለፋው፥። 2.አዘረጠው፥ በሃይል ደበደበው።

**ፈሱን ጠበሰ /ጨረሰ** (ተራ. አነ.) መከራውን አየ፥ ተሰቃየ።

**ፈሳም** (ስድብ) ቅ 1.ቶሎ ቶሎ የሚፈሳ። 2. (ዘይ.) ፈሪ፥ ቡከን።

**ፈስንዱስ** ቅ ፈሳም።

**አስፈሳ** ግ 1. በሃይል መታ፥ ደበደበ። 2. በጣም ከበደ(ለምሳሌ ሸክም) ።

**ፈሳሽ** "ፈሰሰ"ስር ተመ.

**ፈስ** "ፈሳ" ስር ተመ.

**ፈስንዱስ** ዝ.ክ.

**ፈስፋሳ** "ፈሳ" ስር "ፈሰፈስ"ን ተመ.

***ፈቀረ**

**ፍቅር** ስ 1. ከፍተኛ የሆነ የመውደድ ስሜት (ለምሳሌ የሃገር ፍቅር /የእናት ፍቅር/ መንፈሳዊ ፍቅር)። 2. በሁለት ተቃራኒ ፆታዎች መካከል ያለና በወሲብ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የመዋደድ ፥ የመሳሳብ ስሜት። 3. ወዳጅ፥ ስምም። *እገሌና እገሌ ፍቅር ናቸው።*

**በፍቅር ወደቀ** ፍቅር ያዘው።

**ፍቅር አደረበት** በአንድ ነገር ላይ ከፍተኛ የሆነ ፍላጎት፥ የመውደድ ስሜት ኖረው። *የሙስራት ፍቅር አደረበት።*

**ፍቅር ያዘው** ከተቃራኒ ፆታ ጋር በወሲባዊ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የመውደድ ስሜት አደረበት።

**የፍቅር ደብዳቤ** ስ ለፍቅረኛ የሚፃፍ ደብዳቤ።

**ፍቅረ ንዋይ** ስ የገንዘብ መውደድ።

**ፍቅ ሩ ጠና** ስ የጥጥ ፍንድ የሚያካክል ጠጎጎታማ አበባ ያለውና በነካው ነገር ላይ ሁሉ የሚጣበቅ፥ መጠኑ አስተናጋር የሚያክል የእፅዋት አይነት።

**ፍቅረኛ** ስ ከወሲባዊ ፍላጎት ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚወዱት ወይም የሚያፈቅሩት ሰው፤ ወዳጅ።

**ተፈቀረ** ግ ተወደደ ።

**ተፈቃቀረ** ግ ተዋደደ፥ ተስማማ።

**ተፋቀረ** ግ ተዋደደ፥ ተግባባ።

**አፈቀረ** ግ 1. ፍቅረኛ አደረገ። 2. ወደደ።

**አፍቃሪ** ቅ የሚያፈቅር፥ የሚወድ።

**አፈቃቀረ** ግ አፋቀረ፥ እንዲዋደዱ አደረገ።

**አፋቀረ** ዝ.ከ.

**ፈቀቅ (ፈቅ)**

**ፈቀቅ አለ** ግ ራቅ፥ ገሸሽ፥ ገለል አለ።

**ፈቀቅ አይልም** አይሄድም፥ አልፍ አይልም፥ አይንቀሳቀስም።

**ፈቀቅ አደረገ** ግ አራቀ፥ ገለል፥ ገሸሽ አደረገ፣ ገፋ።

**ፈቀደ** ግ 1. ፈቃድ ሰጠ። 2. ወደደ፥ ፈለገ፥ ከጀለ። 3. ቆጠረ፥ አስተዋለ፥ ተከታተለ። *ከብቶቹን ፍቀዳቸው* 4. ተመለከተ፥ በአይኑ ፈለገ። *ከሰው መካከል ብፈቅደው አጣሁት።* 5. ጠበቀ፥ ጥንቃቄ አደረገ። *ሀገሩን ፍቀደው።*

**በዘፈቀደ** እንዳሻው፥ እንደፈለገው፥ እንደፈቀደው።

**እንደፈቀደው** እንዳሻው፥ እንደፈለገው።

**ፈቃድ(ፍቃድ)** ስ 1. አንድ ነገር ለማድረግ፥ ለማከናወን የሚመለከተው ክፍል መስማማቱን ገልፆ ጉዳዩን ለሚያከናውነው አካል የሚሰጠው ማስረጃ። *ንግድ ፈቃድ/ መንጃ ፈቃድ።* 2. ለተወሰነ ጊዜ ከስራ ነፃ መሆን እንዲቻል የሚሰጥ እረፍት። 3. ፍላጎት፥ ስምምነት። *ያለ እሱ ፈቃድ የሚሆን ነገር የለም።*

**ፈቃድ ሰጠ** 1. አንድ ነገር ማድረግ እንዲቻል ፈቀደ፥ ተስማማ። 2. ለተወሰነ ጊዜ ከስራው ላይ እንዲቀር ፈቀደ፥ ተስማማ።

**ፍቃድ ወሰደ** ለማረፍ ወይም ሌላ ጉዳይ ለማከናወን ፈቃድ ጠይቆ ከስራ ገበታው ላይ ቀረ።

**የፈቃድ ወረቀት** ስ አንድ ነገር ለማድረግ ወይም ለማከናወን መፈቀዱን የሚገልፅ የፅሁፍ ማስረጃ።

**ፈቃድ ፈፃሚ** ቅ እሺ ባይ፥ ታዛዥ።

**ፈቃደኛ** ቅ ግዳጅ ሳይኖርበት በራሱ ፍላጎትና ስምምነት አንድ ነገር ለማድረግ የተነሳሳ ወይም የተዘጋጀ።

**ፈቃጅ** ቅ ጠባቂ። *ሀገሩ ፈቃጅ የለውም።*

**ተፈቀደ** ግ እንዳይደረግ ተከልክሉ ወይም ታግዶ የነበረው ነገር መከልከሉ ቀረ፣ ፈቃድ ተሰጠ።

**ተፈቃቀደ** ግ ተጠያየቀ፥ ተሳሰበ።

**ተፈቃቀዱ** ለፍቅር፥ ለጋብቻ፥... ተፈላለጉ። *እገሌትና እገሌ ተፈቃቅደዋል።*

**አስፈቀደ** ግ 1. ፈቃድ ጠየቀ። *አለቃሁን አስፈቀድኩ።* 2. ፈቃድ አገኘ። *ከስራ የቀረው አስፈቅዶ ነው።*

**ፈቀፈቀ** ግ 1. ፋቀ፥ ላገ። 2. የተጣበቀ፥ የተላከከ ነገርን ለማላቀቅ ፈገፈገ።

**ፍቅፋቂ** ቅ 1. እንጨት ወይም ሌላ ነገር ሲፋቅ የሚወጣው ድቃቂ ወይም ገለባ። 2. ከምጣድ ላይ አልነሳ ያለ የትኩስ እንጀራ ስብርባሪ።

***ፈቀፈቀ**

**ፈቅፈቅ አለ** እየተቀቀለ ያለ ነገር በመጠኑ ፈላ፥ ፈለቅለቅ አለ።

**ፈቅፈቅ አደረገ** ግ እየተቀቀለ ያለ ነገርን በመጠኑ አፈላ፥ ፈለቅለቅ አደረገ።

**ተንፈቀፈቀ** ግ 1. ፈላ፥ ተፍለቀለቀ (እየተቀቀለ ያለ ነገር)። 2. (ዘይ.) ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ።3.በተከታታይ ተተኮሰ (ለምሳሌ መትረየስ)።

**አንፈቀፈቀ** ግ 1. አፈላ፥ አፍለቀለቀ። (እየተቀቀለ ያለ ነገርን)። 2. ስቅስቅ አድርጎ አስለቀሰ።3. በብዛትና በተከታታይ ተኮሰ። *መትረየሱን አንፈቀፈቀው።*

**ፈቃ** ግ ሰውነትን በስለት በጣ፥ ሰነጠቀ።

**ፈቃደኛ** "**ፈቀደ**" ስር ተመ.

**ፈቃድ** ዝ.ከ. **ፈቃጅ** ዝ.ከ.

**ፈቅ** "**ፈቀቅ**" ን ተመ.

**ፈተለ**[1] ግ 1. ጥጥ አባዝቶ ወይም ፈልቅቆ በእንዝርት እያከረረ ፈትል እንዲሆን አደረገ። 2. ገመደ፥ ሸረበ።

**ፈታይ** ቅ ጥሩ የመፍተል ችሎታ ያላት (ሴት)።

**ፈትል** ስ ጥጡ ተባዝቶ በእንዝርት እየተከረረ የሚዘጋጅ ማግ፥ ክር፥ ድር።

**አፋተለ** ግ 1. እጆቹን ወይም እግሮቹን እርስ በርሳቸው አሸ፥ አፍተለተለ። 2. እርስ በርሱ አንዱን ከሌላው ጋር አጋመደ፥ አጣመረ።

**ፈተለ**[2] ግ ተረበ፥ አሽሟጠጠ።

**ፈታላ** ቅ ተረበኛ፥ አሽሟጣጭ።

***ፈተለተለ**

**ፍትልትል (ፈተልታላ)** ቅ ቅልጥፍና የሌለው፥ ጎታታ (በአካሄድ፥ በስራ)።

**ፍትልትል አለ** ግ ተፍተለተለ።

**ፍትልትል አደረገ** ግ አፍተለተለ።

**ተፍተለተለ** ግ 1. ሲታሽ እየተድቦለቦለ ወይም እየተጥመለመለ ወጣ፥ ተነሳ (ለምሳሌ የሰውነት እድፍ)። 2. ተጎተተ፥ አልፈጥን አለ (በአካሄድ፥ በስራ)።

**አፍተለተለ** ግ 1. እያሸ የሰውነት እድፍን እንዲወጣ አደረገ:: 2. እንዲጎተት፥ እንዳይፈጥን አደረገ:: 3. ሆድን ቆረጠ፥ አመመ::

***ፈተለከ**

**ፈትለክ አለ** ግ 1. በድንገት ወይም በፍጥነት ሮጠ፥ አመለጠ:: 2. ከአንድ ነገር ውስጥ የነበረ ነገር በድንገት ወጣ::

**ፍትልክ አለ** ግ 1. ከታሰረ ወይም ከተጠላለፈ ክር፥ ገመድ፥... ላይ አንዱ ክፍል ላልቶ ወይም ተፈትቶ ወይም ሾልኮ ወጣ:: 2. ፈትለክ አለ::

**ተፈተለከ** ግ በድንገት ወይም በፍጥነት ሮጠ፥ አመለጠ::

**አፈተለከ** ግ 1. በድንገት ወይም በፍጥነት ሮጠ፥ አመለጠ 2. በድንገት አመለጠ:: (ከእጅ፥ ከአፍ፥...) :: 3. ከታሰረ ወይም ከተጠላለፈ ክር፥ ገመድ፥... ላይ አንዱ ክፍል ላልቶ ወይም ተፈትቶ ወይም ሾልኮ ወጣ::

**ፈተልታላ"*ፈተለተለ"** ስር **"ፍትልትል"**ን ተመ.

**ፈተሸ** ግ 1. ፈለገ፥ መረመረ፥ ጎረጎረ ( የጠፋ እቃን ለማግኘት):: 2. የተደበቀ ወይም ህጋዊ ያልሆነ ነገርን ፈልጎ ለማግኘት በረበረ::3. ጉልበትን፥ ጥንካሬን ወይም አንድ ነገር መስራት አለመስራቱን ሞከረ::

**ፈታሽ** ስ በፍተሻ ስራ የተሰማራ ሰው::

**ፍተሻ** ስ 1. ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የሚወጡና የሚገቡ እቃዎችን፥ ሰዎችን፥... በአንድ በተወሰነ ቦታ ላይ ሆኖ የመቆጣጠር ስራ:: 2. ኪላ::

**ፈተተ** ግ ቆረሰ፥ ገመሰ (ሁበስትን፥ ዛቲን)::

**ተፋተተ** ግ እየቆረሰ ወይም እየገመሰ ተከፋፈለ::

**አፋተተ** ግ እየቆረሰ ወይም እየገመሰ አካፈለ::

**ፈተነ** ግ 1. ጠየቀ፥ ፈተና ሰጠ:: 2. ሞከረ፥ ፈተሸ:: 3. መረመረ:: *ወርቅ በእሳት ይፈተናል::*

**ፈተና** ስ 1. አንድ ሰው ስለአንድ የተወሰነ ነገር ማወቅ አለማወቁን ለመገንዘብ በፅሁፍ፥ በቃል ወይም በተግባር እንዲያሳይ የሚቀርብ ጥያቄ:: 2. ችግር፥ መከራ፥ ስቃይ::*ያልታሰበ ፈተና ገጠመው::*

**ፈተና ወሰደ** ስለአንድ የተወሰነ ነገር ማወቅ አለማወቁን በፅሁፍ፥ በቃል ወይም በተግባር እንዲያሳይ ተደረገ::

**ፈተናውን ደፈነ** የተሰጠውን የፈተና ጥያቄ ሙሉ በሙሉ መለሰ::

**የፈተና ወረቀት** ስ ለፈተና ተብሎ የተዘጋጀ ጥያቄ የተፃፈበት ወረቀት::

**ፈታኝ** ቅ 1. በጣም አስቸጋሪ፥ አድካሚ፥ የሞት ሽረት ትግል ያለበት(ሁኔታ፥ ወቅት፥...): *ፈታኝ ወቅት ላይ ነኝ::* 2. የፈተና ጥያቄዎችን ለተፈታኝ የሚያቀርብ ወይም በፈተናው ወቅት ተፈታኞችን የሚቆጣጠር (ሰው)::

**ፍቱን** ቅ ፈዋሽነቱ ተሞክሮ የተረጋገጠ፥ የታወቀ::*ፍቱን መድሃኒት::*

**ተፈተነ** ግ የችግር፥ የመከራ፥ የስቃይ ጊዜ አሳለፈ::

**የተፈተነ** ቅ ተመርምሮ፥ ተፈትሾ ጥራቱ ወይም ብቃቱ የታየ::

**ተፈታኝ** ቅ 1.ስለአንድ የተወሰነ ነገር ማወቅ አለማወቁን ለማረጋገጥ በፅሁፍ፥ በቃል ወይም በተግባር ሊጠየቅ የቀረበ (ሰው)::

**ተፈታተነ** ግ 1. ታገለ፥ ተከታተለ (በነገር፥ በተንኮል):: 2. አጓጓ፥ አማረ፥ አሰኘ (ለማሳሳት፥ ችግር ላይ ለመጣል)::

**ተፈታታኝ** ቅ በክፉ ነገር የሚከታተል:: 2. የሚያጓጓ፥ የሚያሰኝ (ስህተት ውስጥ ለማስገባት)::

**ፈተገ** ግ 1. ገብስን፥ ስንዴን፥... በውሃ እያራሰ ገለፈቱ እንዲለቅ ወቀጠ፥ ሸከሸከ:: 2. በሃይል አሸ:: 3. ቆዳን አለፋ፥ ዠለጠ:: 4. ፈገፈገ፥ ሳጠ:: *እግሬን ድንጋይ ፈተገኝ::* 5. ራበ ሞረሞረ::*ረሃብ ፈተገኝ::*

**ፍትግ** ቅ ተወቅጦ ገለፈቱ የለቀቀ (ገብስ፥ ስንዴ፥...)::

**ተፈታተገ** ግ ተመላለጠ፥ ተገጣጠበ (ሰውነት)::

**ተፋተገ** ግ 1. ተላፋ፥ ታገለ:: 2. ተፈጋፈገ፥ ተሻሸ:: 3. (ዘይ.)ተፋጨ፥ ተከራከረ (በተለያየ ሃሳብ፥ አመለካከት)::

**አፋተገ** ግ 1. አላፋ፥ አታገለ:: 2. አፈጋፈገ፥ አስተሻሸ:: 3. አፋጨ፥ አከራከረ::

**ፈተፈተ** ግ 1. እንጀራን ወይም ዳቦን፥... ወጥ፥ መረቅ፥...ውስጥ ቆራርሶ በመጨመር ፈረፈረ:: 2. (ዘይ.) በማያገባው ጉዳይ ገብቶ ነገር አቦካ:: 3. የመነዝነዝ ወይም የመጠዝጠዝ አይነት ህመም ተሰማ::

**ፈትፍቶ አጎረሰ** ጥሩ፥ አመቺ አድርጎ ወይም አሳምሮ ሰጠ፥ አቀረበ (ለምሳሌ ትምህርትን)::

**ፈትፋች** ቅ በሰው ጉዳይ ውስጥ ገብቶ ቀና ያልሆነ ሃሳብ የሚሰጥ፥ ነገረኛ፥ ወስዋሳ::

**ፍትፍት** ስ 1. እንጀራን ቆራርሶ በስጋ መረቅ ወይም ማባያ ሊሆን በሚችልና ፈሳሽነት ባለው ሌላ ነገር ውስጥ ጨምሮ በመለወስ የሚዘጋጅ ምግብ::2. (ዝይ.) ቀላል፥ የማያስቸግር::

**ከፍትፍቱ ፊቱ** አቀባበልና ፈገግታ ከማንኛውም ስጦታ ወይም ግብዣ ይበልጣል

ለማለት የሚነገር አባባል።

**ፈታ** ግ 1. የታሰረ፥ የተቋጠረ፥ የተያያዘን ነገር አላቀቀ፥ አለያየ።2. የታሰረበትን አወለቀ፥ በጠሰ። *ውሻው ፈትቶ ጠፋ።* 3. ትዳሩን አፈረሰ፤ ከሚስቱ ተለያየ። 4. ከእስር ቤት አስወጣ፥ ነፃ ለቀቀ። 5. አጠፋ፥ አፈረሰ፥ አወከ፥ በተነ።*አገር ፈታ።* 6. አሸነፈ፥ ድል አደረገ። *ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው ይበልጣል።* 7. ለሞተ ሰው የፍታት ፀሎት አደረገ። 8. የገዘተውን ተወ፥ ሻረ፥ ግዝቱን አነሳ።9. ገደፈ።*ፆም ፈታ።* 10. ተረጎመ፥ ገለጠ፥ አብራራ፥ ፍቺ ሰጠ። 11. አቃለለ፥ መፍትሄ ሰጠ።*ችግሩን በቀላሉ ፈታው።*

**መፍትሄ** ስ የችግር ማቃለያ፥ ማስወገጃ ዘዴ ወይም መንገድ።

**ፈት** ቅ አግብታ የፈታች (ሴት)።

**ፍታት** ስ ለሞተ ሰው የሚፀለይ ፀሎት።

**ፍቺ** ስ 1. የትዳር ወይም የጋብቻ መፍረስ፥ መፋታት። 2. ትርጉም።

**ፈታ አለ** ግ ቀልጠፍ፥ ፈጠን፥ ዘና አለ (ለንግግር፥ ለስራ)።

**ተፈታ** ግ 1. የታሰረው፥ የተቋጠረው፥ የተያያዘው ተላቀቀ፥ ተለያየ። 2. *ፆሙ* አብቅቶ ፍስክ ሆነ። 3. የተሰበሰበው ተበተነ።*ገበያው ተፈታ።*

**ተፈታታ** ግ ተላቀቀ፥ ተለያየ (የተቋጠረው፥ የተያያዘው)።

**ተፋታ** ግ ከሚስቱ ተለያየ፥ ትዳሩን አፈረሰ።

**ተፍታታ** ግ 1. ተቆጣጥሮ ወይም ተተብትቦ የነበረ ነገር ተነጣጠለ፥ ተለያየ። 2. እስርስር ብሎ የነበረው ሰውነት ዘና አለ፥ ተዝናና።3. ተብራራ(ሃሳብ)።

**አፈታ** ግ በብዛት ወረደ፥ ፈሰሰ (ደም)።*ደም አፈታት።*

**አፋታ** ግ ባልና ሚስትን አለያየ።

**አፍታታ** ግ 1. ተቆጣጥሮ ወይም ተተብትቦ የነበረን ነገር አነጣጠለ፥ አለያየ።2. እስርስር ብሎ የነበረውን ዘና አደረገ፥ አዝናና (ሰውነትን በስፖርት)። 3. አብራራ (ሃሳብን)።

**ፈታላ** "ፈተለ[2]" ስር ተመ.

**ፈታሽ** " ፈተሸ" ስር ተመ.

**ፈታኝ** "ፈተነ" ስር ተመ.

**ፈታይ** "ፈተለ[1]" ስር ተመ.

**ፈት** " ፈታ" ስር ተመ.

**ፈትል** " ፈተለ[1]" ስር ተመ.

**ፈትፋች** " ፈተፈተ" ስር ተመ.

**ፈቸል** ስ የተጣበቀ ወይም የተቸነከረ ነገርን ለመንቀል የሚያገለግል መንቀያ፤ ጉጠት።

**ፈነቀለ** ግ 1. የተጣበቀ፥ የተተከለ ነገርን ከስሩ ነቀለ፥ አወጣ፥ አፈለሰ። 2. ከፍተኛ የሆነ የሳቅ፥ የደስታ፥ የለቅሶ፥... ስሜት ከውስጥ አሸንፎ ወጣ።*ሳቅ ፈነቀለው።* 3. አፈናቀለ።

**መፈንቅለ መንግስት** ስ የአንድ አገር ህገመንግስት ከሚፈቅደው ውጪ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በአመፅ የሚያካሂዱት መንግስትን የመቀየር ተግባር፤ መንግስት ግልበጣ፤ ኩዴታ።

**ተፈነቀለ** ግ ፈለሰ፥ ወጣ፥ ተነቀለ።

**ተፈናቀለ** ግ ከመኖሪያ ቦታው ለቅቆ ወደ ሌላ ቦታ ለመኖር ሄደ (በጦርነት፥ በድርቅ፥... ምክንያት)።

**ተፈናቃይ** ቅ ከመኖሪያ ቦታው ለቅቆ ወደ ሌላ ቦታ ለመኖር የሄደ(በጦርነት፥ በድርቅ፥... የተነሳ)።

**አፈናቀለ** ግ ከመኖሪያው፥ ከስራው፥ ከትዳሩ አባረረ፥ አስወገደ።

**ፈነቸረ** ግ 1. ገደለ። 2. ጣለ፥ ዘረረ።

**ተፈነቸረ** ግ 1. ወደቀ። 2. ሞተ።

**ፈነከረ** ግ በጣም ከፈተ፥ በለቀጠ፤ ወዲያና ወዲህ ዘረጋ (ለምሳሌ ጭንና ጭንን)

**ፈንካራ** ቅ (ስድብ) ጉያዋን የማትከልል፤ ጭኗን ከፍታ የምትቀመጥ።

**ፈነከተ** ግ 1. ጭንቅላትን ተረከከ፥ መታ። 2. ከፈለ፥ ገመሰ። 3.ፈረከሰ፥ አደቀቀ።

**ፍንካች** ቅ ከአንድ ነገር ላይ ተከፍሎ ወይም ተፈንክቶ የወጣ፤ ክፋይ።

**ፍንክት** ቅ የተገመሰ፥ የተፈነከተ፤ ስንጥቅ።

***ፈነደረ**

**ፈንዳራ** ቅ ቂጡ ወደ ሂላ ያፈነደደ፥ ያፈነገጠ።

**ፍንድር አለ** ግ አፈነደረ።

**አፈነደረ** ግ ከወደ ሂላ ወጣ አለ፥ አፈነገጠ (ቂጥ ወይም ሌላ ነገር)።

***ፈነደሰ[1]**

**ፈንዳሳ** ቅ ድንቡሽቡሽ ያለ ወፍራም።

**ፍንድስ አለ** ግ ተፈነደሰ።

**ተፈነደሰ** ግ ተጋደመ፥ ተኛ (ብዙውን ጊዜ ወፍራም ሰው)።

***ፈነደሰ[2]**

**ፍንድስድስ አለ** ግ 1. ፍርክስክስ፥ ስንጥቅጥቅ አለ (የተቀቀለ ድንች፥ ንፍሮ፥...)። 2. ብዙ ቦታ ላይ ፈነዳ (ቁስል)።

**ተፈነዳደሰ** ግ ዝ.ክ.

**ፈነደቀ** ግ ተደሰተ፥ ቦረቀ፥ ፈነጨ።

***ፈነደደ**

**ፈንዳዳ** ቅ (ስድብ) ከወገቡ ሰበር ብሎ ቂጡ ያፈነደረ::

**ፍንድድ** ቅ ጉንብስ::

**ፈንደድ አለ** ግ 1. አፈነደረ (ቂጥ):: 2. መቀመጫውን ወደ ሂላ በማፈንደር አጎነበሰ::

**ፍንድድ አለ** ዝ.ከ.

**አፈነደደ** ግ 1. አፈነደረ (ቂጥ):: 2. አጎነበሰ::

**ፈነዳ** ግ 1. ዷ አለ፥ ጮሀ:: 2. ፈካ:: *አበባው ፈነዳ::* 3. ተተረተረ፥ ተሰነጠቀ (እንስራ፥ ኳስ፥ ጎማ፥...):: 4. ፈረጠ፥ መገለ:: *ቁስሉ ፈነዳ::* 5. ይፋ ወጣ፥ ተገለጠ፥ በሁሉም ቦታ ተከሰተ::*አብዮት ፈነዳ/ ተደብቆ የቆየው ምስጢር ፈነዳ::* 6. ሲቆላ ፈካ (ፈንድሻ)::

**ፈንድሻ** ስ ሲቆሉት የሚፈካ የማሽላ አይነት፥ አበባ ቆሎ::

**ፈንጂ** ስ የሚፈነዳ የጦር መሳሪያ፥ ቦምብ::

**ፈንጂ ቀበረ** ፈንድቶ ጉዳት እንዲያደርስ ፈንጂን መሬት ውስጥ ወይም በስውር አስቀመጠ::

**ፍንዳታ** ስ 1. እንደ ቦምብ፥ ድማሚት፥... ያሉ ነገሮች መፈንዳት:: 2. እንደ ቦንብ፥ ድማሚት ያሉ ነገሮች ሲፈነዱ የሚያሰሙት ድምፅ ወይም ጩሀት::

**ፍንድ** ስ ከቅርፊቱ ተላቅቆ የሚወጣ የጥጥ ጓል::

**ፈነገለ**[1] ግ ገፍቶ ወይም ገፍትሮ ጣለ::

**ፈንጋላ** ቅ ተስተካክሎ ወይም ተደላድሎ የማይቀመጥና በቀላሉ የሚፈነገል::

**ፈንግል** ስ በቶሎ የሚገድል የዶሮ በሽታ::

**ፍንግል አለ** ግ ተፈነገለ::

**ተፈነገለ** ግ 1. ወደቀ፥ ክንብል አለ:: 2. (ዘይ.)ሞተ::

**ፈነገለ**[2] ግ (ባሪያን) አፍኖ ሸጠ::

**ፈንጋይ** " ባርያ" ስር "ባርያ ፈንጋይ"ን ተመ.

***ፈነገጠ**

**አፈነገጠ** ግ 1. የነበረበትን ቦታ፥ መስመር፥... ለቀቀ:: 2. ከፓርቲው፥ ከቡድኑ፥... ተለየ::

**አፈንጋጭ** ስ በአመለካከቱ፥ በፖለቲካ አቋሙ ከፓርቲው፥ ከቡድኑ፥ .. ተለይቶ ለብቻው የሆነ፥ ተቃዋሚ፥ አንጃ::

***ፈነጠረ**

**ፈንጣራ** ቅ ገለልተኛ፥ ብቸኛ፥ ከሌላው ራቅ ያለ::

**ፍንጣሪ** ቅ ተፈናጥሮ ወይም ተወርውሮ የወጣ የአንድ ነገር ሽራፊ::*የእሳት ፍንጣሪ::*

**ፈንጠር አለ** ግ ገለል አለ ወይም ራቅ አለ::*ፈንጠር ብሎ ቆሟል::*

**ፍንጥርጥር አለ** ግ እየተፈናጠረ ብትንትን አለ::

**ተፈነጠረ** ግ ተፈናጠረ::

**ተፈነጣጠረ** ግ ተፈናጥሮ ተበታተነ፥ ተረጨ::

**ተፈናጠረ** ግ 1. ዘለለ፥ እንጣጥ አለ:: 2. ተወረወረ::*ድንጋዩ ተፈናጥሮ መታው/ የፈላ ዘይት ተፈናጥሮ አቃጠለኝ::*

**ተስፈነጠረ** ግ ተፈናጠረ::

**ተስፈንጣሪ** ቅ 1. ተወርዋሪ:: 2. (ፖለ.) ግራ አክራሪ::

**አፈናጠረ** ግ ወረወረ፥ አሽቀነጠረ::

**አስፈነጠረ** ዝ.ከ.

**ፈነጠቀ** ግ 1. ወጣ፥ አበራ (ፀሃይ):: *ፀሃይ ፈነጠቀች::* 2. ደፋ፥ አፈሰሰ (ውሃን):: *ውሃውን ፈንጥቀው::* 3. ረጨ፥ በተነ:: 4. ሙሉ ከነበረው ፈሳሽ ላይ በትንሹ አፈሰሰ፥ ቡልቅ አደረገ:: 5. አልፎ አልፎ ጣል ጣል አለበት (ለቀለም፥ ለጌጥ)::*ነጭ የፈነጠቀበት ቀሚስ::*

**ፍንጣቂ** ቅ የተፈናጠቀ ወይም የተረጨ ጠብታ::

**ተፈናጠቀ** ግ ተረጨ::

**አፈናጠቀ** ግ ረጨ፥ አርከፈከፈ::

**ፈነጠዘ** ግ በደስታ በረቀ፥ ዘለለ፥ ጨፈረ::

**ፈንጠዝያ** ስ ደስታ፥ ቡረቃ፥ ጭፈራ::

***ፈነጠጠ**

**ተፈናጠጠ** ግ በበቅሎ፥ በፈረስ፥ ... ጀርባ ላይ ወይም በብስክሌት፥ በሞተር ሳይክል ላይ ከሚጋልበው ሰው ጋር በመደረብ ከበስተሂላው ተቀመጠ::

**ተፈናጣጭ** ቅ በበቅሎ፥ በብስክሌት፥.. ላይ ዋናውን ጋላቢ ተጠግቶ በስተሂላው በኩል በመቀመጥ አብሮ የሚጋልብ (ሰው)::

**አፈናጠጠ** ግ በበቅሎ፥ በፈረስ፥... ጀርባ ላይ ወይም በብስክሌት፥ በሞተር ሳይክል ላይ የሚጋልብ ሰው በስተሂላው በኩል ሌላ ሰው ደርቦ ጫነ::

**ፈነጨ** ግ 1. ዘለለ፥ በረቀ:: 2. በጣም ተደሰተ፥ ፈነደቀ::

**ፈነጨበት** (በንዴት፥ በቁጣ) ብዙ ተናገረው::

***ፈነፈነ**

**መፈናፈኛ** ቅ መንቀሳቀሻ፥ መላወሻ:: *ክፍሉ መፈናፈኛ የለውም፥ ጠባብ ነው::*

**ተፈናፈነ** ግ ወዲያ ወዲህ አለ፥ ተንቀሳቀሰ፥

ተጠጋጋ፡፡

**አፈናፈነ** ግ እንዲንቀሳቀስ፥ ወዲያ ወዲህ እንዲል አደረገ (ብዙውን ጊዜ በአገልግሎት ላይ የሚውለው በአፍራሽ ቅርፁ ነው)፡፡*የስራው ብዛት ላላፈናፍን ላለው፡፡*

**ፈንታ** "ፋንታ"ን ተመ.

**ፈንዜ** ስ ቀጠን ብሎ ጎበጥ ያለ የጎራዴ አይነት

**ፈንዳራ** "*ፈነደረ" ስር ተመ.

**ፈንዳሳ** "*ፈነደሰ[1]" ስር ተመ.

**ፈንዳዳ** "*ፈነደደ" ስር ተመ.

**ፈንድሻ** "ፈነዳ" ስር ተመ.

**ፈንጂ** ዝ.ከ.

**ፈንጋላ** "ፈነገለ[1]" ስር ተመ.

**ፈንጋይ** "ፈነገለ[2]" ስር ተመ.

**ፈንግል** "ፈነገለ[1]" ስር ተመ.

**ፈንጠዝያ** "ፈነጠዘ" ስር ተመ.

**ፈንጣራ** "*ፈነጠረ" ስር ተመ.

**ፈንጣጣ** ስ በሰውነት ላይ እንደ እከክ ሆኖ የሚወጣና ጠባሳ የሚተው ተላላፊ በሽታ፡፡

**ፈከረ** "ፎከረ" ን ተመ.

**ፈካ** ግ 1. እንደ ፈንድሻ ያለ እህል ሲቆላ እንደ አበባ ፈነዳ፡፡ 2. አበበ፥ ፈነዳ(አበባ)፡፡ 3. በፊቱ ላይ ደስታ ታዬ፥ ፈገግ አለ፡፡ *ፊቱ ፈካ* ፡፡

**ፈካ አለ** ግ በፊቱ ላይ ደስታ ታየ፥ ፈገግ አለ፡፡

**ፈካ ያለ** ብሩህ የሆነ ወይም ያልደመቀ፡፡ *ፈካ ያለ ሰማያዊ (ቀለም)* ፡፡

**ፈወሰ** ግ አዳነ፥ አሻረ፡፡

**ፈዋሽ** ቅ 1. አዳኝ፡፡ *ኢየሱስ ፈዋሽ ነው* ፡፡ 2. ፈውስ የሚሰጥ፥ የሚያድን፡፡

**ፈውስ** ስ ከበሽታ መዳን፥ ደህንነት፡፡

**ተፈወሰ** ግ ዳነ፥ ፈውስ አገኘ፡፡

**ፈዘዘ** ግ 1. ድምቀት አጣ፥ ደበዘዘ (ቀለም)፡፡ 2. ሃይሉን ቀነሰ፥ ደበዘዘ፡፡ 3. ነቃ አልል አለ፥ ናበዘ፥ በዘ፡፡

**ፈዛዛ (ፍዝ)** ቅ 1. ደማቅ ያልሆነ፥ ደብዛዛ (ቀለም)፡፡ 2. ነቃ ነቃ የማይል፥ ናባዛ፡፡

**አፈዘዘ** ግ 1. አደነዘዘ፥ አነሆለለ፡፡ *በመድሃኒት አፈዘዘው፡፡* 2. በጣም አስደነቀ፥ አስገረመ፥ ስሜትን ማረከ፡፡

**አፍዝ አደንግዝ** ስ ያፈዛል ወይም ያነሆልላል ተብሎ የሚታመንበት የአስማት አይነት ወይም መተት፡፡

**ፈየደ** ግ ጠቀመ፥ ረባ፡፡

**ፋይዳ** ስ ጥቅም፥ እርባና፡፡

**ፈደፈደ** ግ ያዘ፥ አሰቃየ (ረሃብ፥ ብርድ)፡፡

**ፈጀ[1]** ግ አቃጠለ፥ ለበለበ፡፡

**ተፋጀ** ግ አቃጠለ፥ ለበለበ፡፡

**ፈጀ[2]** ግ 1. ጨረሰ፥ ፈፅሞ አጠፋ፡፡ *ሳዲሉ በሽታ ሰውን ሁሉ ፈጀ፡፡* 2. ያዘ፥ ቻለ፡፡ *እንስራው ሃያ ሊትር ውሃ ይፈጃል፡፡* 3. አወጣ፥ ወሰደ፡፡ *ሹራቡ 100 ብር ፈጅቷል፡፡*

**ፍጅት** ስ 1. እርስ በርስ መጫረስ፥ መተላለቅ፡፡ 2. ጭቅጭቅ፥ ውዝግብ፡፡

**ፍጆታ** ስ 1. በተወሰነ ጊዜ የሚያልቀው ወይም ጥቅም ላይ የሚውለው መጠን፡፡ 2. የንግግር ተራ ወይም ፋንታ፡፡

**ተፋጀ** ግ 1. ተጫረሰ፥ ተላለቀ፥ ተጋደለ፡፡ 2. ተጨቃጨቀ፥ ተነታረከ፡፡

**አፋጀ** ግ 1. አጨቃጨቀ፥ አነታረከ፡፡ 2. አጋደለ፥ አጨራረሰ፡፡

**ፈገመ** ግ 1. ወደቀ፥ ተደፋ፡፡ 2. ሞተ፡፡

**ፍግም አለ** ግ 1. በግንባሩ ወይም ባፍጢሙ ወደቀ፤ ድፍት አለ፡፡ 2. ሞተ፡፡

***ፈገመገመ**

**ፍግምግም** ቅ ሲሄድ የሚንገዳገድ፡፡

**ተፍገመገመ** ግ ተውተረተረ፥ ተንገዳገደ፡፡

**አፍገመገመ** ግ አውተረተረ፥አንገዳገደ፡፡

**ፈገረ** "ፎገረ"ን ተመ

**ፈገገ** ግ ፈካ፥ በራ፡፡

**ፈገግታ** ስ ሳቅ በማለት በፊት ላይ የሚታይ የደስታ ስሜት፡፡

**ፈገግ አለ** ግ 1. ሳቅ በማለት ደስታውን፥ አድናቆቱን፥... ገለፀ፡፡ 2. ጥቁረቱ ቀነሰ፥ ቀላ አለ (ለቆዳ ቀለም)፡፡ 3. ነጣ ወይም ፈካ አለ (ቀለም ወይም የቆሸሸ ልብስ ሲታጠብ)፡፡

**ፍግግ ፍግግ አለ** ግ ሳቅ ሳቅ አለ (ህፃን)፡፡

**ፈገፈገ** ግ 1. አሸ፥ ወለወለ (ለማፅዳት)፡፡ 2. ፋቀ፥ ፈቀፈቀ፡፡

**ተፈገፈገ** ግ ተሳሳጠ፥ ተፋቀ፡፡

**ተፈጋፈገ** ግ አንድ አካል ከሌላው ጋር በሃይል ተሻሸ፡፡

**ፈጋራ** ስ ሬብ፥ የኩስ መውጫ፡፡

**ፈግጠው** ተወው፥ የራስህ ጉዳይ፥ እንደፈለግህ፡፡ *ፈግጠው ፈግጭው ተባባሉ፡፡*

***ፈጠመ**

**ፍጥምጥም(ፍጥጥም)** ስ የጋብቻ ውል ወይም ፊርማ (በተጨማሪ የቀለበትን 3ኛ ፍቺ ተመ.)፡፡

**ተፈጠመ** ግ በህግ የተጠየቀውን ወይም

አድርግ የተባለውን ለመፈፀም ቃል ሰጠ፥ ግዴታ ገባ::

**ተፈጣጠመ** ግ ተዋዋለ ወይም ተፈራረመ (ለጋብቻ)::

**አፈጣጠመ** ግ አዋዋለ ወይም አፈራረመ (ለጋብቻ)::

**ፈጠረ**[1] ግ 1. አስገኘ፥ ሰራ:: *እግዚአብሄር በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን ፈጠረ* :: 2.ዋሸ፥ ያልሆነ ወይም ያልተደረገ ነገር ተናገረ::*ፈጥሮ ያወራል::* 3.ወለደ::*እናቴ ከፈጠረችኝ ጀምሮ እንደዚህ አይነት ነገር አላየሁም::* 4.አደረገ፥ ሰራ::*ምን ፍጠር ነው የምትለኝ?*

**ፈጠራ** ስ 1. በምርምር፥ በሙከራ፥... የሚገኝ የእውቀት ውጤት የሆነ አዲስ ነገር:: 2. ከአእምሮ በማመንጨት የሚሰራ የልብ ወለድ ወይም ስነጥበባዊ ስራ::*የፈጠራ ፅሁፍ::* 3. ውሸት:: *የፈጠራ ወሬ::*

**ፈጣሪ** ስ እግዚአብሄር::

**ፍጡር** ስ በምድር ላይ የሚኖር ሰው ወይም እንስሳ::

**ፍጥረት** ስ 1. በምድርና በሰማይ ያለ ማንኛውም ነገር:: 2. ፍጡር:: 3. አፈጣጠር፥ ተፈጥሮ:: 4.ልጅ:: *ስንት ፍጥረቶች አሉህ ?*

**እንደፍጥርጥሩ** እንደፈለገ፥ እንዳሻው::

**ተፈጠረ** ግ 1. ያልነበረ ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ ተሰራ:: 2. ሆነ፥ መጣ፥ ተከሰተ:: *በመካከላቸው ቅራኔ ተፈጠረ::*

**ተፈጥሮ** ስ 1. የአንድ ነገር መለያ፥ ባህርይ፥ ጠባይ፥ ሁኔታ፥ አሰራር፤ አፈጣጠር:: 2. እንደ ተራራ፥ ወንዝ፥... ያለ ሰው ሰራሽ ያልሆነ ነገር::*ተፈጥሮን ማድነቅ ይወዳል::*

**የተፈጥሮ** ቅ ሰው ሰራሽ በሆነ መንገድ ያልተገኘ፥ ያልተሰራ፥ ያልተፈጠረ::

**የተፈጥሮ ሃብት** ስ በተፈጥሮ የሚገኝና በጥቅም ላይ የሚውል እንደ ውሃ፥ ማእድን፥ ነዳጅ፥... የመሳሰለው ነገር::

**የተፈጥሮ ህግ** ስ በአለም ላይ ያለ ማንኛውም ነገር በተፈጥሮ ባህርዩ የሚያከናውነውና እያንዳንዱ የሚመራበት ተፈጥሮአዊ ስርአት (እንደመብላት፥ መጠጣት፥ መወለድ፥ መሞት፤ መምሸት፥ መንጋት፤ የወራት መለዋወጥ፥...ያለ)::

**አፈጣጠር** የ "**ተፈጥሮ**"ን 1ኛ ፍቺ ተመ..

**ፈጠረ**[2] ግ በእግር ኳስ አጨዋወት ላይ ኳስን ወዲያ ወዲህ እያንከባለለ አታለለ::

**ፈጠራ** ስ በእግር ኳስ ጨዋታ ላይ ኳስን ይዞ ለማለፍ ወይም ላለመነጠቅ ወዲያና ወዲህ በማንከባለል እያታለሉ የመጫወት ዘዴ ወይም ቴክኒክ::

**ፈጠረቀ** ግ 1. አንድን ነገር አንቆ፥ አጥብቆ፥ ጨምቆ ያዘ:: 2. አፈነዳ፥ አፈረጠ:: 3. ፈነከተ፥ ተረተረ:: *ግንባሩን በዱላ ፈጠረቀው::* 4. በሃይል ወርውሮ ጣለ::

**ፈጥርቆ ያዘ** 1. አስገድዶ፥ አስጨንቆ ያዘ:: 2. ወጥሮ፥ አጣብቆ ያዘ::

**ተፈጠረቀ** ግ 1. ፈነዳ፥ ፈረጠ:: 2. ወደቀ፥ ተፈጠፈጠ::

**ፈጠራ**[1] "**ፈጠረ**[1]" ስር ተመ.

**ፈጠራ**[2] "**ፈጠረ**[2]" ስር ተመ.

**ፈጠነ** ግ 1. ቸኮለ፥ ቀለጠፈ:: 2. ቶሎ ሆነ::

**ፈጥኖ ደራሽ** ቅ 1. በችግር ጊዜ ቶሎ ለእርዳታ የሚደርስ (ሰው፥ መልአክ፥ ...):: ስ 2. ችግር በተፈጠረበት ወይም ፀጥታ በሚደፈርስበት ቦታ ሁኔታውን ለማረጋጋት ወይም ለመቆጣጠር ቶሎ በቦታው የሚገኝ ወታደራዊ ክፍል::

**ፈጣን** ቅ 1. ቀልጣፋ:: 2. ቶሎ የሚደርስ፥ ብዙ ጊዜ የማይፈጅ::3. ቶሎ የመገንዘብ፥ የመረዳት፥... ችሎታ ያለው፤ ንቁ::

**ፍጥነት** ስ 1. በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የአንድ ጉዳይ ቶሎ የመፈፀሙ መጠን፥ ልክ:: 2. ቅልጥፍና:: 3. ችኮላ፥ ጥድፊያ::

**ተፋጠነ** ግ በቶሎ ወይም ሳይዘገይ ተከናወነ::

**አፈጠነ** ግ 1. ቀለጠፈ፥ በፍጥነት፥ ሳይዘገይ፥ በቶሎ አከናወነ::2. በፍጥነት የሚከናወን አይነት ሆነ፥ ቀለለ:: *ስራው አፈጠነኝ::*

**አፋጠነ** ግ 1. ቶሎ፥ ሳይዘገይ ወዲያውኑ አከናወነ:: 2. አጣደፈ::

**አፋጣኝ** ቅ አስቸኳይ፥ አጣዳፊ::

**ፈጠጠ** ግ 1. ጎረጠ፥ ተጎለጎለ (አይን):: 2. በደንብ ወደ ውስጥ ካለመግባት፥ ካለመቀላቀል፥ካለመብሰል፥ ... የተነሳ ወደ ውጪ ወጣ፥ ጎላ ብሎ ታየ::*የተዘራው ዘር ፈጦ ታየ /ወጡ ውስጥ ያለው ሽንኩርት ፈጦ ታየ::*

**ፈጠጤ** ስ 1. እህል ተዘርቶ አፈር ሳይለብስ በመቅረቱ ከላይ ሆኖ የሚታይ ዘር:: 2. ፈጣጣ (ለአይን)::

**ፈጣጣ** ቅ አይኑ የፈጠጠ ወይም አይኑ ወጣ ወጣ ብሎ የሚታይ::

**ተፋጠጠ** ግ ፊት ለፊት ተገጣጠመ፤ በመፈራራት፥ በጥላቻ፥ በጠላትነት ተያየ ::

**አፈጠጠ** ግ 1. ትክ ብሎ ወይም አትኩሮ ተመለከተ:: 2. አይኑን ጎለጎለ፥ አጉረጠረጠ::3. ቀላወጠ፥ ከጀለ:: 4. ተቆጣ፥ ጥል ፈለገ:: 5. ጉልህ፥ ግልፅ ሆኖ ታየ::

**አፍጣጭ** ቅ ቀላዋጭ::

**ያፍጣጭ** ስ ለቀላዋጭ ሰው የሚሰጥ ምግብ ወይም ጉርሻ::

**አፋጠጠ** ግ አስጨነቀ፥ ወጥሮ ያዘ።

**ፈጠፈጠ** ግ 1. ፈነከተ፥ ፈረከሰ (ብዙውን ጊዜ ጭንቅላትን)። 2. ጣለ፥ አፈረጠ።

**ተፈጠፈጠ** ግ 1. ተፈነከተ፥ ተፈረከሰ። 2. ወደቀ፥ ፈረጠ።

**ፈጣሪ** "**ፈጠረ**[1]" ስር ተመ.

**ፈጣን** "**ፈጠነ**" ስር ተመ.

**ፈጣጣ** "**ፈጠጠ**" ስር ተመ.

**ፈጨ** ግ 1. አደቀቀ፥ ሰለቀ። 2. ጨፈለቀ፥ ጻጠ። 3. አብዛቶ አደረገ፥ ፈፀመ፥ ... ። *ወሬውን ሲፈጭ አመሸ/ ያን ሁሉ መንገድ በእግሬ ፈጨሁት።*

**ወፍጮ** ስ በፊደል ተራው ተመ.

**ፈጪ (ፈጪይ፥ ፈጭታ)** ስ በመፍጨት ስራ የምትተዳደር ሴት።

**የፈጪይ** ስ በመፍጨት ስራ ለምትተዳደር ሴት የሚከፈላት የጉልበት ዋጋ።

**ፍጩ** ስ የተፈጨው ዱቄት።

**ተፋጨ** ግ 1. ተፋተገ፥ ተፈጋፈገ (ለቢላዋ)። 2. ተጨቃጨቀ፥ ተከራከረ።

***ፈጨረጨረ**

**ተፍጨረጨረ** ግ ለፋ፥ ተጣጣረ።

**ተፍጨርጫሪ** ቅ ታታሪ።

**አፍጨረጨረ** ግ 1. እንዲጣጣር፥ እንዲፍጨረጨር አደረገ። 2. አለፋ፥ አጣጣረ።

***ፈጨጨ**

**ፍጭጭ አለ** ግ በጥቂቱ ወጣ፥ ፈሰሰ (ለምሳሌ መግልና እዥ)።

***ፈጨፈጨ**

**ፈጨፈጭ** ቅ የወረዛ ወይም ውሃ የቋጠረ (መሬት)።

**ፈጭፋጫ** የሚያስቀዝነው ወይም የሚያስቀምጠው።

**ተንፈጨፈጨ** ግ 1. ረጠበ፥ ወረዛ፥ ጨቀየ። 2.ቀዘነ። 3. እርጥብ እንጨት ሲነድ አረፋ መሳይ ነገር በማውጣት ቻስ አለ።

**አንፈጨፈጨ** ግ አስቀዘነ።

**ፈጪ** "**ፈጨ**" ስር ተመ.

**ፈጫ** ስ በወንዝ ወይም በጅረት ዳር የሚገኝ አሸዋ ወይም ጠጠር።

**ፈጫይ** "**ፈጨ**" ስር "**ፈጪ**"ን ተመ.

**ፈጭታ** ዝ.ከ.

**ፈጭፋጫ** "**ፈጨፈጨ**" ስር ተመ.

**ፈፀመ** ግ 1. ጨረሰ፥ አጠናቀቀ። 2. ስራ፥ አደረገ፥ አከናወነ።*ወንጀል ፈፀመ።*

**ፈፅሞ** ተው.ግ. ጭራሽ፥ ጨርሶ።*እቃው መኖሩን ፈፅሞ አላየሁም።*

**ፍፁም** ቅ 1. ፈፅሞ። 2. ምንም እንከን ወይም ጉድለት ወይም ስህተት የሌለው። 3. የበቃ፥ ፃድቅነት ደረጃ የደረሰ።*በገዳሙ ውስጥ አንድ ፍፁም ባህታዊ ነበሩ።*

**በፍፁም** ተው.ግ. በጭራሽ።

**ፍፁም ቅጣት ምት** ስ (ስፖ.) የፍፁም ቅጣት ክልል ተብሎ በተወሰነው አካባቢ ጥፋት ሲፈፀም ለተቃራኒው ቡድን የሚሰጥ የቅጣት ምት።

**ፍፃሜ** ስ መጨረሻ፥ ማለቂያ፥ ማከተሚያ፥ መደምደሚያ።

**ተፈፀመ** ግ 1.አለቀ፥ ተጠናቀቀ፥ አበቃ። 2. ተሰራ፥ ተከናወነ።

**ተፈፃሚ** ቅ 1. ተግባራዊ። *መመሪያው ተፈፃሚ ሊሆን አልቻለም።* 2. ተግባራዊ የሚሆን።

**አስፈፀመ** ግ አስጨረሰ፥ ፍፃሜ እንዲያገኝ አደረገ።

**አስፈፃሚ** ቅ 1. አንድ ስራ በተገቢው ሁኔታ መካሄዱን የሚከታተልና የሚቆጣጠር።ስ 2. አንድን ህግ፥ መመሪያ፥ ጉዳይ፥... ተግባራዊ የሚያደርግ ወይም የሚያስደርግ ክፍል ወይም አካል። *ጉዳዩን ህግ አስፈፃሚው አካል ይከታተለዋል።*

**አፈፃፀም** ስ 1. አሰራር፥አንድን ነገር በስራ ላይ የማዋል ሂደት። 2. ተግባራዊነት። *በመመሪያው አፈፃፀም ላይ ችግር አለ።* 3. አጨራረስ።

**ፈፋ** ስ ጎርፍ የቦረቦረው ወይም የሸረሸረው ጉድባ፥ ገደል።

**ፉ** የ"**ፈ**" ፊደል ካእብ ዘር።

**ፉር**

**ፉርቲ (ፉርፉር)** ስ እንደ ቆርኪ፥ ክብ የቅል ስባሪ፥... ያሉት ሁለት ቦታ በመብሳትና ክር በቀዳዳዎቹ በማስገባት እያሽከረከሩ የሚጫወቱበት የልጆች መጫወቻ።

**ፉር አለ** ግ 1. በድንገትና በፍጥነት ብር ወይም ቱር አለ። 2. የጋማ ከብት በአፍንጫው አየር በማስወጣት ድምፅ አሰማ።

**ፉር ፉር አለ** ግ ፉርቲ ሲሽከረከር የሚያሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ።

**ፉርሽ** "**ፎረሸ**" ስር ተመ.

**ፉርቲ** "**ፉር**" ስር ተመ.

**ፉርኖ** ስ በዘመናዊ የዳቦ መጋገሪያ ከፉርኖ ዱቄት የሚጋገር ነጭ ዳቦ።

**ፉርኖ ዱቄት** ስ ለፉርኖ የሚሆን በጣም ነጭ

የሆነ የስንዴ ዱቄት።

**ፉርሽካ** "ፍሩሽካ" ን ተመ.

**ፉርጎ** ስ ክፍት ወይም ዝግ የሆነና እንደ ጋሪ ያለ፥ ለሰው ወይም ለእቃ፥... ማጓጓዣ የሚሆን የባቡር ክፍል።

**ፉርፉር** "ፉር" ስር "ፉርቲ"ን ተመ.

**ፉሮ** ስ የሚያስነጥስ በአፍንጫ ንፍጥ የመሰለ ነገር የሚያስወጣ የጋማ ከብት በሽታ።

**ፉቅራ** ስ ዛር ወይም ውቃቢ ያለበት ቃልቻ።

**ፉት**

**ፉት አለ** ግ 1. በትንሹ ጠጣ፥ ቀመሰ። 2. ቶሎ ጨረሰ፥ አጠናቀቀ።

**ፉት ቢሉት ጭልጥ** በጣም ትንሽ ወይም ጥቂት የሆነ።

**ፉት አደረገ** ግ በፍጥነት ጨረሰ፥ አጠናቀቀ። *ስራውን በአንድ ጊዜ ፉት አደረገው።*

**ፉንን** "ፎነነ" ስር "ፎናና"ን ተመ.

**ፉንጋ** ቅ ፊቱ አጭርና አፍንጫው ጎራዳ የሆነ።

**ፉከራ** "ፎከረ" ስር ተመ.

**ፉካ** ስ 1. እንደ ፊሳሽ፥ ብርሃን፥ አየር፥... ያሉ ነገሮችን እንዲያስተላልፍ በግንብ ላይ አልፎ አልፎ የሚበጅ ሽንቁር፣ ቀዳዳ። 2. በተዘጋ በር ወይም ግድግዳ በኩል ለመነጋገር ወይምመልእክት ለመለዋወጥ የሚያስችል እንደመስኮት ያለ ትንሽ ቀዳዳ።

**ፉክክር** "ፎከረ" ስር ተመ.

**ፉገራ** "ፎገረ$^{2}$" ስር ተመ.

**ፉጨት** "*ፏጨ"ስር ተመ.

**ፊ** የ"ፈ" ራደል ሳልስ ዘር።

**ፊሊት** ስ እንደ ዝንብ፥ ቢምቢ፥ ቁንጫ፥... ያሉ የቤት ውስጥ ተባዮችን ማጥፊያ መድሃኒት።

**ፊላ** ስ ቀጠን ያለና የሽንበቆ ላንፋ የሚመስል፥ በወንዝ ዳር የሚበቅል የሳር አይነት።

**ፊል**

**ፊል ፊል አለ** ግ 1. ከመሬት ፍልቅ ፍልቅ እያለ ወጣ (የምንጭ ውሃ)። 2. ፈላ፥ ተፍለቀለቀ (ቀጭን ወጥ)።

**ፊልም** ስ 1. ካሜራ ውስጥ ተደርጎ ምስል የሚቀረፅበት ስስ ፕላስቲክ መሰል ነገር። 2. "ሲኒማ" ን ተመ.

**ፊልም ቤት** ስ ሲኒማ ቤት።

**ፊልትሮ** ስ 1. የሞተርን ዘይት የሚያጣራ የመኪና እቃ። 2. አየር አጣርቶ ወደ ካርቡሬተር የሚያስተላልፍ የመኪና እቃ።

**ፊር**

**ፊር አለ** ግ ፊሽካ ሲነፋ የሚሰጠውን ድምፅ አይነት አሰማ።

**ፊሽካ** ስ በትንፋሽ አማካይነት እንደ ፉጨት ያለ ወይም ፊርር... የሚል ድምፅ የሚያወጣ፥ ከቆርቆሮ ወይም ከሌላ ነገር ሊሰራ የሚችል አነስተኛ እቃ (ብዙውን ጊዜ የስፖርት ዳኞችና ፖሊሶች የሚገለገሉበት።

**ፊቀን** ስ እንደ ገንቦ፥ መንቀል፥ እንስራ፥... ያለ የውሃ መያዣ እቃ።

**ፊተኛ** "ፊት" ስር ተመ.

**ፊታውራሪ** ስ በቀድሞ ጊዜ በጦርነት ወቅት በፊት በኩል ያለውን ጦር ለሚመራ ወይም የፊት ጦር አዝማች ለሚሆን ሰው ይሰጥ የነበረ የማእረግ ስም።

**ፊት** ስ 1. ከአገጭ እስከ ግንባር መጨረሻ ያለውና አፍ፥ አፍንጫ፥ አይን፥... ያለበት የራስ ክፍል። 2.በፊት ላይ የሚታይ የመቆጣትን፥ የመደሰትን፥... ሁኔታ የሚገልፅ ስሜት።*ክፍትፍቱ ፊቱ*።3• ቀድሞ የሚታይ፥ ከውጭ በኩል ያለ የአንድ ነገር ገፅታ ወይም አካል። *መኪናው በፊቱ በኩል ተጎድቷል።* 4. ቀድሞ፥ ጥንት፥ ድሮ፥ በፊት።*ፊት እንገናኝ ነበር አሁን ግን ተገናኝተን አናውቅም።*

**ከፊቱ ይነበባል** የተሰማው ስሜት ፊቱ ላይ ይታያል ወይም ያስታውቃል።

**ፊቱ ሳንባ መሰለ** ፊቱ ቀላ (ከብስጭት፥ ከንዴት፥ ከፀሃይ ብዛት፥... የተነሳ)።

**ፊቱ ተለወጠ /ተለዋወጠ/ ልውጥውጥ አለ** በንዴት፥ በድንጋጤ፥ በሃፍረት፥ በህመም፥... የተነሳ ፊቱ ላይ የሚታየው ስሜት ተለወጠ ወይም ተቀየረ።

**ፊቱ ደም መሰለ** ተናደደ፥ ተቆጣ።

**ፊቱን መለሰ** ምህረት አወረደ፥ ይቅር አለ፥ ታረቀ (ብዙውን ጊዜ እግዚአብሄር)።

**ፊቱን አይመልስም** አያወላውልም፥ አያፈገፍግም፥ ውሳኔውን አይሽርም፥ ውሳኔውን አያሽርም።

**ፊቱን ቋጠረ** ተኮሳተረ፣ የመቆጣት ወይም የመናደድ ስሜት ፊቱ ላይ ታየበት።

**ፊቱን አስመታ/ አስወጋ** ወደ አንድ ቦታ ለትንሽ ጊዜ ብቅ በማለት መኖሩን አሳወቀ፥ አሳየ።

**ፊቱን አዞረ** ጠላ፥ ተቀየመ፥ ቸላ አለ።

**ፊቱን ከሰከሰ** ፊቱን አኮሳተረ፥ አጠቆረ።

**ፊቱን ኮሶ አስመሰለ** ፊቱን ጨፈገገ፥ አኮሳተረ።

**ፊቱን ከፋው** የሃዘን ወይም ያለመደሰት ስሜት በፊቱ ላይ ታየ።

**ፊት ሰጠ** 1. ተቃለደ። 2. መቆጣትና መቆጣጠቱን ትቶ እንደ ልቡ ወይም እንዳሻው እንዲሆን አደረገ፤ አቀበጠ።3. እንዲቀርበው ወይም እንዲወዳጀው አደረገ።

**ፊት ነሳ** ችላ አለ፥ አላቀርብ አለ።

**ፊት አሳየ** ፊት ሰጠ።

**ፊት ፊት አለ** ቀደም ቀደም አለ።

**ወደፊት** ተው.ግ. 1. ለሚቀጥለው፥ ለሚመጣው ጊዜ። 2. የአንድ ድርጊት እንቅስቃሴ እንዲቀጥል ለማበረታታት ከመፈከር ጋር የሚባል። *ግይምነትን ለማጥፋት ወደፊት!* 3. በግንባር ትይዩ ወደአለው አቅጣጫ። *ወደፊት ሂድ።*

**ፊት ለፊት** ተው.ግ. 1. ግንባር ለግንባር፥ በአካል በመገናኘት (በአንድ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር፤ ለመወያየት፥...)። 2. ትይዩ። *ሱቁ ከት/ቤቱ ፊት ለፊት ነው።* 3. በፊት በኩል ያለው አቅጣጫ። 4.በአሽሙር ወይም በስውር ያልሆነ፥ በግልፅ። *ፊት ለፊት ሰደበው።*

**ፊት መመለሻ /መግለጫ** ስ እጅ መንሻ፥ ስጦታ።

**ፊት መሪ** ስ በሰልፍ ጊዜ ከፊት ሆኖ የሚመራ።

**ፊትና ሂላ** ተው.ግ. በቅደም ተከተል፥ በመከታተል።

**ፊተኛ** ቅ 1. ቀድሞ የነበረ። 2. ከፊት ያለ።

**ፊና** ስ ወገን፥ በኩል። *ሁሉም በየፊናው ሄደ።*

**ፊናንስ [ፖሊስ]** ስ ህጋዊ ቀረጥ ያልተከፈለባቸው ወይም ፈቃድ የሌላቸው እቃዎች በገበያ ላይ እንዳይውሉ ወይም ከሃገር ወደሃገር እንዳይዘዋወሩ የሚቆጣጠር አካል።

**ፊን**

**ፊን አለ** ግ 1. ውሃ ወይም ሌላ ፈሳሽ ነገር ቀጠንና ረዘም ብሎ በሃይል ወጣ፥ ተረጨ። 2. (ዘይ.) ድንገት ተቆጣ፥ ተቆናጠረ።

**ፊን ፊን አለ** ግ ቆጣ ቆጣ አለ፥ ተቆናጠረ።

**ፊንጢጣ** ስ በሰውና በእንሰሳት አካል ላይ የሚገኝ የአይነምድር ወይም የኩስ መውጫ።

**ፊኖ**[1] ስ ሲሚንቶና ደቃቅ አሸዋ ከውሃ ጋር ተደባልቆ የሚዘጋጅ የግድግዳ መለሰኛ፤ልስኑም ፊኖ ይባላል።

**ፊኖ**[2] **[ዱቄት]** ስ ፉርኖ ዱቄት።

**ፊኛ** ስ 1. ሽንት በቆሻሻነት ወደ ውጭ ከመውጣቱ በፊት በሰውነት ውስጥ የሚጠራቀምበት ከረጢት። 2. በትንፋሽ እየተነፋ እንደ ኳስ የሚለጠጥ የልጆች መጫወቻ ላስቲክ።

**ፊው**

**ፊው አለ** ግ 1. የፉጨት አይነት ድምፅ ተሰማ። 2. በድንገትና በፍጥነት ሽው አለ፥ ቱር አለ።

**ፊውዳሊዝም** ስ ከባሪያ አሳዳሪው ስርአተ ማህበር ቀጥሎ የመጣ ገበሬውና የመሬት ከበርቴው ዋነኛ መደቦች ሆነው የሚገኙበት ስርአተ ማህበር።

**ፊውዳል** ስ 1. በፊውዳሊዝም ስርአተ ማህበር የመሬት ባለቤት የሆነና ስልጣን ያለው የገገር መደብ። ቅ 2. የፊውዳል ስርአተ ማህበር አመለካከትን የያዘ ወይም የሚያንፀባርቅ።

**ፊደል** ስ ንግግርን በፅሁፍ ለማስፈር የሚያስችልና ድምፅን ወክሉ የሚቆም ምልክት (ለምሳሌ ሀ፥ለ፥...)።

**ፊደል ቆጠረ / ለየ** ፊደሉችን (ፊደላትን) ተማረ፥ ማንበብ ቻለ። *ፊደል የቆጠረው ቄስ ት/ቤት ነው።*

**ፊደል አስቆጠረ/አስለየ** ፊደል አስተማረ፥ አሳወቀ።

**ፊደል ሃዋርያ** ስ በቄስ ት/ቤት ልጆች የፊደል ትምህርት ከጨረሱ በሂላ ንባብ ማንበብ የሚለማመዱበት የዮሃንስ መልእክት አጭር ፅሁፍ።

**ፊደል ተራ** ስ የፊደሉች ቅደም ተከተል።

**ፊደል ገበታ** ስ በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ ፊደላት በሙሉ በቅደም ተከተላቸው ተመዝግበው የሚገኙበት ወረቀት ወይም ሰሌዳ።

**ፊጥ**

**ፊጥ አለ** ግ ከፍ ወይም ረዘም ያለ ነገር ላይ ወጥቶ ቁጢጥ፥ ቁጭ፥ ቁብ አለ።

**ፊጥኝ** ስ ሁለት እጅን ወደሂላ በማዞር የሚያስሩት አስተሳሰር።

**የፊጥኝ አሰረ** ግ ሁለት እጅን ወደ ሂላ በማድረግ አሰረ።

**ፉ** የ "ፈ" ፊደል ራብእ ዘር።

**ፉልማ** ቅ በወንዝ ዳርና ዳር የሚገኝ ለም የሆነ መሬት።

**ፉመ** ግ ፍም ሆነ።

**ፍም** ስ እንጨት ወይም ከሰል በእሳት ተቀጣጥሉ ነበልባሉ ካለቀ በሂላ የሚቀረውና ወደ እሳትነት ተለውጦ የሚገኘው የእንጨቱ ወይም የከሰሉ አካል።

**ፍሙ ወረደ** እንጨቱ ወይም ከሰሉ ነዶ ፍም ሆነ።

**ተፋፋመ** ግ ተሟሟቀ፥ ተጋጋለ፥ ተጧጧፈ (ጦርነት፥ ጠብ፥ ክርክር፥...)።

**አፋመ** ግ 1. ፍም ሆነ፥ ፍም በብዛት ወረደ። 2. ከእንጨት ወይም ከከሰል ፍም አዘጋጀ።

**አፋፋመ** ግ 1. አሟሟቀ፥ አጋጋለ:: 2. አጣደፈ፥ አስጨንቆ ያዘ፥ አዳረሰ::*ምጡ አፋፍሟታል::*

**ፋረ** ግ ጫረ፥ ቆፈረ (በጥፍር፥ በዶማ፥...)::

**ፋራ** ስ የሰው ወይም የከብት ዱካ::

**ፋሮ** ስ መሬት የሚጭር ወይም የሚቆፍርና እግሮቹ አጫጭር የሆኑ እንደ ድመት ያለ አውሬ::

**ፋራ**[1] ቅ (ያራዳ አነ.) ያልሰለጠነ፥ ከርፋፋ፥ ባላገር::

**ፋራ**[2] **"ፋረ"** ስር ተመ.

**ፋራናይት** ስ የሙቀት ወይም የቅዝቃዜ መጠን መለኪያ:: 212$^0$ ፋራናይት 100$^0$ ሴንቲግሬድ ይሆናል::

**ፋራፋንጎ "ፈረፋንጎ"**ን ተ.መ.

**ፋርማሲ** ስ የመድሃኒት መሸጫ መደብር::

**ፋሮ "ፋረ"** ስር ተመ.

**ፋሲካ (ፋሲጋ) "ፈሰከ"** ስር ተመ.

**ፋስ** ስ 1. ከስለቱ በኩል ወደ እጀታው ነጠፍ ያለና እንጨት ለመጥረብ፥ ምስማር ለመምታትና ለመንቀል የሚያገለግል የአናፂ መሳሪያ:: 2. መጥረቢያ::



ፋስ 1ኛ ፍቺ

***ፋሸከ**

**ፍሸኪያ (ፍሸጊያ)** ስ ማዛጋት::

**አፋሸከ (አፋሸገ)** ግ አዛጋ::


**ፋሻ** ስ 1. ለቁስል መሸፈኛ ወይም ማሰሪያ የሚያገለግል በጥቅል ሆኖ የሚዘጋጅ ነጭና ረዥም ጨርቅ::

**ፋሽስት** ስ 1. አጀማመሩ በኢጣሊያ ውስጥ የሆነውን የቀኝ ክንፍ አክራሪና አምባገነናዊ አመለካከትን የያዘ የፖለቲካ መስመር ተከታይ::2. (ዘይ.) አረመኔ፥ ጨካኝ፤ ነፍሰ ገዳይ::

**ፋሽን** ስ በአንድ በተወሰነ ወቅትና ቦታ በህብረተሰቡ ዘንድ ቀደም ሲል ከነበሩት የበለጠ ተቀባይነት ያለው ጊዜ አመጣሽ አስተሳሰብን፥ አነጋገርን፥ ልብስን፥ አለባበስን፥ የፀጉር አሰራርን፥... የሚመለከት ሁኔታ ወይም አድራጎት::

**ፋሽኑ ያለፈበት** በአንድ በተወሰነ ወቅትና ቦታ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ኖሮት በሂላ ግን ተቀባይነት ያጣ (የአስተሳሰብ፥ የአነጋገር፥ የልብስ፥ የአለባበስ፥ የፀጉር አሰራር፥.. አይነት)::

**ፋሽኮ** ስ ከወገቡ በታች በሰሌን የተሸፈነና ቂጡ ላይ እንደ ማቶት ሆኖ የተሰራ ማስቀመጫ ያለው የቪኖ ጠርሙስ::



ፋሽኮ

**ፋቀ**[1] ግ 1. ሳጠ፥ መለጠ፥ ፈገፈገ:: 2. በመፋቂያ ጥርስን አሟጠ፥ አፀዳ:: 3. ሰረዘ፥ ደመሰሰ፥ አጠፋ (ፅሁፍን)::

**መፋቂያ** ስ የጥርስ ማፅጃ፥ መሟሟጫ እንጨት::

**ፋቂ** ስ ለልዩ ልዩ አገልግሎት ሊውል የሚችል የእንስሳት ቆዳን እየፋቀና እያለፋ የሚያለሰልስ ባለሙያ::

**ፋቀ**[2] ግ አቃረ::

**ፋቅ** ስ ቃር::

**አፋቀ** ግ አቃረ::

**ፋቂ "ፋቀ**[1]**"** ስር ተመ.

**ፋቅ "ፋቀ**[2]**"** ስር ተመ.

**ፋብሪካ** ስ በተለያዩ ማሽኖች የተለያዩ ቁሳቁሶች በብዛት የሚመረቱበት ድርጅት::

**ፋታ** ስ ጥቂት እረፍት::

**ፋታ ሰጠ** እንዳይቸገር፥ እንዳይጨነቅ፥ እንዳይጣደፍ፥... ጊዜ ሰጠ::

**ፋነነ** ግ 1. ፈረጠጠ፥ ቦረቀ፥ ፈነጨ:: 2. በውዴታ ወይም በገዛ ፈቃዱ ዘመተ::3. አውደለደለ፥ ቦዘነ::

**ፋኖ** ስ ሳይታዘዝ በፈቃዱ የሚዘምት፤ ወደ ዘማች::

**ፋና** ስ የጧፍ፥ የፋኖስ፥... መብራት ወይም ብርሃን::

**ፋና ወጊ** ስ በድሮ ጊዜ በቤተመንግስት ወይም በመኳንንት ቤት ማታ ማታ የእንጨት ወይም የጧፍ መብራት ይዞ የሚቆም አሽከር::

**ፋንታ (ፈንታ)** ስ 1. ድርሻ:: *ይህ ዳቦ የእኔ ፋንታ ነው::* 2.ተራ፥ ወረፋ:: *አሁን መጫወቱ የኔ ፋንታ ነው ::* 3.ምትክ:: *በእኔ ፋንታ እሱ ይሄዳል::*

**ፋንድያ** ስ የጋማ ከብት ኩስ::

**ፋኖ "ፋነነ"** ስር ተመ.

**ፋኖስ** ስ ነጭ ጋዝ ተጨምሮበት መስታወት መሰል ብርጭቆ ውስጥ ያለው ክር ሲቀጣጠል ብርሃን ሊሰጥ የሚችል የመብራት እቃ::



ፋኖስ

**ፋክቱር** ስ ለተገዛ እቃ፥ ለትራንስፖርት፥... ለወጣ ወጪ ማስረጃ እንዲሆን የወጣው የገንዘብ

ልክ የተፃፈበት ወረቀት፣ ደረሰኝ ወይም ማስረጃ::

**ፋይል** ስ የህይወት ታሪክ ወይም የክስ ወይም የማመልከቻ÷... ደብዳቤዎችን የያዘ ማህደር÷ ክላሰር፣ ዶሴ::

**ፋይል ከፈተ** 1. ክስ መሰረተ:: 2. አንድን ጉዳይ በተመለከተ የተፃፉና የሚፃፉ ደብዳቤዎች የራሱ መለያ ቁጥር ባለው ማህደር ውስጥ እንዲቀመጡ አደረገ::

**ፋይናንስ** ስ የገንዘብ ገቢና ወጪ ነክ ጉዳይ:: *የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት::*

**ፋይዳ** "ፈየደ" ስር ተመ.

***ፋደሰ**

**አፋደሰ** ግ አውደለደለ÷ ያለስራ ወዲያ ወዲህ አለ::

**አፋዳሽ** ቅ (ስድብ) አውደልዳይ::

**ፋደት** ስ የሚከረፋ ሽታ ያለው÷ ጅራቱ ጎፍላ የሆነና መልኩ ጥርኝ የሚመስል አውሬ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)::

**ፋገ** ግ በትንሹ የነበረው እየሰፋ ሄደ (እሳት÷ ቁስል)::

**አፋገ** ግ ፋገ::

**ፋገረ (ፏገረ)** ግ 1. ለፋ÷ ወጣ ወረደ÷ ደከመ:: 2. ጫረ÷ ጎደፈረ÷ ቆፈረ፣ ፎገረ::

**ፋጉሎ** ስ 1. ተጨምቆ ዘይቱ ከወጣ በሗላ የሚቀረው የኑግ ወይም የተልባ አሰር÷ አተላው:: 2. (ዘይ÷ ስድብ) መልከ ጥፉ::

**ፋጋ** ስ ለጠላ መጠጫ÷ ለውሃ መጥለቂያ÷... የሚያገለግል አፈ ሰፊ አንኮላ ወይም የቅል ጉማጅ::

**ፋፋ** ስ ከተለያዩ የእህል አይነቶች በፋብሪካ ውስጥ ተዘጋጅቶ በላስቲክ እየታሸገ ለህፃናት ምግብነት የሚቀርብ የምግብ ዱቄት::

**ፋፋ** ግ ወፈረ÷ ዳበረ (ህፃን÷ ተክል÷...)::

**ፌ** የ "ፈ" ፊደል ሃምስ ዘር::

**ፌራ** ስ በንክኪ የሚተላለፍ የተሰቦ በሽታ::

**ፌርማታ** ስ የከተማ አውቶቡስ ቆሞ ተሳፋሪዎችን የሚያሳፍርበትና የሚያወርድበት ቦታ::

**ፌቆ** ስ በተራራና በገደል የምትኖርና ፍየል የምትመስል የዱር እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)::

**ፌንጣ** ስ አንበጣ የሚመስል÷ ሳር የሚበላና ሲሄድ ጡብ ጡብ የሚል የነፍሳት አይነት::



ፌንጣ

***ፌዘ**

**ፌዝ** ስ ቀልድ÷ ቧልት::

**ፌዘኛ** ቅ ቀልደኛ÷ቧልተኛ::

**አፌዘ** ግ ቀለደ÷ አላገጠ÷ አሾፈ::

**ፌጦ** ስ ፍሬው ሰሊጥ የሚመስል÷ ሲበሉት የሚሰንፍጥና ብዙውን ጊዜ ለመድሃኒትነት የሚገለገሉበት የቅመም አይነት::

**ፍ** የ "ፈ" ፊደል ሳድስ ዘር::

**ፍለጋ** "ፈለገ" ስር "ፈለግ"ን ተመ.

**ፍላሎት** "ፈላ[1]" ስር ተመ.

**ፍላሽ** ስ በቤት ውስጥ ወይም በቂ ብርሃን በሌለበት ቦታ ፎቶግራፍ ለማንሳት እንዲቻል ተፈላጊውን ብርሃን የሚሰጥ የካሜራ መብራት::

**ፍላቂ.** "ፈለቀ" ስር ተመ.

**ፍላጎት** "ፈለገ" ስር ተመ.

**ፍላጭ** "ፈለጠ" ስር ተመ.

**ፍላፃ** ስ ቀስት::

**ፍል[1]** "ፈላ[1]" ስር ተመ.

**ፍል[2]** "ፈላ[2]" ስር ተመ.

**ፍልሚያ** " ፈለመ" ስር ተመ.

**ፍልም** ዝ.ከ.

**ፍልሰታ** ስ (ኢ .ኦ .ተ .ቤ.) ከነሃሴ 1 እስከ ነሃሴ 16 ቀን ድረስ ያለው የፆም ጊዜ::

**ፍልስልስ** "ፈለሰ" ስር ተመ.

**ፍልስፍና** "ፈለሰፈ" ስር ተመ.

**ፍልቃቂ** "ፈለቀቀ" ስር ተመ.

**ፍልቃጭ** "ፈለቀጠ" ስር ተመ.

**ፍልቅልቅ** "ፈለቀ" ስር ተመ.

**ፍልቅቅ** "ፈለቀቀ" ስር ተመ.

**ፍልጥ** "ፈለጠ" ስር ተመ.

**ፍልፈል** ስ በመሬት ውስጥ የሚኖር÷ አፈሩን ከውስጥ እየቆፈረና ወደ ውጭ እየገፋ የሚቆልል አይጥ መሰል አውሬ::

**ፍልፍል** "ፈለፈለ[2]" ስር ተመ.

**ፍሎረሰንት** ስ ረጅም ዘንግ የሚመስል የአምፖል አይነት::

**ፍም** "ፋመ" ስር ተ.መ.

**ፍሩሽካ (ፉርሽካ)** ስ 1. ዱቄት በፋብሪካ ሲዘጋጅ የሚገኝና ለእንስሳት መኖነት የሚያገለግል ተረፈ ምርት፣ የእህል አሰር:: 2. የእንጨት (የጣውላ) ፍቀፋቂ፣ ስጋቱራ::3. (ዘይ.) የማይረባ÷ ጥራት የሌለው::

**ፍሪሲዎን** ስ ሞተርንና ትራንስሚሲዮንን ከካምቢዮ ጋር በማገናኘትና በማለያየት

የመኪናውን ፍጥነት ለመጨመርና ለመቀነስ የሚያስችል የመኪና እቃ።
**ፍሪዳ** ስ የተቀለበ የእርድ ከብት ወይም ሰንጋ።
**ፍሪዳ ጣለ** ሰንጋ ወይም በሬ ወይም መሲና አረደ።
**ፍሪጅ** ስ የተለያየ መጠን ያለውና በኤሌክትሪክ ሃይል የሚሰራ፥ ምግብን ወይም ሌላ ፈሳሽ ነገርን፥ መድሃኒትን፥... አቀዝቅዞና ሳይበላሽ ለረጅም ጊዜ ጠብቆ ለማቆየት የሚያገለግል፤ እቃ፤ ማቀዝቀዣ ወይም በረዶ ቤትም ይባላል።
**ፍራሽ** "ፈረሰ" ስር ተመ.
**ፍራሽ** ስ ጥጥ፥ስፖንጅ፥ ቁርጥራጭ ጨርቅ፥... በአልጋ ልክ በተሰፋ ከረጢት መሰል ጨርቅ ውስጥ አስገብቶ በመስፋት የሚዘጋጅና በመተኛነት የሚያገለግል ድልዳል።
**ፍራት (ፍራቻ)** "ፈራ" ስር "ፍርሃት" ን ተመ.
**ፍራንክ** ስ 1. ሳንቲም። 2. ገንዘብ።
**ፍራንኮ ቫሉታ** ስ ከሃገር ውስጥ የውጭ ምንዛሪ ሳይጠየቅ መሳሪያዎችንና እቃዎችን በፈቃድ ወደ ሃገር ውስጥ በማስገባት የሚካሄድ ንግድ።
**ፍራክሽን** (ሂሳ.) ስ ክፍልፋይ ።
**ፍራፍሬ** "*ፈራ" ስር ተመ.
**ፍሬ** ዝ.ከ.
**ፍሬን** ስ የተሽከርካሪ እግሮች እንዲቆሙ ለማድረግ ወይም ፍጥነትን ለመቆጣጠር የሚያስችል የተሽከርካሪው አካል።
**ፍሬን ለቀቀ** አእምሮውን መቆጣጠር እስኪሳነው ድረስ በጣም ሰከረ።
**ፍሬክርስኪ (ፍሬፈርስኪ)** "*ፈራ" ስር ተመ.
**ፍርሃት** "ፈራ" ስር ተመ.
**ፍርምርም** "ፈረመረመ" ስር ተመ.
**ፍርምባ** ስ ከአንገት በታች በፊት እግሮች መካከል የሚገኝ የከብት አካል ክፍል ወይም ብልት።
**ፍርስራሽ** "ፈረሰ" ስር ተመ.
**ፍርቅርቅ** "*ፈረቀረቀ" ስር ተመ.
**ፍርንስ** "*ፈረነሰ" ስር ተመ.
**ፍርንትት** ስ በብልትና በጭን መካከል ያለ፥ ቆዳው ለስላሳ የሆነ የሰውነት ክፍል፤ ብሽሽት።
**ፍርኩታ** ስ የተበረበረ ዋሻ፤ ጎሬ።
**ፍርክርክ** "*ፈረከረከ" ስር ተመ.
**ፍርክስ** "ፈረከሰ" ስር ተመ.
**ፍርድ** "ፈረደ" ስር ተመ.
**ፍርጃ** ዝ.ከ.
**ፍርግርግ** ስ 1. እንደ ኤክስ(x) ምልክት ሆኖ ወይም በሰያፍ የሚበጅ ማገር። 2. ከብረት በተሰራና ባለመስተዋት በሆነ የብረት መዝጊያ ወይም መስኮት ላይ ከብረት ዘንጎች በተለያየ ቅርፅ የሚሰራ መከታ ወይም መከልከያ፤ ግሪል።
**ፍርጥም** "ፈረጠመ" ስር ተመ.
**ፍርፋሪ** "ፈረፈረ" ስር ተመ.
**ፍርፍር** ዝ.ከ.
**ፍሳሽ** "ፈሰሰ" ስር ተመ.
**ፍስሃ** ስ ደስታ።
**ፍስክ (ፍስግ)** "ፈሰከ" ስር ተመ.
**ፍሽኪያ (ፍሽጊያ)** "ፋሸከ" ስር ተመ.
**ፍቃድ** "ፈቀደ" ስር "ፈቃድ"ን ተመ.
**ፍቅረኛ** "ፈቀረ" ስር ተመ.
**ፍቅር** ዝ.ከ.
**ፍቅፋቂ** "ፈቀፈቀ" ስር ተመ.
**ፍተሻ** "ፈተሸ" ስር ተመ.
**ፍቱን** "ፈተነ" ስር ተመ.
**ፍታት** "ፈታ" ስር ተመ.
**ፍትህ** ስ ትክክለኛ ፍርድ፥ ብያኔ፥ ውሳኔ፥ በህግ መሰረት መዳኘት።
**ፍትሃብሄር** ስ 1. ከወንጀል ውጪ የሆኑና ከገንዘብ፥ ከንብረት፥... ጋር የተያያዙ ጉዳዮች የሚታዩበትና ፍርድ የሚሰጥበት ህግ። 2. የፍትሃብሄር ህግ የተፃፈበት መፅሃፍ።
**ፍትሃነገስት** ስ በዘመናዊ መልክ የተዘጋጁት ፍትሃብሄርና ወንጀለኛ መቅጫ መፃህፍት ከመፃፋቸው በፊት መንፈሳዊና ስጋዊ ጉዳዮችን በተመለከተ የዳኝነት ጉዳይ ይታይበት የነበረ የህግ መፅሃፍ።
**ፍትሃዊ** ቅ ትክክለኛ፥ ህጋዊ።
**ፍትልትል** "*ፈተለተለ" ስር ተመ.
**ፍትወት** ስ 1. ምኞት፥ ፍላጎት። 2. ፍትወተ ስጋ።
**ፍትወተ ስጋ** ስ የወሲብ ፍላጎት።
**ፍትግ** "ፈተገ" ስር ተመ.
**ፍትፍት** "ፈተፈተ" ስር ተመ.
**ፍች** "ፈታ" ስር ተመ.
**ፍናቅ** ስ ጉድጓድ ወይም ጉድባ የበዛበት ያልተስተካከለ ቦታ።
**ፍናቂ** ቅ 1. ፍናቅ። 2. የግንብ ንቃቃት፥ ብስ፥ ሽንቁር።
**ፍናፍንት** ስ የወንድም የሴትም የተፈጥሮ

መለያዎች ያሉት ሰው፤ ወንዳገረድ።
**ፍንትው አለ** ግ ግልፅ ሆኖ ወይም ቀልጥ ብሎ ታየ።
**ፍንካች** "ፈነከተ" ስር ተመ.
**ፍንከች**
**ፍንከች አይልም** ግ 1. አይበገርም፥ አይደፈርም። 2. ንቅንቅ፥ ዝንፍ አይልም፤ የማይለወጥ፥ የፀና ነው።*ከተናገረው ፍንከች አይልም።*
**ፍንዳታ** "ፈነዳ" ስር ተመ.
**ፍንድ** ዝ.ከ.
**ፍንድድ** "*ፈነደደ" ስር ተመ.
**ፍንጃል** ስ የቡና ወይም የሻይ መጠጫ፤ ስኒ።
**ፍንጣሪ** "ፈነጠረ" ስር ተመ.
**ፍንጣቂ** "ፈነጠቀ" ስር ተመ.
**ፍንጥር**
**የፍንጥር** ስ ከብት፥ እቃ፥... ሲሸጥ ገዢና ሻጭ ገንዘብ አዋጥተው ላሻሻጧቸው ወይም ላስማሟቸው ሰዎች የሚያደርጉት የደስደስ ግብዣ።
**ፍንጭ** ስ 1. የወሬ ወይም የአንድ ጉዳይ ጭላንጭል ወይም ምልክት። 2. የቀስል፥ የእበጥ ቀዳዳ ወይም አፍ።
**ፍንጭት** ስ 1. በላይኛው ሁለት የፊት ጥርሶች መካከል ያለ ክፍተት።2. ጥርሱ ፍንጭት የሆነ ሰው።
**ፍንፅቅ ዘር** ስ እንደ ሂ ተኳ፥ ሟ፥... ያሉ የፊደላት ዘር።
**ፍካሬ ኢየሱስ** ስ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሃዋርያት የነገራቸውንና በስምንተኛው ሺህ የሚደረገውንና የሚሆነውን ነገር ይናገራል ተብሎ የሚታመንበት የትንቢት መፅሃፍ።
**ፍዝ** "ፈዘዘ" ስር "ፈዛዛ" ን ተመ.
**ፍየል** ስ የበግ ቅርፅ ያለው፥ አካሉ ከርደድ ባሉና አጫጭር በሆኑ ፀጉሮች የተሸፈነ የቤት እንስሳ (ለአሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.)።
**ፍየለ ፈጅ** ስ በደጋና በወይና ደጋ አካባቢ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።
**ፍየል ምላስ** ቅ (ዘይ.) ለፍላፊ፥ቀባጣሪ።
**ፍዳ** ስ መከራ፥ ስቃይ።
**ፍዳ አስቆጠረ** መከራ አሳየ፥ አሰቃየ።
**ፍዳውን አየ** ብዙ ተሰቃየ፥ መከራ ተቀበለ።
**ፍጅት** "ፈጀ[2]" ስር ተመ.
**ፍጃታ** ዝ.ከ.
**ፍግ** ስ በበረት ውስጥ ደርቆ የተሰባበረ ወይም የደቀቀ እበት፥ ፋንድያ፥ በጠጥ።

**ፍግምግም** "*ፈገመገመ" ስር ተመ.
**ፍጡር** "ፈጠረ[1]" ስር ተመ.
**ፍጥምጥም** "*ፈጠመ[1]" ስር ተመ.
**ፍጥረት** "ፈጠረ[1]" ስር ተመ.
**ፍጥነት** "ፈጠነ" ስር ተመ.
**ፍጥጥም** "*ፈጠመ" ስር "ፍጥምጥም" ን ተመ.
**ፍጩ** "ፈጨ" ስር ተመ.
**ፍፁም** "ፈፀመ" ስር ተመ.
**ፍፃሜ** ዝ.ከ.
**ፎ** የ"ፈ" ፊደል ሳብእ ዘር።
***ፎለፎለ**
**ፎልፏላ (ፎለፎል)** ቅ ተጫዋች፥ ሳቂታ።
**ተንፎለፎለ** ግ ተንገርቀገርቀ፥ በብዛት ፈሰሰ (ፈሳሽ)።
**አንፎለፎለ** ግ በብዛት አፈሰሰ፥ አንዶለዶለ፥ አንገርቀገርቀ (ፈሳሽን)።
**ፎሌ** ስ ለመጠጫና ለውሃ መጥለቂያ የሚያገለግል ሸክና የሚመስል ቅል።
**ፎልፏላ** "*ፎለፎለ" ስር ተመ.
**ፎረሸ** ግ ሳተ፥ ተሳሳተ፥ አበላሸ (በልጆች ጨዋታ ስርአት) ።
**ፉርሽ** ቅ ልጆች እንደ ሰኞ ማክሰኞ፥ ጠጠር፥.. ያሉ ጨዋታዎችን በሚጫወቱበት ጊዜ ስህተት የሰራውን ተጫዋች ተሳስተሃል ለማለት የሚጠቀሙበት ቃል።
**ፉርሽ ሆነ** 1. ተሳሳተ (በልጆች ጨዋታ)።2. ከሸፈ።
**ፎረፎር** ስ የሚያሳክክ ደቃቅ ብናኝን በራስ ቆዳ ላይ የሚያስከትል በሽታ፤ ብናኙም ፎረፎር ይባላል።
**ፎርማሊቲ** ስ አንድን ጉዳይ ለማከናወን መሟላት ያለባቸውና ስርአትና ደንብን ተከትለው የሚፈፀሙ ድርጊቶች።
**ፎርማጆ** ስ የደረቀ አይብ።
**ፎርም** ስ 1. መልክ፥ አይነት፥ ቅርፅ። *በዚህ ፎርም ይሰራ።* 2. ቅፅ። *የቅጥር ፎርም።* 3. ቁንጥ።*እገሌ አካሄዱ ፎርም አለው።*
**ፎርፌ** ስ (ስፖ.) በተያዘለት ጊዜና ቦታ ለውድድር ባልቀረበ ወይም በውድድር ጊዜ ጨዋታው እንዲቋረጥ የሚያደርግ የስነ ስርአት ጉድለት በፈፀመ ወገን ላይ የሚጣልና አጥፊውን ወገን ተሸናፊ የሚያደርግ ቅጣት።
***ፎሸፎሸ**
**ፎሽፏሻ** ቅ ምስጢር መያዝ የማይችል፥ ወሬኛ።

**ተንፎሸፎሸ** ግ 1. ወሬ ነዛ:: 2. በሃይል ወይም በብዛት ፈሰሰ(ፈሳሽ)::

**አንፎሸፎሸ** ግ በብዛት አፈሰሰ፥ ለቀቀ (ፈሳሽን)::

***ፎቀቀ**[1]

**እንፉቅቅ** ስ በቂጥ እየተንፏቀቁ መሄድ::

**ፎቃቃ** ቅ (ስድብ) መራመድ የማይችልና በቂጡ እየተንፏቀቀ የሚሄድ::

**ፎቀቅ አለ** ግ 1. በቂጡ እየተንፏቀቀ ወይም እየተሳበ ሄደ:: 2.ራቅ ወይም እልፍ አለ፤ ፈቀቅ አለ::

**ፎቀቅ አደረገ** ግ ገፋ፥ ፈቀቅ አደረገ::

**ተንፏቀቀ** ግ በቂጡ እየተሳበ ወይም እየተንሸራተተ ሄደ::

**አንፏቀቀ** ግ ፎቀቅ አደረገ::

***ፎቀቀ**[2]

**ፎቃቃ** ቅ (ስድብ) አሳባቂ፥ አዋሻኪ::

**አንፏቀቀ** ግ አሳበቀ፥ አዋሸከ::

**አንፏቃቂ** ቅ (ስድብ) ወሬ ወዲያና ወዲህ የሚያመላልስ፥ አሳባቂ::

**ፎቀፎቀ** ግ የተላከከ ወይም የተጣበቀ ነገርን ለማላቀቅ ፈገፈገ (ብዙውን ጊዜ ምጣድ ላይ የተጣበቀ እንጀራን፥ ቂጣን፥...)::

**ፎቃቃ**[1] "ፎቀቀ[1]" ስር ተመ.

**ፎቃቃ**[2] "ፎቀቀ[2]" ስር ተመ.

**ፎቅ** ስ ወደላይ ተደራርበው የተሰሩ ቤቶች ወይም ክፍሎች ያሉበት ህንፃ ፤ ደርብ ::

**ፎተተ** ግ ሸረደደ፥ አሽሟጠጠ::

**ፎታች** ቅ አሽሟጣጭ::

**ፎቴ** ስ ሶፋ::

**ፎቶግራፍ (ፎቶ)** ስ በካሜራ አማካኝነት በፊልም ተቀርፆ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ወረቀት ላይ የሚታተም የአንድ ነገር ምስል::

**ፎቶግራፍ ተነሳ** በካሜራ ምስሉ ተቀረፀ::

**ፎቶግራፍ አነሳ** በካሜራ የአንድን ነገር ምስል ቀረፀ::

**ፎቶግራፍ ማንሻ** ስ ካሜራ::

**ፎቶግራፍ አንሺ** ስ ፎቶግራፍ በማንሳት የሚተዳደር ባለሙያ::

**ፎነነ** ግ አፍንጫን ቆረጠ ወይም ጎመደ::

**ፎናና (ፉንን)** ቅ (ስድብ) አፍንጫው የተቆረጠ:: 2. አፍንጫው አጭር የሆነ::

**ፎከረ (ፈከረ)** ግ 1.የፈፀመውን ጀብዱ በድንፋታ (ጀግንነትን ወይም ወኔን በሚቀሰቅስ ሁኔታ) ተናገረ፤ ዘራፍ አለ:: 2. ዛተ፥ አስፈራራ::

ፎክርባኛል::

**መፈክር** ስ የአንድን ትግል ወይም እንቅስቃሴ የቅርብም ሆነ የሩቅ አላማና አቅጣጫ ለማመልከት በአጭር ሃረግ ወይም አረፍተ ነገር ተዘጋጅቶና በጉልህ ተፅፎ የሚታይ ወይም በቃል የሚባል መሪ ሃሳብ::

**ፉከራ** ስ አንድ ሰው ስለፈፀመው ጀብዱ እያነሳ በድንፋታ (ጀግንነትንና ወኔን በሚቀሰቅስ ሁኔታ) የሚለው ቃል:: 2. ዛቻ::

**ፉክክር** ስ 1. አንዱ የሆነውን፥ ያደረገውን፥... ሌላው ለመሆን፥ ለማድረግ፥... ወይም በልጦ ለመገኘት የሚደረግ ጥረት፥ ውድድር:: 2. አንተ አድርግ አንተ አድርግ መባባል::

**ተፎካከረ** ግ 1. አንዱ የሆነውን፥ ያደረገውን፥... ሌላው ለመሆን፥ ለማድረግ፥... ወይም በልጦ ለመገኘት ጣረ፥ ሞከረ፤ ተወዳደረ:: 2. አንተ አድርግ አንተ አድርግ ተባባለ::

**ተፎካካሪ** ቅ 1. ተቀራራቢ፥ አቻ (በሃብት፥ በእውቀት፥...):: 2. ተወዳዳሪ::

**ፎከተ** ግ 1. የስውነት ቆዳን በጣም አድርጎ አከከ:: 2. (ዘይ.) በድህነት በጣም ተቸገረ:: 3. ያላደገ ሳርን ከስር ፈግፍጎ አጨደ፥ ጋጠጠ::

**ፎከት** ስ እከክ፥ ደረመን::

**ፎከታም** ቅ (ስድብ) እከካም::

***ፎደፎደ**

**ፎድፏዳ(ፎደፎድ)** ቅ እርብትብት::

**ተንፎደፎደ** ግ ተንበደበደ፥ ተብረከረከ::

**አንፎደፎደ** ግ አንበደበደ፥ አንቀጠቀጠ::

**ፎገረ**[1]**(ፈገረ)** ግ ከብት፥ ውሻ፥... መሬትን ፋረ፥ መነቀረ፥ ቆፈረ::

**ፎገረ**[2] ግ (ያራዳ አነ.) 1. ደለለ፥ አታለለ:: 2. ፎተተ፥ አሽሟጠጠ::

**ፉገራ** ስ 1. ማታለል፥ መደለል:: 2. ፉተታ፥ ሟሽሟጠጥ::

**ፎጋሪ** ቅ 1. አታላይ:: 2. ፎታች::

**ተፎገረ** ግ ተነቃበት፥ ታወቀበት::

**አስፎገረ** ግ አስነቃ፥ እንዲታወቅበት አደረገ::

**ፎጠና** ስ ወጣት፥ ሶታ፥ ኮበሌ::

**ፎጣ** ስ ሰውነትን፥ እጅን፥... ታጥቦ ለማድረቂያ የሚያገለግል፥ እርጥበትን መምጠጥ የሚችል ጭገር ያለው ወፍራምና ለስላሳ የሆነ ጨርቅ::

**ፏ**[1] የ "ፈ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር::

**ፏ**[2]

**ፏ አለ** ግ 1. ድንገት በሃይል ፈሰሰ:: 2. በግ፥ ደመቅ አለ (ብዙውን ጊዜ ለመብራት)::

**ፏሸረ**

**አንፏሸረ** ግ አዘጠዘጠ፥ አምቧተረ፥ ጉራ ነዛ።
**አንፏሻሪ** ቅ (ስድብ) አዘጥዛጭ፥ አምቧታሪ፥ ጉረኛ።
**ፏደደ** ግ እንደ ጅብ ጎንበስ ጎንበስ፥ ደፋ ቀና እያለ ገሰገሰ ፥ ሮጠ።
**ፏድድ ፏድድ አለ** ግ ፏደደ።
**ፏገረ** "ፋገረ"ን ተመ.
***ፏጨ**
**ፏጨት** ስ አፍን አሞጥሙጦና ከናፍርን አጥብቦ፥ በመካከሉ ባለው ጠባብ ቀዳዳ አየር በማስወጣት የሚፈጠር ድምፅ።
**አፏጨ** ግ ፏጨት አሰማ።
***ፏፏ**
**ፏፏቴ** ስ ከገደል አፋፍ ላይ በሃይልና በብዛት ተወርውሮ የሚወርድ ውሃ።
**ፏፏ አለ** ግ 1. በብዛት እየተንቦለቦለ ፈሰሰ። 2. ፏፏቴ የሚያሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ።
**ተንፏፏ** ግ በሃይልና በብዛት ፈሰሰ፥ ወረደ፣ ተንቧቧ (ፈሳሽ)።
**አንፏፏ** ግ በሃይል አፈሰሰ፥ አወረደ (ፈሳሽን)።

# ፐ

**ፐ** ከ "ፈ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

**ፐርሶኔል** ስ 1. የሰራተኛ ማስተዳደሪያ ክፍል።2. የሰራተኛ ማስተዳደሪያ ክፍል ሃላፊ።

**ፑ** የ "ፐ" ፊደል ካእብ ዘር።

**ፑሽአፕ** ስ በተለይ የእጅና የትከሻ አካባቢ ጡንቻዎችን ለማጠናከር ሲባል በእግር ጣቶችና በእጅ መዳፎች መሬት ላይ ተመርኩዞ ሰውነትን ቀጥ አድርጎ በመዘርጋትና የሰውነትን ክብደት ወደላይና ወደታች በማንቀሳቀስ የሚሰራ የጅምናስቲክ አይነት።

**ፒ** የ "ፐ" ፊደል ሳልስ ዘር።

**ፒራሚድ** ስ ባለሶስት ወይም ባለአራት ማእዘን መሰረት ኖሮት ጎኖቹ ወደላይ እየረዘሙ ሄደው ሾጣጣ ቅርፅ በመያዝ አንድ ቦታ ላይ እንዲጋጠሙ ተደርጎ የሚሰራ ቅርፅ (ለምሳሌ የግብፅ ፒራሚዶች)።



ፒራሚድ

**ፒሳ** ስ ቶርኖ ዱቄት በስሱ ተጋግሮ ይደራረብና እንደአስፈላጊነቱ የቲማቲም ስልስ ወይም ሞርታዴላ ወይም ቺዝ፥... በላዩ ላይ ተደርጎበት የሚበላ የምግብ አይነት።

**ፒንሳ** ስ ብረታብረቶችን ቆንጥጦ ለመያዝ፥ ለሽቦ መቁረጫ፥ ለምስማር መንቀያ፥... የሚያገለግል አነስተኛ መሳሪያ።

**ፒያኖ** ስ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.) ።

**ፒጃማ(ቢጃማ)** ስ በሱሪ፥ በቀሚስ፥... መልክ የሚዘጋጅና ለመኝታ ጊዜ ብቻ የሚያገለግል ሰፋ ያለ ልብስ።

**ፒፓ** ስ የትንባሆ ማጨሻ።

**ፓ** የ "ፐ" ፊደል ራብእ ዘር።

**ፓራሹት** ስ ከአይሮፕላን ዘሎ አየር ላይ እየተንሳፈፉ ቀስ በቀስ ምድር ላይ ለማረፍ የሚያገለግል ጃንጥላ መሰል መሳሪያ፤ ጃንጥላ።



ፓራሹት

**ፓርላማ** ስ 1. የመንግስት መማክርት ጉባኤ።2. መማክርቱ ጉባኤ የሚያደርጉበት አዳራሽ።

**ፓርቲ** ስ 1. ተመሳሳይ አስተሳሰብ፥ እምነትና አላማ ባላቸው ሰዎች የሚቋቋምና የራሱ የሆነ ደንብና ፕሮግራም የሚኖረው አካል (ብዙውን ጊዜ በፖለቲካ መስመር)።2. ብዙውን ጊዜ ዳንስ የሚኖርበት ግብዣ።

**ፓርክ** ስ በተፈጥሮ የሚገኙ፥ ልዩልዩ አውሬዎችና አእዋፍ የሚኖሩበት፥በመንግስት ተከልለሉ ሰዎች እንዲጎበኙት የሚደረግ ቦታ።

**ፓስቲ** ስ የቶርኖ ዱቄት ሊጥ በስሱ ከተዳመጠ በሂላ በዘይት የሚጠበስ የምግብ አይነት።

**ፓስቲኒ** ስ የማካሮኒ አይነት።

**ፓስታ** ስ በተወሰነ ቁመትና ውፍረት ተሸምልሎ ከተቆራረጠ የስንዴ ዱቄት ሊጥ ተዘጋጅቶ ከደረቀ በሂላ ተቀቅሎ የሚበላ የምግብ አይነት።

**ፓስታል ፉርኖ** ስ እንደ ዳቦ ሆኖ ከፓስታ የሚሰራ ምግብ።

**ፓስፖርት** ስ ስለአንድ ሰው ማንነት ተፈላጊውን መግለጫ የያዘና ግለሰቡ ከአገር ውጭ እንዲዘዋወር የሚያስችለው በመንግስት የሚሰጥ ሰነድ ወይም መታወቂያ።

**ፓትርያርክ** ስ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከፍተኛው ማእረግና ስልጣን ያለው መንፈሳዊ መሪ ወይም መንፈሳዊ አባት።

**ፓኬት** ስ መጠኑ አነስተኛ የሆነ እቃ የያዘ ጥቅል፤ እሽግ።

**ፓኮ** ስ ዝ.ከ.

**ፓይለት** ስ አይሮፕላን አብራሪ።

**ፓፓያ (ፓፓዬ)** ስ ለስላሳና ጣፋጭ የሆነ፥ ባብዛኛው ሞላላ ቅርፅ ያለውና ከጥቁር አዝሙድ ከፍ የሚሉ ጥቋቁር ዘሮች ያሉት የሚበላ የፍራፍሬ አይነት፤ ፍሬውን የሚያፈራው ተክልም ፓፓያ ይባላል።

**ፔ** የ "ፐ" ፊደል ሃምስ ዘር።

**ፔሬድ** ስ ክፍለ ጊዜ።

**ፔርሙዝ** ስ የተፈላ ፈሳሽ (ሻይ፥ ቡና፥...) ሳይቀዘቅዝ ለረዥም ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሰአት በውስጡ እንዲቆይ የሚያደርግ እቃ።

**ፔቲካሽ** ስ ጥቃቅን እቃዎችን ለመግዛት ወጪ የሚሆን ገንዘብ (በመስሪያ ቤት አካባቢ)።

**ፔኒሲሊን** ስ ጀርሞች እንዳያድጉ ወይም

እንዳይራቡ የሚከላከል ፀረ ባክቴሪያ የሆነ መድሃኒት።

**ፔዳል** ስ ብስክሌት በሚነዳበት ጊዜ የእግር ጫማ የሚያርፍበትና ካቴናውን ለማሽከርከር የሚረዳ መርገጫ።

**ፔዳጎጂ** ስ የማስተማር ሙያ ሳይንስ።


**ፕሉቶ** ስ ከፀሃይ ጀምሮ ሲቆጠር በርቀት ዘጠነኛ ሆኖ የሚገኝና በፀሃይ ዙሪያ ከሚሽከረከሩት ፕላኔቶች አንዱ (በተጨማሪ ፕላኔትን ተመ.)።

**ፕላስተር** ስ በአንድ በኩል ሙጫነት ያለው ሆኖ ከጨርቅ ወይም ከፕላስቲክ የሚሰራ ማጣበቂያ።

**ፕላስቲክ** ስ በቀላሉ ሊተጣጠፍና ልዩ ልዩ ቅርፅ ሊይዝ የሚችል፥ ውሃ የማያሳልፍ፥ እሳት በቀላሉ የሚያቀልጠውና እንደ ዝናብ ልብስ፥ ባልዲ፥ ጀሪካን፥... ያሉ ነገሮች የሚሰሩበት በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽነት የሚገኝ ቁስ።

**ፕላቲነም** ስ ግራጫ መልክ ያለውና ከብረት ክፍል የሆነ ንጥረ ነገር።

**ፕላኔት** ስ. እንደ መሬት ያለ፥ በፀሃይ ዙሪያ የሚዞርና በህዋ ውስጥ የሚገኝ አካል (ሜርኩሪ፥ ቬኑስ፥...) ።




ፕላኔት

**ፕላን** ስ 1. እቅድ 2. ንድፍ።

**ፕላን አወጣ** ፕላን (እቅድ) ነደፈ፥ አዘጋጀ።

**ፕላዝማ** ስ በሰውነት ውስጥ የደም ሴሎችን የሚሸከም ቢጫ መሰል ፈሳሽ።

**ፕሬስ** ስ 1.ጋዜጦች፥ መፅሄቶች፥ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ዘገባዎች።2. በጋዜጠኝነት ሙያ የተሰማሩ ሰራተኞች ስራቸውን የሚያካሂዱበት መስሪያቤት ወይም ድርጅት።

**የፕሬስ መግለጫ** በመንግስት አካል፥ በፖለቲካ ፓርቲ፥... የሚሰጥና በመገናኛ ብዙሃን የሚገለፅ ኦፊሴላዊ መግለጫ።

**የፕሬስ ነፃነት** ህዝብ ሊያውቃቸው የሚገቡ ዜናዎችንና ሚዛናዊ አስተያየቶችን ያለምንም ተፅእኖና ፍራቻ በነፃ የመግለፅ መብት።

**ፕሬስ ኮንፈረንስ** ስለአንድ አቢይ ጉዳይ በሚመለከተው አካል በኩል በመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ ይፋ ለማድረግ የሚካሄድ ቃለ ምልልስ፤ ጋዜጣዊ መግለጫም ይባላል፡

**ፕሬዚዲዬም** ስ በዋናዋና የመንግስትና የፓርቲ ስብሰባዎች ወይም ጉባኤዎች ላይ ስብሰባዎችን ወይም ጉባኤዎችን የሚመራና አመራር የሚሰጥ የሰዎች ስብስብ ወይም የበላይ አካል።

**ፕሬዚዳንት** ስ የአንድ አገር ወይም ድርጅት፥... የበላይ መሪ፥ ሹም።

**ፕሮቲን** ስ እንደስጋና እንቁላል ባሉ የምግብ አይነቶች ውስጥ የሚገኝና ለሰውነት ግንባታና ለጤንነት በጣም አስፈላጊ የሆነ አልሚ ምግብ።

**ፕሮቴስታንት** ስ 1. በዘመነ ተሃድሶ (ሪፎርሜሽን) ከሮማ ቤተክርስቲያን ተገንጥሎ የወጣ የክርስትና ሃይማኖት ቅርንጫፍ። 2. ከላይ የተጠቀሰው ሃይማኖት ተከታይ።

**ፕሮቶኮል** ስ በመንግስት አመራር አባላትና አካላት አካባቢ ልዩ ልዩ ክንዋኔዎችንና ስነስርአቶችን የሚመለከት የማእረግ ደረጃ ቅደም ተከተል።

**የፕሮቶኮል ስምምነት** ስ በሃገሮች መካከል የሚደረግ የትምህርት፥ የባህል፥ የኢኮኖሚ፥... ስምምነት፥ ውለታ (ውል)።

**የፕሮቶኮል ሹም** ስ የመንግስትን የፕሮቶኮል ስነስርአት የሚያስከብር ሃላፊ።

**ፕሮጀክተር** ስ ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀሱ የፊልም ስእሎችን በነጭ ሰሌዳ ላይ ለማሳየት የሚያገለግል መሳሪያ።

**ፕሮጀክት** ስ ከለት ተእለት መደበኛ ስራ በተለየ ሁኔታ አንድን ስራ ለማከናወን የተዘረጋ እቅድ።

**ፕሮግራም(መርሃ ግብር)** ስ 1. አንድ ተግባር የሚከናወንበት የተወሰነ የጊዜ ክልል። *የቴሌቪዥን ፕሮግራም ስንት ሰአት ላይ ይጀምራል?* 2. እቅድ። *ኑሮውን በፕሮግራም የሚመራ ሰው ነው።* 3. የተወሰነ የጊዜ ርዝመት የተመደበላቸው ድርጊቶች ዝርዝር። *የስብሰባው ፕሮግራም ደርሶሃል?*

**ፕሮግራም አወጣ** እቅድ ነደፈ፥ የተለያዩ ስራዎች በቅደም ተከተል የሚሰሩበትን ጊዜ መደበ።

**ፕሮፌሰር** ስ በዩኒቨርስቲ፥ በኮሌጅ፥ በሙያ ጥናት ተቋም ውስጥ በሚያደርገው ምሁራዊ ስራ (በጥናትና ምርምር፥ በማስተማር፥...) ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሳደረገ ሊቅ ወይም ምሁር የሚሰጥ ማእረግ።

**ፕሮፌሽናል** ቅ በአንድ የሙያ ዘርፍ ሰልጥኖ በቂ እውቀት ያለውና በዚያው ሙያ የሚተዳደር፤ ባለሙያ::

**ፕሮፌሽን** ስ በስልጠና የሚገኝ ሙያ::

**ፕሮፓጋንዳ** ስ አንድን የተወሰነ ሃሳብ ወይም እምነት በተለያየ ስልትና የስርጭት ዘዴ በማስተላለፍ የህዝብን አስተያየት ለመሳብ፥ ድጋፍ ለማግኘትና አመለካከትን ለመቀየር የሚደረግ ጥረት::

**ፖ** የ "ፐ" ፊደል ሳብእ ዘር::

**ፖለቲካ** ስ ከስልጣንና አገር ከማስተዳደር አኳያ አንድ መንግስት ከሚያስተዳድረው ህዝብና ከሌሎች መንግስታት ጋር ያለው ግንኙነት ሁኔታ፥ አመለካከት፥ እንቅስቃሴ፤ ስነመስተዳድር ወይም የመስተዳድር ሳይንስ::

**ፖለቲካ ተናገረ** በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት የሚነቅፍና አመፅ ሊያስነሳ የሚችል ነገር ተናገረ::

**የፖለቲካ ጥገኛ** ስ በፖለቲካ ምክንያት ከአገሩ ተሰዶ በባእድ አገር የሚኖር ሰው::

**የፖለቲካ ጥገኝነት** በፖለቲካ ምክንያት ከራስ አገር በመሰደድ በባእድ አገር መኖር::

**ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ** ስ በምርት ሂደት ውስጥ በሰዎች መካከል የሚፈጠረውን የኢኮኖሚ ግንኙነት (ምርትን፥ ክፍፍልን፥ ልውውጥንና ፍጆታን) የሚገዙ ማህበራዊ ህጎችን የሚያጠና ሳይንስ::

**ፖለቲከኛ** ስ የፖለቲካ ስራ የሚሰራ የፖለቲካ ሰው::

**ፖሊሲ** ስ በመንግስት፥ በፖለቲካ ፓርቲ ወይም በኩባንያ የሚዘጋጅ የተግባር መመሪያ::

**ፖሊስ** ስ ሰላምና ፀጥታን እንዲሁም ህግን የሚያስከብር፥ ወንጀልን የሚከላከል፥ በመንግስት የተቀጠረ መለዮ ለባሽ::

**ፖሊስ ጣቢያ** ስ ፖሊስ ተግባሩን የሚያከናውንበት ፅህፈት ቤት::

**ፖሊዮ** ስ ልምሻ::

**ፖምፕ** ስ የመኪና፥ የብስክሌት ጎማን፥...አየር ለመሙላት የሚያገለግል መሳሪያ::

**ፖርቶመጋሊያ** ስ እንደ ታክሲ፥ አውቶቡስ፥... ባሉ መኪናዎች አናት ላይ የሚገጠምና ለእቃ መጫኛ ወይም ማስቀመጫ የሚያገለግል የመኪና እቃ::

**ፖስተር** ስ አንድን ነገር ለማስተዋወቅ ወይም ለማስተማር ሲባል ብዙ ህዝብ ሊያየው በሚችልበት ቦታ በትልልቅ ወረቀት የሚለጠፍ የማስተማሪያ ወይም የማስተዋወቂያ ስእልና ፅሁፍ::

**ፖስታ** ስ ብዙውን ጊዜ በፖስታ ቤት በኩል ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ የሚላክ ፅሁፍ ወይም መጠኑ አነስተኛ የሆነ ሌላ እቃ የሚከተትበት የተለያየ መጠን ያለውና ሊታሸግ የሚችል የወረቀት ከረጢት::

**ፖስተኛ** ስ ፖስታ የሚያመላልስ ሰራተኛ::

**[የ] ፖስታ ሳጥን** ስ 1. በፖስታ ቤት በኩል የሚላኩ ደብዳቤዎች፥ መፅሄቶች፥... የሚከተቱበት ወይም የሚጠራቀሙበት ሳጥን:: 2. የሚላኩላቸው ደብዳቤዎች፥ መፅቶች፥... ይጠራቀሙበት ዘንድ ተገልጋዮች ከፖስታ ቤት የሚከራዩትና መለያ ቁጥር ያለው ሳጥን::

**ፖስታ ሳጥን ቁጥር** ስ ለፖስታ ሳጥን የሚሰጥ መለያ ቁጥር::

**ፖስታ ቤት** ስ የአገልግሎት ዋጋ በማስከፈል ፖስታዎችን እየተቀበለ በአድራሻቸው የሚልክ፥ የሚያስተላልፍ፥ የሚያድል መንግስታዊ መስሪያ ቤት::

**ፖታሽ** ስ ሳሙና፥ ማዳበሪያ፥... ለመስራት የሚያገለግል ኬሚካል::

**ፖፖ** ስ የሽንት እቃ፤ መክፈያ::